ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ
ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት /ቴሲስ/

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን
በማስተማር ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ
ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
ጌታቸው አዱኛ

ሰኔ/1986 ዓ.ም.

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ምንባቦች ቅንጅት ደረጃ


በ

ጌታቸው አኛ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


<u>የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ</u>

________________ ________________

አማካሪ

________________ ________________

ፈታኝ

________________ ________________

ፈታኝ

________________ ________________

ፈታኝ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድሕረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአሥረኛ ክፍል የቀረበው የአማርኛ ቋንቋ
የማስተማሪያ ምንባቦች ዝግጅት ደረጃ

በ

ጌታቸው ለማ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ</u>

[illegible] (ዶር.) ______

አማካሪ

[illegible] (ዶ.ር) ______

ፈታኝ

[illegible] ______

ፈታኝ

______ ______

ፈታኝ

## ምስጋና

ከጥናቱ መነሻ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለመሰለቸትና ትርፍ ጊዜያቸውን ሳይቆጥቡ ረቂቁን ደጋግመው በማንበብና ተገቢውን ቅርጽ በማስያዝ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ::

በንግድ ሥራ ኮሌጅ የቋንቋ መምህር የሆኑት ዶክተር ግረው ዘውዴ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መጽሐፍችንና ፅሑፍችን በመስጠትና የአሠራር ዘዴን በመጠቆም ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

በትምህርቱ ላይ በቆየሁባቸው ሦስት ዓመታት ቤተሰብ የማስተዳደርን፤ በተለይም ልጆች የማሳደግን ከባድ ሐላፊነት ከመሸከም በተጨማሪ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፏ ለአፍታም ላልተለየኝ ውድ ባለቤቴ ለወይዘሮ ንጏቷ አሸብር የተለየ ምስጋና አቀርባለሁ::

ትምህርቱን ስከታተል እንደወትሮው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ያደረጉልኝ አቶ ሸመለስ ዋቅጅራ ከነቤተሰቡ፤ ሃ አለቃ ጥላሁን ፍሬሕይወት ከነቤተሰባቸው፤ አቶ ጌታቸው ሁሪሳ ከነቤተሰቡ ሻለቃ ጌታቸው ፍቃዴ፤ አቶ ጉዛዬ አርጋው ከነቤተሰቡ፤ ወ/ሮ አፀደ ቱፋ ከነቤተሰቧ፤ ወ/ሮ ቀንጃት ፈይሣ፤ አቶ አማሪ ላቀው፤ አቶ ጌታቸው ዘለቀና ስማቸው ያልተጠቀሰ ጓደኞቼ ባለውለታዬ ናቸው::

የዚህ ጥናት ውጤቱ አስተማማኝ እንዲሆን ጊዜያቸውን ሰውተው መጠይቆችን በመሙላት ለተባበሩኝ በናሙናነት ለተመረጡ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን፤ ዩኒት መሪዎችን፤ መምህራንንና ተማሪዎችን ከልብ አመሰግናለሁ::

[illegible] ጽሁፉን በጥራት ለተየበችልኝ ወ/ት አስቴር አስገዶ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የታለመው በ1984 ዓ.ም. ታትሞ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ማገልገል የጀመረውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች ብቃት ለመገምገም ነው:: ገምገማውን ለማካሄድ የመማሪያ መጽሐፍና የመርሀ-ትምህርቱ ግንኙነት፣ የመጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ ፍላጎት ያላቸው ቀረቤታ፣ የምንባቦቹ ተነባቢነትና ተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብበው ለመረዳት ያላቸው ችሎታ ምን ያህል እንደሆነ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል::

የመማሪያ መጽሐፉ መለመጃዎች ይዘቶችና የመርሀ-ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች /ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ገምገማዎች/ በተዛማጅ ቀመር ተሰልተው የተገኙት ውጤቶች በ"ቲ" ቴስት ሲፈተኑ ሁለቱ መማሪያዎች ግንኙነት እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል::

የመጽሐፉ ምንባቦች ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ስላላቸው ቅርበት ለማወቅ እንዲረዳ መጠይቆች ለመምህራንና ለተማሪዎች ተበትነዋል:: ከመጠይቆቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ምንባቦቹ ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮች...ወዘተ ከሚጎድሉዋቸው በስተቀር በከፍተኛ ደረጃ ለፍላጎታቸው እንደሚስማሙ የተማሪዎቹ መልሶች አመለከተዋል:: ከመምህራን የተሰጡት መልሶች የሚጠቁሙት ተማሪዎቹ አንብበው ባይረዱዋቸውና የተለያዩ ስልቶች /ዘይቤያዊ አነጋገሮች፣ ፈሊጦች፣ ተረትና ምሳሌዎች../ ቢጎድሉዋቸውም ለተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ለምድና አካባቢ በመካከለኛ ደረጃ እንደሚስማሙ ያስረዳሉ::

ለሁለተኛ ደረጃ ምንባቦች ተነባቢነት መለኪያ ከሚያገለግሉ 4 ቀመሮች መካከል በፍለሽ ቀመርና በፍሪ ግራፍ በመጠቀም ተነባቢነታቸውን ለመለካት ተሞክሯል:: 3 ናሙና ምንባቦችን ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ በመውሰድ በተደረገው ስሌት ከ2ቱም ቀመሮች የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ምንባቦቹ ተነባቢነት እንደሌላቸው ነው:: ምንባቦቹ በተናጠልም ሆነ በጋራ ሲታዩ ለድህረ-ምረቃና ለ7ኛ በላይ የክፍል ደረጃ ላላቸው ሰዎች ብቻ የሚነበቡ ሆነው ተገኝተዋል::

ለመጨረሻው ጥያቄም የተገኘው መልስ አሉታዊ ነው:: ከመግሪያ መጽሐፉ በተወሰዱ 3 ናሙና ምንባቦች አማካይነት የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ደረጃ ለማወቅ እንዲያስችል ለ90 ተማሪዎች የግንዛቤ ሙከራ ተሰጥቶ ነበር:: በተገኘው ውጤት አተረጓጐም መሠረት በጧት ከሚቀጠሩት ተማሪዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ ምንባቦቹን አንብበው መረዳት አይችሉም::

ከላይ ከተገኙት ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፤

1/ የመግሪያ መጽሐፉና የመርሀ-ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች ግንኙነት ስለሌላቸው፤ የመጽሐፉን መለመጃዎች ይዘቶች ከመርሐ ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች አንጻር በማዘጋጀት የግንኙነታቸው ስፋት የሚጠብበት መንገድ መቀየስ አለበት፤

2/ የመግርያ መጽሐፉ ምንባቦች የሚገድሉዋቸው የተለያዩ ስልቶች ለክፍሉ ደረጃ በሚመጥን ሁኔታ በመግሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚጠመሩበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፤

3/ ቀመሮቹ ለአማርኛ መምሪያነት ማገልገል መቻል አለመቻላቸውን በጥናት ማረጋገጥ፤ የምንባቡንም ተነባቢነት ከዚህ አንፃር ከፍ ለማድረግ መሞከር፤

4/ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት መጣርና የምንባቦቹንም ክብደት ከተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ጋር ለማመጣጠን መሞከር::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ማውጫ

ገፅ

ምስጋና ........................................ ሀ

አጠቃሎ ........................................ ለ

ምዕራፍ 1

መግቢያ

1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር ........................ 1
1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................ 6
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................ 6
1.4 የጥናቱ ወሰን ........................ 7
1.5 የደነኑ ፅንሰ–ሀሳቦች ገላጭ ቃላት ማብራሪያ ......... 8

ምዕራፍ 2

የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ........................ 11

2.1 የቋንቋ መርሀ–ትምህርት ምንነት ................ 11

2.1.1 ሰዋሰዋዊ መርሀ–ትምህርት ............ 12
2.1.2 ሁኔታዊ መርሀ–ትምህርት ............ 12
2.1.3 ተግባቦታዊ መርሀ–ትምህርት ............ 13

2.2 የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ ................ 14
2.3 የመርሀ–ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ ግንኙነት ......... 16
2.4 የምንባብ አመራረጥ ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር ....... 21
2.5 የምንባቦች ተነባቢነት ........................ 26

2.5.1 የተነባቢነት ቀመሮች ................ 30
2.5.1.1 የደለቻለ ቀመር ............ 35
2.5.1.2 የፍለሽ ቀመር ............ 36
2.5.1.3 የጡግፍርድ ሠንጠረዥ ......... 36
2.5.1.4 የኤድዋርድ ፍሪ ግራፍ ....... 36

2.6 የግንዛቤ ሙከራ ........................ 37

. . . /

ገጽ

ምዕራፍ 3


የጥናቱ ዘዴ .............................. 40

3.1 የመርሀ-ትምርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ግንኙነት .... 40

3.2 የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦችና የተማሪዎች ፍላጎት ........ 43

3.3 የምንባቦቹ ተነባቢነት ..................... 45

3.3.1 የፍለሽ ቀመር .................... 45

3.3.2 የኢድዋርድ ፍሪ ግራፍ ............... 47

3.4 የግንዛቤ ሙከራ ........................ 47

3.4.1 የናሙና ምንባቦች አመራረጥ ............ 47

3.4.2 የናሙና ተማሪዎች አመራረጥ ............ 48

3.4.3 የሙከራው አደረጃጀት ................ 48

3.4.4 የሙከራው አሰጣጥ .................. 48

3.4.5 የነጥብ አሰጣጥና የአተረጓጎም ዘዴ ........ 49


ምዕራፍ 4


የመረጃ ትንታኔና ማብራሪያ .......................... 50

4.1 የመረጃ ትንተና ........................... 50

4.1.1 ከመርሀ-ትምህርትና ከመማሪያ መጽሐፉ የተገኙ መረጃዎች ትንተና .................. 50

4.1.2 ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................... 58

4.1.2.1 ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች .... 58

4.1.2.1.1 በክፍል አንድ ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ..... 59

4.1.2.1.2 በክፍል ሁለት ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ..... 59

ገጽ


4.1.2.1.3 በክፍል ስስት ለተማሪዎች
የቀረቡ ጥያቄዎች ....... 64
4.1.2.1.4 በክፍል አራት [illegible]ተማሪዎች
የሰጧቸው አስተያየቶች..... 68

4.1.2.2 ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ........... 69

4.1.2.2.1 በክፍል አንድ ለመምህራን
የቀረቡ ጥያቄዎች ....... 69
4.1.2.2.2 በክፍል ሁለት ለመምህራን
የቀረቡ ጥያቄዎች ....... 70
4.1.2.2.3 በክፍል ሦስት ለመምህራን
የቀረቡ ጥያቄዎች ....... 73
4.1.2.2.4 በክፍል አራት ከተሰጡት
የመምህራን አስተያየቶች
የተገኙ መረጃዎች ....... 77

4.1.3 ከተነባቢነት ቀመሮች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 79

4.1.3.1 ከፍለሽ ቀመር የተገኙ መረጃዎች ትንተና .... 79
4.1.3.2 የፍሪ ግራፍ ውጤት ትንታኔ ........... 80

4.1.4 ከገንዘቤ ሙከራ የተገኙ ውጤቶች ................. 82

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ......................... 84

4.2.1 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትና የመማሪያ
መፅሐፉ ግንኙነት ......................... 84
4.2.2 የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦችና የተማሪዎች ፍላጎት ....... 86
4.2.3 የምንባቦቹ ተነባቢነት ..................... 89
4.2.4 የገንዘቤ ሙከራ ውጤት ትንተና ................. 91

ምዕራፍ 5

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ............................ 92

ገፅ


5.1. ማጠቃለያ.................. 92

5.2. የመፍትሔ ሃሳቦች ............ 94

አምደ=ቃላት ............................ 97

ማስታወሻዎች ............................ 98

ዋቢ መጻሕፍት............................ 99

## የሠንጠረዥ ዝርዝር


ሠንጠረዥ ገጽ

1 የአሥረኛ ክፍል ሥርዐ-ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ግምገማዎች.............................. 40

2 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይዘቶች.................................. 41

3 የናሙና ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል ምድቦችና የተማሪዎች ብዛት.................................. 43

4 የፍላሽ ቀመር የንባብ ቅለት ትርጉም.................. 46

5 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ሥርዐ-ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች መግለጫ ........................................ 50

6 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ሥርዐ-ትምህርት ይዘቶች መግለጫ...... 51

7 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ሥርዐ-ትምህርት ክንውኖች መግለጫ..... 52

8 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ሥርዐ-ትምህርት ግምገማዎች መግለጫ ........................................ 53

9 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይዘቶች መግለጫ ........................................ 54

10 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይዘቶችና የሥርዐ-ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች ግንኙነት.............. 55

11 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሥርዐ-ትምህርት ይዘትና የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መግለጫ.............. 56

12 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሥርዐ-ትምህርት ክንውኖችና የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መግለጫ......... 56

13 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሥርዐ-ትምህርት ግምገማዎችና የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መግለጫ......... 57

14 ስለተማሪዎቹ የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ............ 59

15 ፍላጎትን በሚመለከት የተማሪዎች መልሶች መግለጫ............ 60

16 ስለመጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎች መልሶች መግለጫ............ 61


.../

ሰንጠረዥ ገጽ


17. ፍላጎትን በሚመለከት የተማሪዎች መልሶች መግለጫ................... 64

18. ምንባቦቹ ለችሎታቸው ስላላቸው ቀረቤታ የተማሪዎች መልሶች መግለጫ.....65

19. ምንባቦቹ ከዕድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት
የተማሪዎች መልሶች መግለጫ ........................... 66

20. ስለምንባቦቹ ይዘትና ገለጻነት በተማሪዎች የተሰጡ መልሶች
መግለጫ ................................. 67

21. በክፍል አንድ ከመምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ....... 69

22. ፍላጎትን በሚመለከት የመምህራን መልሶች መግለጫ.................. 70

23. ስለምንባቦቹ አጠቃቀም የመምህራን መልሶች መግለጫ............... 72

24. ስለምንባቦቹ ይዘት፣ ክብደትና ምጣኔ ለጠየቁት ጥያቄዎች ከመምህራን
የተገኙ መልሶች መግለጫ........................... 72

25. ተማሪዎቹ ስለምንባቦቹ ያላቸውን አመለካከት በሚመለከት ለቀረቡት
ጥያቄዎች መምህራን የሰጡዋቸው መልሶች መግለጫ................. 73

26. ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ለምድ ስላላቸው ቀረቤታ የመምህራን መልሶች
መግለጫ.................................. 74

27. ስለምንባቦቹ ገለጻነት፣ ምጣኔና ይዘት ለቀረቡት ጥያቄዎች የመምህራን
መልሶች መግለጫ............................. 75

28. ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ለተጠየቁት
ጥያቄዎች መምህራን የሰጧቸው መልሶች መግለጫ................. 77

29. በፍሌሽ ቀመር መሠረት የተገኘው የስሰቱ ናሙና ምንባቦች ውጤት
መግለጫ ................................. 79

30. የናሙና ምንባቦቹ የቀለም ብዛት፣ የዓ.ነገር ዝርመትና የተገመቱለት
የክፍል ደረጃ ............................. 81

31. የናሙና ተማሪዎች የግንዛቤ ሙከራ ውጤት የድግግሞሽ ሥርጭት ....... 82

32. በየናሙና ትምህርት ቤቶች የናሙና ተማሪዎች የመረዳት ደረጃ........ 83

# የአባሪዎች ዝርዝር


| አባሪዎች | ገጽ |
| --- | --- |
| ሀ. የፍሬ ገራፍ .............................. | 106 |
| ለ. የተዛምዶ ቀመር ስሌትና የአተረጓጎም ዘዴ ........... | 107 |
| ሐ. የተማሪዎች መጠይቅ ......................... | 108–114 |
| መ. የመምህራን መጠይቅ ......................... | 115-122 |
| ሠ. የቀለም አቀጧጠር .......................... | 123 -129 |
| ረ. የገንዘብ ሙከራ ናሙናዎች ..................... | 130–134 |
| ሰ. የገንዘብ ሙከራ ናሙናዎች መልሶች ................ | 135–137 |
| ሸ. የገንዘብ ሙከራ ውጤት ...................... | 138–140 |

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር

የመጀመሪያው የአማርኛ መርሀ=ትምህርት[1] ከተዘጋጀበት ከ1947=48[2] ጀምር /አስፋውና መሪስን 1976፡372/ አማርኛ በትምህርት ዓይነትነትም ሆነ በማስተማሪያ ቋንቋነት ሲሰጥ ቢቆይም ለቋንቋው ማስተማሪያነት ታስቦ የተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሐፍ አልነበረም:: በትምህርት ዓይነትነት የመሰጠቱ ሂደት ቀደም ብሎ በሚሲዮን፣ በኋላም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በመደበኛነት ሲሰጥ ቆይቷል:: ቋንቋው በመደበኛ የትምህርት ዓይነትነት መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ የተለያዩ መርሀ=ትምህርቶች በተለያዩ ጊዜያት መዘጋጀታቸው ቢታወቅም ከመርሀ=ትምህርቱ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ የማስተማሪያ መጽሐፎች አልነበሩም:: ለማስተማሪያነት ተመድበው ያገለግሉ የነበሩት መጽሐፎች ለዩ ለዩ ደራሲዎች እንዲነበቡላቸውና እንዲሸጡላቸው በማሰብ ያዘጋጁዋቸው መጽሐፎች ነበሩ /አስፋውና መሪስን 1976፡408/:: እነዚህ መጽሐፎች ለማስተማሪያነት ሆነ ተብለው የተዘጋጁ ሳይሆኑ የተለያዩ ደራሲዎች የጻፏቸው ለብወለዶች፣ ታሪክ ነክና የመሳሰለ ይዘት ያላቸው ነበሩ:: ይህም፣ መጽሐፎቹ ለዚህ ክፍል "ይበጃሉ" ወይም "ይመጥናሉ" ተብለው የተመረጡ አለመሆናቸውን ያሳያል::

መጽሐፎቹ በማስተማሪያነ የተመረጡ ባለመሆናቸው እርስ በራሳቸው ይዘታዊ ግንኙነት የሌላቸው፣ የመጀመሪያው ክፍል ለሚቀጥለው ክፍል መሠረት የማይጥሉ፣ በመካከላቸውም ተከታታይነት የማይታይባቸውና ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን የክፍል ደረጃ ትምህርት ሳይማሩ የሚቀጥለውን ክፍል ደረጃ ትምህርት ሊከታተሉ ስለሚችሉ የትምህርቱ አሰጣጥ ተለጣጣቂነት እንደሌለው /አስፋውና መሪስን 1976፡408/ ያስረዳሉ:: ይህም በወቅቱ ያገለግሉ የነበሩት የማስተማሪያ መጽሐፎች ብቃት ናርአቸው ተመጣጣኝነትና ተከታታይነታቸው ታስቦ የተመረጡ አለመሆናቸውን ያሳያል::

ኢያሌው አሰፋው እስከ 1984 ዓ.ም. የነበረትን የማስተማሪያ መጽሐፍት ቅድመ–አብዮትና ድህረ–አብዮት የነበረት የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍት የነበረባቸውን ከፍተኛና ጉልህ ድክመቶች ሲገለጽ፣ ከ1966 ዓ.ም. በፊት የነበረት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍት ለመማሪያ መጽሐፍትነት ያልተዘጋጁ፣ በወቅቱ ያገለገሉ የነበረትም በግለ የተደረሱ የአማርኛ ለብወለድ መጽሐፍት፣ የታሪክ መጽሐፍትና ከእንግሊዘኛ የተተረጎሙ መጽሐፍት ነበሩ:: እነዚህ መጽሐፍት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስላልተዘጋጁ በአቀራረባቸው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሌላቸው፣ ይዘታቸው ለሚቀርቡለት የክፍል ደረጃ የማይመጥንና የአንዳንዶቹ የቋንቋ አወቃቀር ለዛ የሌለው እንደነበረ አስረድቷል /1985 ዓ.ም.፣53/::

ይህ የመማሪያ መጽሐፍት ድክመት የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ ካለመሆኑም በተጨማሪ በመምህሩም ሆነ በተማሪው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ተጽዕና ተማሪው አንድን የክፍል ደረጃ በጨረሰ ቁጥር በእያንዳንዱ ተማሪ ላይ ሊታይ የሚገባውን የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ለማስከተል ያላስቻሉ ከመሆናቸውም በላይ መምህራኑ ሊያበረክቱ የሚገባቸውን አስተዋጽኦ በእጅጉ ዝቅ አድርጓታል/ 1985 ዓ.ም.፣53/::

[illegible] ከላይ ከተሰጡት አስተያየቶች የምንረዳው አጠቃላይ ቁምነገር ከ1966 ዓ.ም. የማስተማሪያ መጽሐፍት ሆነ ተብለው ለማስተማሪያነት ማለትም ለተማሪዎቹ የባሕርይ ለውጥ፣ የአስተሳሰብ ዕድገትና ከመሳሰሉት ግንዛቤዎች እንዳልተዘጋጁና ያገለገሉ የነበረትም ቢሆኑ በተለያዩ ደራሲያች ለተለያዩ ዓላማዎች /ለለብ ወለድ፣ ለታሪክ፣ ለኢለብወለድ/ ማስተማሪያነት፣ በተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች የቀረቡ እንደነበሩ ነው:: ይህም በመሆኑ መጽሐፍቱ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉና የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የማያስችሉ ነበሩ:: መምህራንም የሚፈለገባቸውን አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ እንቅፋት እንደሆኑባቸው ከሁለቱ አስተያየቶች መረዳት ይቻላል::

በ1970 ዓመተ ምህረትም የመጀመሪያዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፎች ተዘጋጅተው ይቀረቡ እንጂ ግራታቸውና ለተመደቡለት የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸው፣ እንዲሁም የተፈለጉትን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር ከማስቻል አንጻር ሲታዩ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል የተገኙ የመመረቂያ ጽሑፎች በአዎንታዊ መልክ አይመለከቱዋቸውም:: ለምሳሌ አስፋው አጩና / 1975ዓ.ም.፣28/ የመማሪያ መጽሐፍቱ ከተማሪው ለምድ ጋር የማይጣጣሙ፣ ለአካባቢው ተገባራዊ እንቅስቃሴ እንግዳ የማይሆኑ ምንባቦች እንደያዙና አቀራረባቸው የማይስብ ሆና እንዳገኛቸው ገልጿል:: ጠሰቡንም ሲያጠቃልል የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍት አቀራረብ የማይስብ አሰደሳች ታሪኮችን ያልያዘ፣ በሥነ ጽሁፍ ላይ ያላተኮረ፣ ከተማሪዎቹ ችሎታ በላይና ገቢራዊ የማይሆኑ ጥያቄዎችን ያካተተ በመሆኑ የአማርኛ ትምህርት በተማሪዎቹ እንዲጠላ ማድረጉን አስረድቷል::

ስለሞን ገዛው /1978 ዓ.ም./ ከ1966-1976 ዓ.ም. ያገለገሉ የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍት የማስተማሪያነትን ዓላማ የሚያሟሉ፣ በከፊል የሚያሟሉና የማያሟሉ መሆናቸውን መሠረት በማድረግ የመመረቂያ ጽሑፉን በሦስት ከፍሎ ለማሳየት ሞክሯል:: ብርሃኑ ዘሪሁንም /1978 ዓ.ም./ እንደዚሁ የማስተማሪያ መጽሐፎቹ ድክመት እንዳለባቸው አስረድቷል:: ደሴ መሉዓለም /1972 ዓ.ም.፣ 58/ በማስተማሪያ መጽሐፍቱ ላይ ድክመት መኖራቸውን አመልክቶ ይህም ድክመት በትምህርትም ሆነ በተማሪዎቹ ትምህርት አቀባበል ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ሲያስረዳ፣ ትምህርቱ በሙሉ በምንባብ ላይ የተመሰረተ፣ ስለቋንቋ ምንነት የማያሳውቅና የሥነ ጽሁፍ ፍቅር የማያሳድርባቸው በመሆኑ ለትምህርቱ የዝቅተኝነት ግምት እንዲሰጥ ማድረጋቸውን ገልጿል:: በነዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጁት የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍት ላይ በተጠናቀረው የድክመት ግምገማ ላይ ጠንከር ያለ ሃሳብ የሰነዘረው አያሌው አስፋው በ1985 ዓ.ም. ባቀረበው የመመረቂያ ጽሑፍ ላይ ነው:: አያሌው /1985 ዓ.ም.፣53/ እንዳብራራው በ1967 ዓ.ም. የተዘጋጁት የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍት ለማስተማሪያነት ሆነ ተብለው ይዘጋጁ እንጂ ከቀድሞ አብዮት መጽሐፍት የሚሻሉት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው በመዘጋጀታቸው፣

ምንባቦችንና መልመጃዎችን በመያዛቸው ነው፣ ሆኖም ይዘታቸው ከቋንቋ ይልቅ ለሌላ የትምህርት ዘርፍ የሚያገለግሉ፣ የተማሪዎቹን ችሎታ የማይመጥኑ፣ መመሪያና ገለጻነት የሌላቸው መልመጃዎችን መያዛቸው፣ የተማሪውን የመማር ስሜት የማይቀሰቅሱና አሰልቺነት የሚታይባቸው ናቸው::

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ከአብዮት በፊትም ሆነ በኋላ ለማስተማሪያነት ያገለግሉ የነበሩት መጽሐፍች በሙሉ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ብቁ እንዳልሆኑ ነው:: በይዘት አመራረጥ፣ በአቀራረብ ስልት ለተማሪዎቹ ለዕድሜ ዕድገ ካላቸው ቀረቤታ አንጻር ሲታዩ የታለመውን የቋንቋ ማስተማር ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጠቃሚነት የሌላቸው ናቸው:: በተለይም በድህረ-አብዮት የተዘጋጁት የማስተማሪያ መጽሐፎች ለአራቱም የክፍለ ደረጃዎች /ከ9ኛ-12ኛ ክፍል/ የተመረጡት የዘቶች /ምርት፣ እርሻ፣ ጤና፣ ፖለቲካ፣.../ ተመሣሣይ በመሆናቸው የተማሪውን የመማር ፍላጎት ሆነ የመምህሩን የማስተማር ፍላጎት በእጅጉ የሚያዳክሙ ከላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ሃሳቦች መረዳት ይቻላል:: በመሆኑም ከመጽፍቱ ምንባብ ይዘቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን የቋንቋ ክሂሎች በተግባር መለክ ለማስተማር ታስበው የተመረጡ ባለመሆናቸው ለቋንቋ ማስተማሪያነት ብቃት የሚጐድላቸው ጽሑፍች እንደሆኑ መገንዘብ አያዳግትም::

የማስተማሪያ መጽሐፍቱ ሲተቹ የቆዩት ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጽሑፎችና በነአስፋው ብቻ ሳይሆን ለሲምፖዚየምና ለሴሚናር በቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ጭምር ነው:: የጥናታዊ ጽሑፍቱ አጠቃላይ ይዘቶች የሚጠቁሙት ሲያገለግሉ የነበሩት የማስተማሪያ መጽሐፍች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ብቃት የሚጐድላቸው መሆናቸውን ነው:

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የሚበቁ ምንባቦች እንደሌሉና የነበሩትም ቢሆኑ ድክመት እንደሚታይባቸው ተመለከቷል፣ ሆኖም እስካሁን ድረስ ምንባቦች ብቃት ያጡበትን ምክንያት ለመመርመርና ለመተንተን የሞከረ ጥናት የለም:: በሌላ አባባል ምንባቦቹ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ብቃት ያጡበት ምክንያት በጥናታዊ ጽሑፎች

አጠቃላይ በሆነ ሞላኩ ይታይ እንጂ 'ከዚህና በዚህ ምክንያት ብቃት የላቸውም፣ ይህ ይጎድላቸዋል...' ተብሎ የቀረበ ዝርዝር የድክመት ዓይነት የለም:: ጥናታዊ ጽሑፉ ምንባቦቹን ብቃት ያሳጧቸውን የጉድለት ነጥቦች ቢያብራሩም ከአጠቃላይ ይዘታቸው መረዳት የሚቻለው ተመርጠው ሲያገለግሉ የነበሩት ምንባቦች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ብቃት እንዳልነበራቸው ነው::

መጽሐፍቱ ብቃት የላቸውም ተብለው በመተቸታቸው ይሁን ወይም ብቃት እንደሌላቸው በጥናት በመረጋገጡ እንደሆነ ባይታወቅም ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩት የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፎች ተወግደው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ አዳዲስ መጽሐፍች በማስተማሪያነት ማገልገል ጀምረዋል:: እነዚህ ለሁለተኛ ጊዜ የተዘጋጁት የማስተማሪያ መጽሐፍች በየክፍል ደረጃው አማርኛን በተሻለ ሁኔታ ለማስተማር ያገለግላሉ ተብለው የተመረጡና በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተገለጹትን ዓለማዎች ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያስችሉ የተገመቱ ምንባቦች አሉዋቸው::

ከአጠቃላዩ የአማርኛ መርሀ-ትምህርት / ት/ሚኒስቴር 1984 ዓ.ም./ ዓላማዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብና መጻፍ በዋናነት የሚጠቀሱ ክሂሎች ናቸው:: በትምህርቱ አማካይነት ለማዳበር የተፈለገውም እነዚህኑ መሠረታዊ የቋንቋ ክሂሎች ሲሆን፣ በተጨማሪም የሥነ ለሣንና የሥነ ጽሑፍ የትምህርት ዘርፎች በዓላማው ውስጥ ተካትተዋል::

በአዲስነት የተዘጋጁት የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍችም እነዚህን ክሂሎች፣ የሥነለሳንና የሥነጽሑፍ ዘርፎችን ያዳብራሉ ተብለው የተገመቱ ምንባቦች ሲኖሩዋቸው፣ ምንባቦቹ እንዴት፣ ለምን ዓላማና በምን መስፈርት እንደተመረጡ አይታወቅም:: በመሆኑም በአዲስነት ተመርጠው ማገልገል የጀመሩት ምንባቦች ለቋንቋ ማስተማሪያነት የቱን ያህል ብቃት እንዳላቸው መመርመርና ማረጋገጥ የተገባ በመሆኑ ይህን ጥናት ማካሄድ አስፈለገ::

## 1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት

የማስተማሪያ መጽሐፎች ጠቃሚነትና አስፈላጊነት አጠያያቂ ባለመሆኑ መጽሐፍቱ በሥራ ላይ መዋል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምር በየወቅቱ ሊተቹ፣ ሊተነተኑና ለመዘኑ ይገባቸዋል:: ይህም የመማር ማስተማሩን ሂደት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በመሆኑም ፣ ይህ ጥናት ተከሄደ ከውጤት ላይ ሲደርስ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ስለሚያስገኝ አስፈላጊነቱ የጉላ ነው::

1.2.1 ከሉት የአሥረኛ ክፍለ ተማሪዎች ፍላጎት፣ እንዲተገበሩ ከሚፈለጉት ዓላማዎች አንጻርና ለደረጃው ተነባቢነት ኖርአቸው ተገቢና ብቁ የሆኑ የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ እንዴት መሆን እንዳለበት ፍንጭ ይሰጣል፣

1.2.2 ለማስተማሪያ ምንባብ አዘጋጆችና መምህራን ስለምንባብ አመራረጥና አዘገጃጀት የመነሻ ወይም የመንደርደሪያ ሐሳብ ይጠቁማል፣

1.2.3 ለወደፊቱ በዚህ መስክ ለሚደረጉት ሰፊ ጥናቶች መንገድ ይከፍታል::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የማስተማሪያ መጽሐፍ ለቋንቋ ትምህርት የሚኖረው አስተዋጽኦና ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው:: በተለይም እንደኢትዮጵያ ባሉ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /እንደ ቪዲዮ ካሴትና የመሳሰሉትን/ ተጠቃሚ መሆን ላልቻሉ አገሮች የማስተማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት ገደብ የለውም::

የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ ከሚይዛቸው ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው ምንባብ ነው:: የአንድ የማስተማሪያ ምንባብ ለቋንቋ ትምህርት ስኬታማነት ተገቢውን ድጋፍ

ያደርጋል ተብሎ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚመረጥ መሆን እንዳለበት የብዙ ምሁራን እምነት ነው:: ምንባቡ በቋንቋ ማስተማሪያነት ብቁ መሆን አለመሆን ተመዝኖና ተመርምሮ መመረጥ እንዳለበትም ምሁራኑ ይስማሙበታል:: ስለዚህ የማስተማሪያ ምንባቡ ብቃት እንዲኖረው በአመራረጡ ላይ ጥንቃቄ ማድረጉ የግድ አስፈላጊ ነው:: ከዚህ አንጻር ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ለአሥረኛ ክፍል ተመርጠው በአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያነት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት አዳዲስ ምንባቦች ሲመረጡ ምን ያህል ጥንቃቄ እንደተደረገና ብቃታቸው ምን ያህል እንደተጠበቀ መመርመሩ አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት አራት ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል::

1. ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡት አዳዲሶቹ የአሥረኛ ክፍል ምንባቦች በመርሀ - ትምህርቱ ላይ የቀረቡትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው ?

2. ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡት የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባቦች የክፍሉን ተማሪዎች ፍላጎት በማሟላት ረገድ ያላቸው ብቃት ምን ያህል የተጠበቀ ነው ?

3. ለክፍሉ የተመረጡት ምንባቦች የተዘጋጁለትን የክፍል ደረጃ የጠበቀ ተነባቢነት አላቸዉ ?

4. የተማሪዎቹ ምንባቦችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ምን ያህል ነው ?

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች በመተንተን ላይ የተመሠረተ ነው:: በዚህም ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች፣ ምንባቦቹ ከመርሀ - ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ፣

የተማሪዎችን ፍላጎት በማሟላት ረገድ ያላቸው ብቃት፣ የምንባቦቹ ተነባቢነትና የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ደረጃ የሚሉት ናቸው:: ስለዚህ በምንባቦቹ ትንታኔ ውስጥ የምንባቦች የቃላት አመራረጥ፣ የዓረፍተ ነገር አስካከ፣ የዓረፍተ ነገርና የቃላት አገባብ፣ የስዋስው አወቃቀር፣ የመለመጃዎች አደረጃጀት ፣ የምንባቦቹ ተከታታይነትና የመሰሰሉት ጉዳዮች ትኩረት ያለተሰጣቸው ነጥቦች ናቸው::

## 1.5 የጸነኑ ጽንሰ-ሐሳቦች ግላጭ ቃላት ማብራሪያ

ይህ ንዑስ ክፍል አሻሚነት የሚታይባቸው ቃላት የሚገለፁበት ሲሆን፣ ቃላቱ ከዚህ ጥናት ውስጥ ከሚይዙትና ከሚያስተላለፉት መልዕክት አንጻር ማብራሪያ የተሰጣቸው ናቸው::

ብቃት- ምንባቦቹ ለተመረጡላቸው የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸውን የይዘት ተመጣጣኝነት፣ ተገቢነትና ተስማሚነት የሚያሳይ ነው::

መርሀ-ትምህርት - ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና፣ ግምገማዎች ተመርጠው፣ ተወስነውና በሥርዓት ተዋቅረው የሚገኙበት መጽሐፍ ነው::

መማሪያ/ ማስተማሪያ መጽሐፍ - በመርሐ-ትምህርት መነሻነትና መሠረትነት ተዘጋጅቶ ተማሪዎች የሚማሩበትና መምህራን የሚያስተምሩበት መጽሐፍ ነው::

ፍላጎት - ተማሪዎች የተመረጠላቸውን የመማሪያ ምንባብ ተቀብለው ለመጠቀም ያላቸውን ዝንባሌና ጉጉት ያመለክታል::

ክሂሎት - አራቱ መሠረታዊ የቋንቋ ችሎታዎች /ማዳመጥ፣ [illegible] መናገር፣ [illegible] / [illegible] ጽንሰ ሐሳብ ወይም ክህሎ[illegible]

**የደረጃ መመጠን** = ለክፍሉ የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች በክፍሉ ለሚገኙት ተማሪዎች የሚስማሙና በችሎታቸው ለክ ወይም መጠን የቀረቡ መሆኑን የሚያመለክት ሐረግ ነው::

**ክንውን** - በመምህሩና በተማሪው መካከል የሚደረግ የመማር ማስተማር ግንኙነት አመለካች እንቅስቃሴ::

**ግምገማ** - ለደረጃ ይመጥናል ተብሎ የተነደፈው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ መድረስ አለመድረሱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ተግባር አመለካች ቃል ነው::

**ተለጣጣቂነት** - ቀደሚው ትምህርት ለሚከተለው ትምህርት መሠረት በመሆን እያደገና እየዳበረ የሚሄድን የይዘት አደረጃጀት ያመለክታል::

**ተከታታይነት** = የመጀመሪያው ምንባብ ከሚቀጥለው ምንባብ ካለተቀራረበ ሁኔታ መከታተለና ተያይዞ መምጣትን ያስረዳል::

**ምንባብ /ምንባቦች** = ለማስተማሪያነት ተመርጠ /ተመርጠው ከ1984 ዓ.ም. ጀምር ማገልገል በጀመረው የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ምንባብ /የሚገኙትን ምንባቦች ያጠቁማል::

**የተነባቢነት ነጥብ** - አንድ ምንባብ በምን ያህል ደረጃ ሊነበብ እንደሚችል ወይም እንደሚገባው ያሰያል::

**የቀመር ውጤት** - የተመረጡ ናሙና ምንባቦችና የቀመሮችን የስሌት ዘዴ በመጠቀም የሚገኘው ውጤት ነው::

<u>የንበብ ቅሌት /ደረጃ/ነጥብ</u> - ምንባቡ የተገመተለትን የክፍለ ደረጃ ወይም ምንባቡ ለመነበብ ያለውን የቅሌት ደረጃ የሚያሳይ ነጥብ ነው::

<u>የምርጫ ጥያቄ</u> - ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች ለመለስ እንዲያስችሉ ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን ብቻ ለመመለስ የሚያገዝ፣ በእውነት /ውሸት/ና አዛምድ መልክ የማይመለሱ አማራጮች ያሉት የጥያቄ ዓይነት ነው::

<u>ተዛምዶ</u> - የሁለት ነገሮች ግንኙነት፣ መስማማትና ተጧጥዋ /ተመሳስሎ/ ወደአንድነት የመምጣት ሁኔታን ያሳያል::

.../

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ለቋንቋ ማስተማሪያነት እንዲያገለግል የሚቀርብ ምንባብ በከፍተኛ ጥንቃቄ መመረጥ እንደሚኖርበት የትምህርት ባለሙያዎች /ናታል 1982/ ይስማሙበታል:: ምንባቡ ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ መምታት ብቃት ያለው መሆን አለበት:: ምንባቡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ታይቶ፣ ተመዝኖና ተተንትኖ፣ ደረጃውና ተከታታይነቱ ተጠኖ፣ ተስማሚነቱና ወቅታዊነቱ ተረጋግጦ ብቃት ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ተመርጦ ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል ይደረጋል /ናታል 1982፣ ጉድማንና ሌሎችን 1966 ያወዳድሯ/::

ስለማስተማሪያ ምንባቦች ምንነት፣ አስፈላጊነትና አመራረጥ የበለጠ ለመረዳት ያመች ዘንድ ስለመርሀ-ትምህርትና ስለማስተማሪያ መጽሐፍ አንዳንድ ገንዘቤ መጨበጥ አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ በታች በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን::

### 2.1 የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ምንነት

መርሀ-ትምህርት የትምህርት እንቅስቃሴ መሪያ ነው:: አንድ አስተማሪ ከተማሪዎቹ ጋር በሚያደርገው የመማር-ማስተማር መስተጋብር የተወሰነውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተዘጋጀ ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት የሚቀርብበት ሰነድ ነው:: እንደኪኒንገወርዝ /1989፣22/ አገላለጽ መርሀ-ትምህርት የትምህርት ይዘቶች ሥርዓታዊ ቅደም ተከተል መግለጫ ነው፤ ሥርዓታዊ ነው የሚባለውም የቋንቋ ትምህርት ዘርፎችን ዝርዝር ብቻ የያዘ መዝገብ ወይም ሰነድ አለመሆኑን ለማሳየት ነው:: መርሀ-ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለመማር-ማስተማሪ ሥራ አመቻችቶና አስማምቶ የሚያቀርብ፤ ይዘቶችን ለመምረጥና ለደረጃው መጥኖ ለማቅረብ የሚረዳ በመሆኑ፣ ጠቃሚነቱና አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም::

የመማር ማስተማር ሂደት /በተለይም የቋንቋ/ ውስብስብ በመሆኑ ደረጃና ምጣኔ ያስፈልጋል:: ለትምህርቱ የተዘጋጀው ይዘት ሁሉ በአንድ ጊዜ የሚቀርብ ሳይሆን ደረጃውና

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምቢነው ተጠብቆ ፣ ቅደም ተከተሉና አወቃቀሩ ተመዝና መቅረብ ይኖርበታል:: ለዚህም መርሀ-ትምህርት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው /ኑናን ፣ 1991/::

ኑናን /1991፣6/ መርሀ-ትምህርት የትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚያሳውቅ፣ የትምህርቱን አወቃቀርም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከሚታወቀው ወደማይታወቀው፣ ከቅርብ ወደሩቅ እያደራጀ የሚያቀርብ፣ መምህሩ ምን እንደሚያስተምርና ተማሪው ምን እንደሚማር በግልጽ የሚያሳይ መዝገብ መሆኑን ያስረዳል::

መርሀ-ትምህርት ከሚሰጠው ትኩረትና ከተግባራዊነቱ አንጻር ሲታይ የሚከተሉትን ዓይቶች ሊሆን ይችላል::

### 2.1.1 ሰዋሰዋዊ መርሀ-ትምህርት

ይህ በጣም የተለመደና ብዙ ጊዜም ሲሰራበት የቆየ የመርሀ-ትምህርት ዓይነት ነው:: ትኩረቱ ለትምህርቱ የቀረበውን ቋንቋ ሰዋሰው /ሥርዓተ-ቃላት፣ አገባብ፣ ቅጽል፣ መስተዋድድ፣ ነጠላና ብዙ.../ በክብደት ቅደም ተከተል/ ከቀላል ወደ ከባድ/ ለተማሪው ማቅረብ ነው:: ይሁን እንጂ ሰዋሰዋዊ ከፍለ ከቋንቋ ውስብስብ ገጽታዎች አንደኛው ዘርፍ ብቻ በመሆኑ ቋንቋን በምሉዕነቱ የማይቀበለ፣ በቋንቋው የመገልገል ችሎታ የሚያዳብር ለትምህርት የሚቀርበውን ሥርዓት ሁሉ በቅደም ተከተለ አዘጋጅቶ ለማቅረብ አያስችልም የሚሉ ሃሳቦች ይሰነዘሩበታል:: በዚህም ምክንያት ጠቀሜታውና አስፈላጊነቱ እየቀነሰ መጧ /ኑናን፣ 1991 ያወዳድሩ/::

### 2.1.2 ሁኔታዊ መርሀ-ትምህርት

ብዙም ያልተሰራበት መርሀ-ትምህርት ሲሆን፣ ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ተጠቃሚዎች ቋንቋውን በምን በምን ዓይነት ሁኔታዎች እንደሚገለገሉበት በመለየት እነዚህን ሁኔታዎች ፈጥሮ ለሁኔታው የሚስማማ ቋንቋን ለማስተማር የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት ነው:: የመርሀ ትምህርቱ ትኩረት የቋንቋውን ትምህርት ከትጠባጥ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ማቅረብ ነው /ኑናን፣1991 ያወዳድሩ/::

ሁኔታዊ መርሀ=ትምህርትም ድክመት አይታጣበትም:: የቋንቋ አገልግሎት በተወሰኑ ጉዳዮች /አካባቢያች/ ላይ ብቻ መወሰን አይገባውም፤ እንዲያውም የቋንቋ አገልግሎት በተፈለገው ጊዜና ቦታ ሁሉ መሆን ይገባዋል:: ከዚህ አንፃር ሲታይ የሁኔታዊ መርሀ=ትምህርት ጠቀሜታ የተገደበ ይሆናል የሚሉ ምሁራን አሉ::

### 2.1.3 ተግባቦታዊ መርሀ=ትምህርት

ዳቪድ ኑናን /1991፤11/ እንደሚሉት ይህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን፤ አቢይ ዓላማው ተማሪው ቋንቋውን የሚማረው ለምን እንደሆነ ማመለከት ነው:: ተማሪው የትኛውን የቋንቋ ክሂል ወይም ዘርፍ መማር ይፈልጋል ወይም መማር አለበት ፤ በሚለው ጠሳብ ላይ ኣያተኩርም፤: ይልቁንም ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያ ነውና በዚህ መሠረታዊ ፅንሰ ጠሳብ ዙሪያ ግለፅ የሆነ ዓላማ ነድፈን ማስተማር አለብን የሚል ጠንካራ አቋም አለው::

የመርሀ=ትምህርት ዓይነቶች ሊበዙ የቻሉት የትኩረት አቅጣጫቸው መለያየት ያስከተለው ተጽዕኖ ነው:: ይህም ማለት አንዱ የመርሀ=ትምህርት ዓይነት በስዋስው ላይ ሲያተኩር ሌላው ደግሞ በተግባቦታዊ ሁኔታ...ላይ ያተኮረ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ግን የትኩረት አቅጣጫቸው ቢለያይም ሁሉም የመርሀ=ትምህርት ዓይነቶች በጋራ መመለስ የሚገቡዋቸው ጥያቄዎች አሉ::

ግሬይ /1990፤ 261/ የመርሀ=ትምህርት ዝግጅት የሦስት ቁልፍ ጥያቄዎችን መልሶች አሟልቶ መያዝ እንዳለበት አመለከተው የጥያቄዎች መልሶች ስለ ትምህርቱ ይዘት፤ ስለተማሪውና ስለመማር-ማስተማር ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆናቸውን ያስረዳሉ:: በሌላ አባባል መርሀ=ትምህርቱ ሲዘጋጅ ስለ ትምህርቱ፤ ስለተማሪውና ስለመማር ሂደት

.../

አመለካች ውጤቶች መኖር አለባቸው:: ምን ዓይነት የቋንቋ ትምህርት ዝርዝሮች በትምህርትነት መቅረብ እንዳለባቸው ፣ ተማሪው ቋንቋውን ምን ሊያደርግበት እንደሚፈልግና የቋንቋ ትምህርቱን ዓላማ አገብ ለማድረስ የሚያገለግሉ የማነቃቂያና የማበረታቻ ተግባሮች በየትኛውም ዓይነት መርሀ=ትምህርት ውስጥ መካተት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች እንደሆኑ አመለከተዋል::

የመርሀ=ትምህርቱ ይዘቶች በቋንቋ፣ በተማሪውና በትምህርቱ ንድፈ=ሐሳባዊ እውነታዎች ላይ መመሥረት አለበት:: ይህም ሁኔታ የትምህርቱን ዝግጅትና አቀራረብ መነሻ በማድረግ የመርሐ=ትምህርት ዓይነቶችን የሚያቀራርብና የሚያመሳስል ይሆናል::

## 2.2 የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ

የማስተማሪያ መጽሐፍች ዝግጅት ጥለቅና በዕውቀት እየዳበረ የሚሄድ ሙያ ነው:: "ሙያ" ነው የተባለውም የማስተማሪያ መጻሕፍች በሚሰጡትና ከሚኖራቸው ጠቀሜታ በመነሳት ነው:: የማስተማሪያ መጽሐፍች የመምህሩ አጋዥ ከመሆናቸውም በላይ ተማሪው በግሉ ጥረቱ ለመማር እንዲችል የሚረዱ መሣሪያዎች ናቸው::

የቋንቋ ባሕርይ በተፈጥሮ ውስብስብ ነው፤ ይህ ውስብስብ ባሕርይ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተደረገለት በስተቀር የሚቀርበውን ቋንቋ ለመማርም ሆነ ለማስተማር አስቸጋሪነቱ አያጠያይቅም::

ኑናን/ 1991፣6/ የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያ መዘጋጀት ያለበት የቋንቋን ውስብስብ ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ምጢኔ ሊኖረው እንደሚገባ "ቋንቋ በጣም ውስብስብና ሁሉንም የክሂል ዘርፎችን በአንድ ጊዜ ማስተማር የማይቻል በመሆኑ፣ ውጤታማ ማስተማር

.../

ዓሪማውን በመገለጽ በእውቀት ደረጃና በትምህርት ቀይታ ላይ የተመሰረተ የማስተማሪያ መማሪያ መምረጥ ይጠይቃል" ሲሉ አስረድተዋል::

ጥቅሱ የቋንቋ ማስተማሪያ ዝግጅት ዓላማን እንደመነሻ በመውሰድ በእውቀት ደረጃና በትምህርት ቀይታ ላይ መመስረት እንዳለበት ያመለክታል::

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የተለያየ ነው:: ለአጥር ጊዜ የሚሰጥ፣ ለተለየ አገልግሎትና ለመሳሰሉት ዓላማዎች የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ አለ::

የቋንቋው ትምህት ዓላማ መለያየት የሚዘጋጀውንም የመማሪያ መጽሐፍ ዓላማ የተለያየ እንዲሆን ያደርገዋል:: ይህም በተራው መምህራን ስለመማሪያ መጽሐፍች ያላቸው አመለካከት ተመሣሣይ እንዳይሆን ያደርገዋል::

ግራንት/ 1989፡7/ እንደሚሉት መምህራን ስለመማሪያ መጽሐፍ ያላቸው አመለካከት በሦስት ይከፈላል:: የመጀመሪያው አመለካከት መምህሩ የራሱን የማስተማሪያ መማሪያ አዘጋጅቶ ቢጠቀም የበለጠ ውጤታማ ሥራ ሊሰራ እንደሚችል ይገፃታል:: ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ይቀርባሉ:: መምህሩ ቋንቋውን የሚያስተምረው ለተለየ ዓላማና ተግባር ሊሆን ይችላል፤ ወይም ለዩ ሥልጠና የሚሰጥ መምህር ይሆንና ለስልጠናው ተስማሚ የማስተማሪያ መማሪያ ለማግኘት የሚቸገረው ሊሆን ይችላል፤ ወይም የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ይሆንና ተስማሚ የማስተማሪያ መማሪያ ለማዘጋጀት ጊዜ ያለው መምህር ሊሆን ይችላል፤ ለለበለዚያ ተማሪዎቹ የተለየ ችሎታ ያላቸው ሆነው መጽሐፉን ለመጠቀም የማያመቸው መምህር ሊሆን ይችላል::

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ የማስተማሪያ መጽሐፍ የግድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስገነዝብ አመለካከት ነው:: መምህራን ምንና እንዴት እንደሚያስተምሩ ስለሚያመለክት ፣ ጠቃሚ ቁምነገሮችን መጥና በገለጸ ስለሚያቀርብ፣ መምህራንን ከጊዜ

ብክነት ስለሚያድንና ተማሪዎችንም በብዙ መለክ ስለሚያግዝ የመማሪያ መጽሐፍ መኖር የግድ ያስፈልጋል የሚሉ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: በነዚህ ነጥቦች ብዙዎቹ መምህራን ይስማሙባቸዋል፤ ይሁን እንጂ ፍጹም የሆነ የማስተማሪያ መጽሐፍ ማግኘት ስለመቻላቸው ጥርጣሬ እንዳላቸው ግራንት /1989 ፣ 8 / ያስገነዝባሉ::

ሦስተኛው አመለካከት መምህራን ስለማስተማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት ያላቸው ግምት ከሁለተኛቹ ጋር የተቀራረበ አመለካከት ነው:: ለሚያቀርቡት ትምህርት ይዘት በመጻፉ ላይ ብቻ አይወሰኑም፣ ወይም የመጽሐፉ ተገዥ አይሆኑም:: እንደዚሁም ከመማሪያ መጽሐፉ ብዙም ርቀው አይሄዱም::

በአጠቃላይ ሲታይ እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የመማሪያ መጽሐፍ መጠቀሙ አማራጥ አይገኝለትም:: ቋንቋውን ለማስተማር በክፍለ ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ብዛት፣ ከኢኮኖሚው ደካማነትና ከተማረ የሰው ኃይል ዕጥረት አንጻር ሲታይ የመማሪያ መጽሐፍ የግድ አስፈላጊ ነው::

2.3 መርሀ=ትምህርትና የማስተማሪያ መጽሐፍ ግንኙነት

አማርኛን ለማስተማር በተለያዩ ጊዜያት ሥርዓተ=ትምህርቶችና የማስተማሪያ መጽሐፍት ሲዘጋጁ እንደቆዩ ይታወቃል:: የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከቋንቋውና ከሕብረተሰቡ ዕድገት በመነጨ ምክንያት በየጊዜው ሲሻሻሉና ሲለወጡ ቢቆዩም፣ በይዘትም ሆነ በዓለማ ብዙም ለዩነት አይታይባቸውም::

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የይዘቶችንና የዓላማዎችን ለዩነትና ዝምድና መመርመር ባለመሆኑ በነዚህ ነጥቦች ላይ አያተኩርም:: ይህ ንዑስ ክፍለ መርሀ=ትምህርትና የማስተማሪያ መጽሐፍ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነትና ተዛምዶ ከተለያዩ ምሁራን

እንፀር የመለከት ዓላማ አለው::

በ1984 ዓ.ም. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ተብሎ የተዘጋጀው መርሀ=ትምህርት አምስት አጠቃላይ ዓላማዎች እንዳሉት ተገልጿል:: እነዚህን አጠቀላይ ዓላማዎች ተገበራዊ ለማድረግ ያስችላሉ በሚል ዓላማ የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍችም በየክፍለ ደረጃው ተዘጋጅተዋል::

የማስተማሪያ መጽሐፍ በተለይም የማስተማሪያ ምንባብ አስፈላጊነቱ የቋንቋ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የሚጠበቅባቸውን ዓላማ /ዓላማዎች/ ከግብ ከመድረሱ ላይ ነው:: ምንባቡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊያገለግል የሚችለው በተዘጋጀው መርሀ=ትምህርት ላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ገብ ሊያስመታ ከቻለ ብቻ ነው::

የማስተማሪያ መጽሐፍ መሠረቱ መርሀ=ትምህርት በመሆኑ በመርሐ-ትምህርቱ ላይ የተገለጹትን ዓላማዎች አሟልቶና ወደተገባር በሚያደርስ መለኩ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል:: " የማስተማሪያ መማሪያዎች ዝግጅት ፕሮጀክት " በሚለው ጽሑፍ ውስጥ የሰፈረው ሐሳብ ይህንን አባባል ያረጋግጣል፡

> ሥርዓተ=ትምህርት ለማዘጋጀት የመጀመሪያው ተግባር ሁሉንም የኘርግራሙን ዓላማዎች መግለጽ ያስፈልጋል የሚል ንድፈ ሐሳብ አለ:: እነዚህ ዓላማዎች ከታለመላቸው ዕቅድ ሊያደርሱዋቸው በሚችሉ ሌሎች ዝርዝር ግቦች ይወከላሉ:: ግቦቹ በተራቸው በሌሎቹ ንዑሳን ዝርዝር ግቦች እየተከፈሉ ይሄዳሉ:: በመጨረሻም ዙር ግቦቹ እንደተለያዩ ክፍሎች ቢዘረዘሩም ስፊ ባሕርያዊ የዓላማዎች ስብስብ የሆነ ግብ ይመሠርታሉ:: ከዚህ በኋላ ለእያንዳንዱ ባሕርያዊ ዓላማ አንድ ወይም ከአንድ

> በላይ የሆነ የመግር ተግባር ይዘጋጃል /ተግባሮች ይዘጋጃሉ/:: እነዚህ ራሳቸው የማስተማሪያ መማሪያ ይሆናሉ::
>
> / ብሪትሽ ኩንሲል ፣ 1980 ፣ 148 /

የማስተማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ከመርሐ-ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖረው እንደሚገባና በመርሀ-ትምህርቱ መገዛት እንዳለበት ይታመናል:: ከኒንገወርዝ /1989፣ 5 / እንደሚሉት የማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሐ-ትምህርቱ ጋር የቀርብ ተዛምዶ ሊኖረው እንደሚገባና የማስተማሩ ዓላማ የማስተማሪያ መጽሐፉኝ ይዘት መወሰን እንደሚኖርበት ያስረዳሉ:: በሌላ አባባል ሁለቱ መማሪያዎች በሚኖራቸው የጠበቀ ግንኙነት የማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት የሚወስነው በመርሀ-ትምህርቱ ዓላማ እንጂ በተቃራኒው የማስተማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን ይዘት መወሰን የለበትም::

እንደኪኒንገወርዝ ሁሉ ግራንትም /1989 / የመማሪያ መጽሐፉ ተቀባይነት ማግኘትና አለማግኘት የሚወስነው ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ባለው ግኙነት መሆኑን ያስረዳሉ::

የማስተማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ መሠረት የሚያደርገው የትምህርቱን ዓላማ ነው:: የማስተማር ዓላማው የሚገለፀው በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በመሆኑ መጽሐፉም የመርሐ-ትምህርቱን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል:: ስለዚህ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎቹን የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን፣ እንደዚሁም የሥነ ልሳንና የሥነጽሑፍ የትምህርት ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል::

የማስተማሪያ ምንባቦች ሲዘጋጁ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: ሁለቱ የቋንቋውን ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ አጅና ጓንት ሆነው ማገልገል እንዳለባቸው ይታመናል:: መርሀ-ትምህርት የመማሪያ መጽሐፍ ምንጭ በመሆኑ የሁለቱ ተዛምዶ [illegible] ጥብቅ ነው፡፡ ዱብሪናና አለሽተን /1990፣29/ ፣

…/

ይህን የሚያረጋግጡት ወርሀ ትምህርቱና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ካላቸው ተስማሚነት አንፃር ነው:: የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ ቴክኒኮችና አቀራረቦች በሙሉ በወርሀ=ትምህርቱ ውስጥ ከተገለጹት ዘዴዎች፣ ቴክኒኮችና አቀራረቦች ጋር ስምም ሆነው መቅረብ አለባቸው::

ሪቻርድስ /1987፣21=22 / የወርሀ-ትምህርትንና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ዝምድና እንደሚከተለው ይገልጻሉ፣

> ለመማር=ማስተማር ሂደት የመጀመሪያው የወርሀ=ትምህርት ዝግጅት ነው:: ሌላው ቅንጅት በማስተማሪያ መሣሪያዎች አማካይነት የወርሀ=ትምህርቱ ዓላማዎች በመምህራንና በተማሪዎች መጠቀምን ያመለክታል:: ስለዚህ ዝግጅቱ ተማሪዎቹ ይማሩበታል ተብሎ የሚገመተውን ይዘትና መምህራን ያስተምሩበታል ተብሎ የሚገመተውን ስልት፣ እንደዚሁም በወርሀ=ትምህርቱ መሰፈርትነት የተዘጋጁትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች እንዴት ሊጠቀሙባቸው እንደሚገባቸው ያሳያል::

ይህ ጥቅስ የሚያሳየው ለማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት መሠረት የሚሆነው ወርሀ-ትምህርት መሆኑን ነው:: በወርሀ ትምህርቱ ላይ በመመርኮዝ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ያዘጋጃሉ:: መምህራንና ተማሪዎችም በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚገለገሉት እነዚህኑ መሣሪያዎች ይሆናሉ::

የማስተማሪያ መጽሐፍ በወርሐ=ትምህርት ላይ ካልተመሰረተ ቋንቋን ማስተማር አስቸጋሪ ነው:: ወርሀ=ትምህርት ምን ማስተማር እንደሚያስፈልግ ፣ እንዴት ማስተማር እንደሚቻልና እንዴት መገምገም እንደሚናርብን መረጃ ስለሚሰጠን የቋንቋ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: የወርሀ ትምህርቱ ይዘቶች በመማሪያ

.../

መጽሐፍ ውስጥ ካልተመለከቱ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ያጧል፣ አለበለዚያም ገለጸነት የጐደለው ይሆናል::

የማስተማሪያ መማሪያዎች በመርሐ-ትምህርቱ ላይ የተነደፉትን ዓላማዎች መሠረት አድርገው የተመረጡትን ይዘቶች ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: መርሐ-ትምህርቱ አጠቃላይም ሆኑ ዝርዝር ዓላማዎች የታለመላቸውን ግብ መምታታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል:: ይህም በሪቻርድስ /1987 ፤ 25 / አባባል እንደሚከተለው ተገልጿል፣

> መርሀ-ትምህርት በሌለበት እንኳን ቢሆን የማስተማሪያ መማሪያዎች የትምህርቱን ይዘት ይገልጻሉ። በተጨማሪም የመርሀ-ትምህርቱ ነጥቦች ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ እንደሆኑ፣ ለያንዳንዱ ነጥብ የተሰጠውን ትኩረትና ዝርዝር ገለጻ ያሳያሉ ወይም ያብራራሉ:: በመጨረሻም የማስተማሪያ መማሪያዎቹ የየተናጠል ዓላማዎች ተሰብስበው የመርሀ-ትምህርቱ ግቦች የሚሆኑትን የዕለት ተዕለት ትምህርታዊ ዓላማዎች ያብራራሉ::

በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በአጠቃላይነት የሰፈረት የትምህርት ዓላማዎች በማስተማሪያ መማሪያዎች አማካኝነት ይዘረዘራሉ ፤ ለመምህሩና ለተማሪው ቀርበው ተግባራዊ ይሆናሉ:: በሌላ አነጋገር ሁለቱ በተናጠል ሆነው የመማር-ማስተማርን ዓላማ ውጤታማ ለማድረግ አስቸጋሪ ስለሚሆን አንዱ የሌላው ምንጭ በመሆን መዘጋጀት እንዳለባቸውና ሁለቱ መደጋገፍ እንደሚኖርባቸው መረዳት ይቻላል::

የመማሪያ መጽሐፍና የመርሀ-ትምህርቱ ግንኙነት ይዘቶችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የይዘቶቹን አወቃቀር፣ የቴክኒክንና የአቀራረብ ስልትን ጭምር መሆን አለበት:: ይህም በመርሀ-ትምህርት መሠረትነት / ያለ ቀጥተኛ ግንኙነት / ያልተዘጋጀ የመማሪያ መጽሐፍ ዋጋ ቢስ መሆኑን ያሳያል:: የማስተማሪያ መጽሐፉ [illegible]

. . . /

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ግንኙነት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት ይኖርበታል / ከዱቢንና አለሸቱ ፤ 1990 ጋር ያወዳድሯ/::

ከመርሀ-ትምህርቱና ከማስተማሪያ መጽሐፎች ግንኙነት ሌላ ለክፍሉ በተዘጋጀው መርሀ-ትምህርት አማካይነት ለደረጃው የሚመጥን ዕውቀት ለማስተላለፍ የማስተማሪያ መማሪያዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል:: ከደረጃው የሚጠበቀው የዕውቀት ደረጃ በመርሀ-ትምህርቱ ዓላማ መሠረትነት የሚቀርብ በመሆኑ መማሪያዎቹ እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መሆን ይገባቸዋል::

ለመማሪያ መጽሐፉ መሠረት መርሀ-ትምህርት የመሆኑን ያህል መርሀ-ትምህርትም የሚዘጋጀው የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ተመስርቶ በመሆኑ የተማሪውን ችሎታና ፍላጎት ያመለክታል:: የተማሪው ችሎታና ፍላጎት በመርሀ-ትምህርቱ ላይ መንፀባረቁ ለመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት በቂ መረጃ ለማግኘት ይረዳል::

የመማርያ መጽሐፉ የመምህራንና የተማሪዎች የዘወትር መሣሪያ በመሆኑ የመርሀ ትምህርቱን ይዘቶች የግድ ማካተት እንዳለበት ይታመናል:: የማስተማሪያ መጽሐፍና መርሀ-ትምህርቱ አገልግሎትና አስፈላጊነት የተለያየ ቢሆንም ለቋንቋ ትምህርት የሁለቱም ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ አይደለም::

2.4 የምንባብ አመራረጥ ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለትምህርቱ መጕልበት የተማሪውን ፍላጎት መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: ለዊስና ሃለ /1990፤12/ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ፍላጎት ከመምህሩ ዝግጅት ጋር ካልተጣጣመና ችግር ከተፈጠረ ችግሩን የሚቃለየው መንገድ ለተማሪዎቹ ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት መሆኑን ያስረዳሉ:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት በንቃት ቢሳተፉ ውጤታማና ደስተኞች እንደሚሆኑ ያስገነዝባሉ:: በነዚህ ምሁራን አምነት የማስተማሩ ሥራ የተማሪዎቹን ፍላጎት የሚያሟላ ይዘት ሊኖረው ይገባል:: ተማሪዎቹ ያልተሳተፉበት የምንባብ አመራረጥ የመማር ሂደቱን ውጤታማነት አጠራጣሪ ያደርገዋል::

በለ /1976፣/ ጉድማንና ሌሎች /1966/፣ ናታል /1982/ እና ኒጅ /1987/ ፣ የማስተማሪያ ምንባብ ሲመረጥ ብዙዎቹን ተማሪዎች የሚስብ መሆን አለበት፣ ይህ ማለት ግን ጥቂት ተማሪዎችንም ቢሆን የሚያስለች መሆን አለበት ማለት አይደለም:: ምንባቡ ሲመረጥ ብዙዎቹ ተማሪዎች የሚደሰቱበት፣ ጥቂቶቹም ቢሆኑ የማይሰለቹት ሆኖ በተማሪዎቹ ሙሉ ተሳትፍና ፍላጎት አንፃር መመረጥ እንዳለበት አበክረው ያስረዳሉ::

ሐርከርና /1977-78/ ፣ ሃጅ /1987/ የምንባብ መምረጫ መሥፈርቶች ብዙ ቢሆኑም የተማሪዎቹ ዱሬና /ምን ያህል እንደሚያውቁና እንደማያውቁ በመመርመር/ ግፊት ሊተከርባቸው የሚገቡ ነጥቦች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ::

የማስተማሪያ ምንባብ ለመምረጥ ፍላጎት ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: ዊሊያምስ/1986፣42/ ይህንኑ ሐሳብ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፣

> በምንባብ ላይ ፍላጎት ከሌለ ሊደረግ የሚችለው በጣም ጥቂት ነው::ይህ መሠሪያ ግለጽ መሆን ሲገባው ሁልጊዜ እንደተረሳ ነው:: የመማርን ግፊት ስለሚጨምር ፍላጎት በጣም አስፈላጊ ነው:: የግፊት መኖር ደግሞ በተራው ጥሩ የመማር-ማስተማር ሂደት እንዲኖር ያግዛል::.....ዋናውና የመጀመሪያው ለተማሪው ቢሆንም መምህሩንም የሚያስደስት መሆን አለበት::....

ጥቅሱ እንደሚያስረዳው የተማሪዎች ፍላጎት ከግምት ውስጥ ሳይገባ የተመረጠ ምንባብ ብዙም አይጠቅምም፣ ያለተማሪው ፍላጎት በተመረጠ ምንባብ ሊሠራ የሚችለው ተግባር በጣም ውሱን ነው:: በተማሪው ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተመረጠ ምንባብ ለተማሪው የትምህርት አቀባበል ከፍተኛ ግፊት ይሰጣል:: የግፊት መኖር ደግሞ ጥሩ የመማር-ማስተማር ሂደት ይከናወናል ማለትን ያመለክታል:: ስለዚህ ምንባብ ሲመረጥ በቅድሚያ የተማሪዎች ፍላጎት ሊጤን ቢገባም

መምህሩንም የሚያስደስት ቢሆን ውጤቱ የበለጠ ያማረ ይሆናል::

ካሬለም /1984፣339/ ፍላጎት ለምንባብ መምረጫ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን ያስረዳሉ:: ምንባብ የሚመርጥ ባለሙያ እንደመስፈርት መገለገል ያለበት ተማሪው የሚደሰትበትን ሲሆን ከተቻለ በራሱ በተማሪው ተሳትፍ የተመረጠውን ጽሁፍ ማካተት አለበት::

በማስተማሪያ ምንባብ አመራረጥ ላይ የተማሪው ፍላጎት መኖር የመማር-ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ሊያደርጉ ከሚችሉ መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው:: ፍላጎትን አስመልክተው ናታል /1982፣30/ መምህሩ ምንባብ ሲመርጥ የተማሪውን ፍላጎት መያዝ እንዲችል የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ያስረዳሉ፣

1. ምንባቡ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል የማያውቁትን ያሳውቃቸዋል ?

2. ከአዳዲስ ሐሳቦች ጋር ያስተዋውቃቸዋል ?

3. ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡ ወይም ምን እንደሚሰማቸው ለመረዳት ያግዛቸዋል ?

4. ተማሪዎቹ በራሳቸው ፍላጎት እንዲያነቡ ይገፋፋቸዋል ?

ይህም የተማሪዎቹን ፍላጎት ለማነሳሳት በቁጥራቸው አነስተኛ በይዘታቸው ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ መረጃዎች በምንባቡ ውስጥ መኖር እንዳለባቸው ያስረዳል:: ተማሪዎቹ የሚሰሟቸውን አዳዲስ ሐሳቦች ከምንባቡ ውስጥ ባገኙ ቁጥር የማንበብ ፍላጎት ያድርባቸዋል:: ሆኖም ግን በርካታና ያልተብራሩ ሐሳቦች ካሉ ጽሑፉን ከባድ ስለሚያደርገው የተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎት ይቀንሳል:: በአንጻሩም በጣም አነስተኛና ግልጽ የሆኑ መረጃዎች በምንባብ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ጽሑፉን አሰልቺ ያደርገዋልና የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት ይገድበዋል:: ከዚህ ሌላ ምንባቦቹ ስለሌሎች ሰዎች ባሕርይ፣ ሁኔታና አስተሳሰብ ለተማሪዎቹ የሚያስተዋውቁና የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት በማነሳሳት ራሳቸው ተገፋፍተው እንዲያነቡ የሚረዱ መሆን አለባቸው:: ስለዚህ በምንባቡ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ይዘት

ተስተውሎ የተመረጠ፣ ከተማሪያቹ ፍላጎት፣ ለምድና ዕድሜ ጋር ተጣጥሞና ተመጣጥኖ የሚቀርብ መሆን አለበት::

የማስተማሪያ ምንባቦች በደረጃው ለሚገኙት ተማሪዎች ተስማሚ ይዘት ሊኖራቸው ይገባል:: ተማሪዎቹ ራሳቸውን የቻሉ ፀጤታማ አንባቢያች መሆን የሚችሉት በቋንቋ ይዘትን እንዴት ማስተላለፍ እንደሚቻልና በቋንቋ የተላለፈውን ይዘት ከቋንቋው ውስጥ ለማውጣት የሚያስችሉ ክሂሎችን ሲያዳብሩ ነው:: ስለዚህ ምንባቦች መመረጥ ያለባቸው እነዚህን ክሂሎች ለማዳበር ከማገዝ አኳያ እንጂ በቋንቋው ወይም በይዘቱ ላይ ብቻ በማተኮር መሆን የለበትም /ናታል 1982፣ 31 ያወዳድሯ/::

ለማስተማሪያነት የሚመረጥ ምንባብ ተማሪዎቹን አየሰበ ወይም አያጉጉ ያለመሰላቸት ከዳር እስከዳር የሚያነቡት መሆን ይገባዋል:: ከሚያውቁት ነገር ወይም ከሚኖራቸው ለምድ ጋር ተቀራርቦና ከደረጃቸው ጋር ተመጣጥኖ የቀረበ ጽሁፍ የይዘት ተስማሚነት አለው ሊባል ይችላል:: ኑናን /1988፣ 44-45/፣ ተማሪዎች ከምንባቦች የሚፈልጉቸውን አራት ነጥቦች ሲያመለክቱ፣ የቃላቱ 90% ተማሪዎች አንብበው የሚረዷቸው፣ የቃላት አገባብና የዓረፍተ ነገሮች አወቃቀር የተለመደ፣ የሚተላለፈው መልእክት ግልፅና ፍችያቸው ቀላል ሆኖ መገኘት እንዳለበት ያስረዳሉ::

ይህም የምንባቦቹ የክብደት ደረጃ ተማሪዎቹን ተስፋ የማያስቆርጥ ፍፁም የማያውቁት ይዘት የማያቀርብ መሆን እንዳለበት ያሳያል:: ናታልም /1982፣ 31/ ይህንኑ ሲያጠናክሩ፣ የሚመረጡት ምንባቦች የትምህርቱን ሂደት ስኬታማነት ከተማሪዎቹ ፍላጐት፣ ለምድና ችሎታ አንፃር የሚያመቻቹና በሚያስፈልጉበት ጊዜም ተማሪዎቹ እንደ ችሎታቸው ሊጠቀሙባቸው የማያስቸግሩ መሆን እንዳለባቸው ይገልጻሉ::

ጢርትሌ / 1978፣ 101/ "የማስተማሪያ መጽሀፍ በጥቅም ላይ ሊውል እንዲችል በተቻለ መጠን ትክክለኛ፣ የማያሻማ፣ ወቅታዊና ዓላማውን የሚያሟላ ይዘት ሊኖረው ይገባል." ሲሉ የይዘቱ ተስማሚነትና ዓላማውን ማሟላት

.../

አብቃት ተፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ያስረዳሉ:: የማስተማሪያ መጽሀፉን ይዘት ተስማሚነት ለመጠበቅ አስቸጋሪ የሚሆኑ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ:: በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉና በአንድ ክፍለ ውስጥ የተለያየ ዳራ ያላቸው ተማሪዎች በሚገኙባቸው አገሮች ችግሩ የባሰ መሆኑ አያጠያይቅም:: በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የማስተማሪያ ምንባብ ለመምረጥ የሚያጋጥመው ችግር የከፋ እንደሚሆን ይታመናል፣ ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን ለተማሪዎቹ ብጤረሰብና ዕድሜ ተስማሚ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሊመረጡ ይገባል::

የማስተማሪያ መጽሀፍ መኖር ለቋንቋ ትምህርት መነሻ ይሆናልና ጠቀሜታው በጣም ከፍተኛ ነው:: ይሁን እንጂ የመጽሀፉ መኖር ብቻ የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ውጤት አያስገኝም:: መጽሀፉ የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የግድ የተማሪውን ስሜት ወይም ፍላጐት የሚስብ መሆን አለበት:: ስለበለዚያ የመጽሀፉ መኖር ብቻ ጠቀሜታውን ስለማያመለክት የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የማያስችል ከሆነ የመጽሀፉ መኖር ዋጋ ቢስ ነው /ከብረሞሬኛ 1980፣ 7 ጋር ያወዳዱሩ/

የማስተማሪያ ምንባብ ብቃት አለው ሊባል የሚችለው የተማሪዎቹን ፍላጎት ማሟላት ሲችል ነው:: ብዙ ምሁራን የተማሪውን ፍላጎት የማያሟላ የማስተማሪያ መሣሪያ በመማር-ማስተማሩ ክንዋኔ ውስጥ ቦታ ሊሰጠው እንደማይገባ ያስረዳሉ:: የመማሪያ ምንባብ ለመምረጥ የመጀመሪያው መስፈርት የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት መቻል አለመቻሉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ጨርመር /1983፣ 237/ ምንባብ ለመምረጥ ከመቀከር በፊት ስለተማሪዎቹና ስለ ፍላጎታቸው ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ:: ጨርትሊም / 1978፣ 103 / እንደሌሎቹ ምሁራን ሁሉ ጥሩ የማስተማሪያ ምንባብ ለመምረጥ የአንባቢውን የንባብ ችሎታ ማወቁ ብቻ ተገቢ እንዳልሆነና ከተቻለ የተማሪውን ዳራ ማወቁ እንደሚጠቅም ይገልጻሉ:: ይህም ተማሪው ስለሚቀርብለት ርዕሰ-ጉዳይ መጠነኛ ዕውቀት ካለው፣ጽሁፉ የበለጠ እንደሚነበብለትና እንደሚቀበለው ከማመለከቱም በላይ በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ጽናት እንዲኖረው ይረዳዋል:: ከዚህም በመነሳት ስለተማሪዎቹና

ስለፍላጎታቸው ግወቅ ለማስተግሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት የሚኖረው አስተዋጽኦ አጅግ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

ጡራስን / 1980፣ 46 / ለተማሪዎች ፍላጐት የሚሰጠው ግምት ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ያምናሉ:: ምክንያቱም ተማሪዎቹ ፍላጐታቸው ሲሟላላቸው ትምህርቱን ለመከታተል ጥረት ያደርጋሉ:: በትምህርታቸው ደካማ የሆኑ ተማሪዎች እንኳን የሚያስደስታቸውን ጽሁፍ ሲያገኙ ለማንበብ ከመጓጓት አልፈው ጽሁፉን ይጠቀሙበታል፤ ይህም ለትምህርቱ እንዲነቁ ያደርጋቸዋል::

የተማሪዎቹ ፍላጐት እንደመስፈርት የሚያገለግለው ምንባቦችን ለመምረጥ ብቻ አይደለም:: ጽሁፍን አሻሽሎ ለመግር ግስተግር ሂደት እንዲስማማ አድርጐ ለማቅረብም ቁልፍ ሚና ይጫወታል:: ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ፍላጐት በሚስማሙበት ሁኔታ ካለተሻሻሉ በስተቀር የትምህርቱን ሂደት ያደናቅፋሉ:: አንድን ጽሁፍ ለማስተማሪያነት ተስማሚ እንዲሆን ለማሻሻል የመጀመሪያው ውሳኔ ስለ ተማሪዎቹ ዳራ በገለጸ ግወቅ አስፈላጊ ነው:: /ስቴቪክ 1965፣ 116 /:: በመሆኑም ማንኛውም ምንባብ የተማሪዎቹን ፍላጐትና ዝንባሌ የማያሟላ ከሆነ ለማስተማሪያነት ሊረዳ ስለማይችል ለማስተማሪያነት መቅረቡ ለይስጡለ ያህል ብቻ ይሆናል::

## 2.5 የምንባቦች ተነባቢነት

የተነባቢነት ጽንሰ ሀሳብ በብዙ ምሁራን ለብዙ ጊዜያት ሲገለፅ ቆይቷል:: ለምሳሌ ጉድማን / 1973፣ 472 / ተነባቢነት በማስተማሪያ መልክ ታትመው የቀረቡ ጽሁፎች የተዘጋጁላቸውን ሰዎች የማስደስትና ከመረዳት ችሎታቸው ጋር ላላቸው ግንኙነት መለኪያ እንደሆነ ይገልጻሉ:: ይህም ጽሁፉ ተነባቢነት አለው የሚባለው እንዲያነቡት ለሚፈለጉት ግለሰቦች /ቡድኖች/ ያለምንም ችግር የሚነበብ ሆኖ የመገኘትን ሀሳብ ያንፀባርቃል:: በቀላሉ ከመነበቡም በተጨማሪ አንባቢውን ለመሳብ የሚችል ሆኖ መገኘትንም ያመለክታል:: በሌላ አባባል ጽሁፉ አንባቢውን የመሳብ ኃይል ሊኖረው ይገባል::

ለድረዩር / 1984፣ 334 / ፣ ተነባቢነት በቀላሉ የሚነበብ ጽሁፍ፣ አንባቢውን የማስደሰት ኃይል ያለው፣ አንብቦ ለመረዳት ቀላል የሆነ ወይም እነዚህን ሁሉ በአንድነት የሚያሟላ ጽሁፍ መሆኑን የሚያመለክት ጽንሰ ሀሳብ ነው:: በሌላ አነጋገር ተነባቢነት የአንድን ጽሁፍ ወይም ይዘት በቀላሉ መነበብንና ለመረዳት አለመክበድን ወይም ይዘቱ የተዘጋጀላቸውን ሰዎች የመሳብ ኃይልና የመማረክ ፕሬት ያለው መሆኑን ያመለክታል::

ጢራስንዎ /1980፣ 14/ ተነባቢነትን የሚገልፁት መጽሀፉ አንባቢውን እንደሚስበው፣ እንደሚያስደስተውና በቀላሉ እንደሚረዳው መወሰን የሚችል የመጽሀፉ ጉዳዮች ስብስብ መሆኑን ይገልጻሉ::

ዳይ /1994፣ 21-22/ በምንባብ አመራረጥ ጊዜ ተነባቢነት ከፍላጐትና ከጠቀሜታ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው መሰፈርት መሆኑን ካመለከቱ በኋላ ከረለን በመጥቀስ የሚከተሉት ስድስት ነጥቦች የተነባቢነት አካል መሆናቸውን ያቀርባሉ፣

1. <u>የቃላት ዕውቀት</u>:- የቃላት ዕውቀት የምንባብን ክብደትና ቀለት የሚወስኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ነው:: በጽሁፉ ውስጥ ከባድ ቃላት በበዙ ቁጥር የተማሪዎቹ ምንባቡን አንብቦ የመረዳት አቅም የተዳከመ ይሆናል:: ስለዚህ የቃላት ዕውቀት ለምንባብ መረጣ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ዋናና አንገብጋቢ ነጥብ መሆኑ መረሳት የሌለበት ነጥብ ነው::

ዳይ በማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባብ ውስጥ የከባድ ቃላት መብዛት የምንባቡን ተነባቢነት ስለሚጎዳ በምረጣ ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ ቢያመለክቱም ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ አዳዲስ ቃላት መኖር እንዳለባቸው ያምናሉ:: በመሆኑም በአንድ ገጽ ላይ ከአንድና ከሁለት ያልበለጡ አዳዲስ ቃላት መኖር እንዲኖሩባቸው ይመከራሉ::

. . . /

2. ዳራዊ ዕውቀት:- የተማሪው ዳራ /የዓለም ዕውቀት/ ከቃላት ዕውቀት ባላነሰ ሁኔታ ለምንባብ ተነባቢነት አስፈላጊ ነው:: አንባቢያቱ ስለአንድ ስለተለየ ርዕስ መጠነኛ ዕውቀት ካላቸው በትክክልና በፍጥነት ማንበብ ይችላሉ::

3. የአገባብ ተስማሚነት:- የሰዋሰዋዊ አገባብ ከተማሪያቱ ለምድና ችሎታ በላይ መሆን የምንባብን ተነባቢነት ሊቀንሰው ይችላል:: ተማሪያቱ የማያውቁትና አዲስ አይነት አገባብ ያለበት ምንባብ ገሬ ሊያጋባቸው ይችላል፤ አንብበው መረዳትም ይቸገራቸዋል:: በመሆኑም የአንድን ጽሁፍ ተነባቢነት ከሚያጎድሉና ጽሁፉን ከባድ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል የአገባብ ተስማሚነት አንዱ ጉዳይ በመሆኑ በምንባብ መረጣ ጊዜ ሊጤን ይገባዋል::

4. ቅንጅት:- ምንባቡ የተቀናጀበትን ስልትና ሁኔታ ማወቅ አንብቦ ለመረዳት ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋል፤ የጽሁፉንም ተነባቢነት ያረጋግጣል::

5. ተግባቦታዊ ሁኔታ:- የተግባቦታዊ ሁኔታ መሠረቱ በቋንቋው የመገልገልን ወይም የመጠቀምን ችሎታ የሚመለከት ነው:: ማክርቲም /1991፣ 5/ የተግባቦታዊ ሁኔታን ምንነት ሲገልፁ የሚከተለውን ብለዋል፣

> የተግባቦት ትንተና መሠረታዊ ጠቀሜታ ቋንቋው ና ቋንቋው የሚያገለግለበት አውድ ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት ነው:: ... የተግባቦት ትንታኙ ማንኛውንም ዓይነት ጽሁፍና መረጃ ከተራ መግባባት እስከ ከፍተኛ የመግባባት ቅርፅ ድረስ ያሉትን የቋንቋ አገልግሎቶች ያጠናል::

./

ይህም ቋንቋው ምን እንደሆነ፣ እንዴት፣ በምን ዓይነት ሁኔታና ጊዜ ሊያገለግል እንደሚችል ይጠናበታል፤ የቋንቋው የአገልግሎት ሁኔታም ይመረመርበታል:: ስለዚህ ተግባቦታዊ ሁኔታ በሚቀርበው ምንባብ ላይ ሊታይ የሚችለውን የተነባቢነት ጥንካሬና ድክመት ማመልከት ከሚችሉት ውስጥ ሊካተት የሚገባ ነጥብ ነው::

ዳይ፣ የጽሁፉ ርዕስ፣ና በጽሁፉ ውስጥ የሚሰጡት አስተያየቶች ቅደም ተከተላቸው፣ሕብረተሰቡ በለመደውና በሚገለገለበት ሥርዓት ተከታትለውና ተያይዘው መግባባትን በማያፋልስ ሁኔታ ሙኒሪዝ አንዳለባቸው ሲገልፁ፣ "በንግግር ደረጃ ያለ አወድ በምንባቡ ውስጥ ያሉት ርዕሶችና አስተያየቶች መከታተላቸውንና መያያዛቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባል::" /1994፣ 22/ በማለት ያስረዳሉ::

ተግባቦታዊ ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ ነው:: የቋንቋ አስፈላጊነቱ ለመግባባት እስከሆነ ድረስ ለዚህ ሊረዱ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ የተግባቦት ሁኔታ ነው:: ለዚህም ነው ማከርቲ /1991፣ 170–171/ "... የተግባቦት ትንተና አስፈላጊነት ተግባራዊ ማይንስን በቅርበት ለመርመር ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ የሚሆኑ መማሪያዎችንና የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎችንም ለማጥናት ይረዳል ...." በማለት ተግባቦታዊ ትንታኔ በመማር–ማስተማር ሂደት ውስጥ ለማስተማሪያ መማሪያዎች ዝግጅትና ለክፍል ውስጥ ክንዋኔዎች አስፈላጊነት እንዳላቸው የሚያስረዱት::

ዊደውሰንም /1985፣ 75/ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተግባቦታዊ ሁኔታ መናር የሚያስፈልግ መሆኑን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤ "... ቋንቋ ማስተማር ንድፈ–ጠሳባዊና ተግባራዊ ክንውን መሆኑን መረዳት ተገቢ ይመስለኛል፤ ውጤታማ የቋንቋ ማስተማሪያ መማሪያና የክፍል ውስጥ ሥርዓት ቋንቋ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚሠራ መረዳትን በሚያመለክቱ መመሪያዎች ላይ ይመሠረታል ... "::

ስለዚህ የአንድን የቋንቋ ማስተማሪያ መማሪያ ለማዘጋጀት የቋንቋው አገልግሎት ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት መረዳት ይቻላል:: በዚያውም የክፍል ውስጥ ተግባርን ከተግባቦታዊ ሁኔታዎች ጋር ማያያዝ ያስፈልጋል:: ይህ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ማለት ደግሞ የማስተማሪያ ምንባቡን ተነባቢነት ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ በመማሪያው ዝግጅት ጊዜ መረሳት እንደሌለበት ያመለክታል::

6. <u>የምንባቡ ርዝመት</u>:- ዳይ ከሚያነሱዋቸው ተነባቢነትን ከሚያመለክቱ ነጥቦች መካከል የምንባቡ ርዝመት የመጨረሻው ነው:: ለተማሪዎቹ የተመጠነ ምንባብ ያለማቅረብ ትምህርቱን ውጤት አልባ ሊያደርገው ይችላል:: በዳይ አበባል /1994፣ 22/ ተማሪዎቹ በተወሰነ ጊዜ እንዲያነቡት የቀረበላቸውን ምንባብ ( ጊዜው እንበበው መጨረስ ካልቻሉ ትምህርቱ ዉጤታማ አይሆንም:: ምንባቡን እንዲያነቡት የታሰቡት ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን እንደደከማ አንባቢ በመቁጠር ተስፋ ይቆርጧሉ::

ስለሆነም ምንባቡ ተነባቢነት እንዲኖረው ከተፈለገ ርዝመቱ ከተማሪዎቹ የማንበብ ችሎታና ፍጥነት ጋር ተመጣጣኝና ተቀራራቢ መሆን አለበት:: በዳይ እምነት የአንድን ምንባብ ተነባቢነት ሊያጉድሉ የሚችሉ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ስድስት ነጥቦች የማስተማሪያ ምንባብ ሲመረጥ ትኩረት ሊሰጧቸው ይገባል::

### 2.5.1 የተነባቢነት <u>ቀመሮች</u>

የተነባቢነት ፅንሰ—ሐሳብ ከባድና ቀላል የማስተማሪያ ፅሁፍ ለመለየት ማገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በርካታ ለውጦችና ዕድገት አሳይቷል:: ይህም እንፃራዊ ብቃት ያላቸውን፣ከባድ ፅሁፍን ከቀላል ፅሁፍ ለመለየት የሚያስችሉ፣ዘመናዊ የተነባቢነት ቀመሮችን ለመፍጠር አስችሏል /ድሬዩር 1984፣ 334/::

በድሬዩር አመለካከት /1984/፣ የተነባቢነት ቀመሮች ስለአንድ ፅሁፍ ክብደት ወይም ቅለት አጠቃላይ ግምት ለመስጠት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ናቸው:: መምህራንም ሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች ተማሪዎቻቸው እንዲያነቡዋቸው የሚፈልጓቸውን ፅሁፎች ክብደት መመዘን ይኖርባቸዋል::

ጠርከር /1977–78/፣ የተነባቢነት ቀመሮች የማስተማሪያ መማሪያዎችን ለመምረጥ የመጀመሪያ መሰፈርቶች መሆናቸውን ካመለከቱ በኋላ ክሌርን በመጥቀስ ከሠላሳ በላይ የተነባቢነት ቀመሮች መኖራቸውንና ከዚያ ወዲህ ቢያንስ ሁለት ቀመሮች /የፍሪገሬፍ 1968፣ የስምግ 1969/ መዉመራቸውን ያትታሉ:: እነዚህ ቀመሮች ተነባቢነትን ለመገመት ፈጪን መለኪያዎች ቢሆኑም አንዳንድ ጉድለቶች እንዳሉዋቸውም አመልከተዋል::

በኔለስንም /1978፣ 621–622/ አምነት፣ የተነባቢነት ቀመሮች ጉድለት አለባቸው:: ቀመሮቹ የጠሳብን ረቂቅነትና ውስብስብነት፣ የቋንቋ ቅርፅና ቅንጅት ያላቸውን አንድነትና ልዩነት የማይለኩ ናቸው:: ከዚህም ሌላ ብዙ ምሁራን የሚቀበሉትንና አስፈላጊነቱን የሚያምኑበትን ፍላጎቱን፣ የመነቃቃት ደረጃንና የቋንቋ ችሎታን ወይም አንድ አንባቢ ያለውን ለምድ ለመለካት ብቃት የላቸውም::

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ድክመቶች ቢኖሩባቸውም: ቀመሮቹ በማዕከላዊ ደረጃ መለኪያነታቸው አስተዋጽኦ ስላለው የሚከተሉትን አምስት ማሳሰቢያዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት መጠቀም ይቻላል /ኔለስን 1978፣ 624–625/፤

1. ለተማሪዎች ሊጠቅም የሚችለውን ጽሁፋዊ መማሪያ ለመገምገም ቀላሉን የተነባቢነት ቀመር እንደድጋፍ መማሪያ ለመጠቀም ተማር፣

2. በሚቻለው ሁኔታ ሁሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ዕውነታዎችን፣ ጠሳቦችንና የትምህርቱን ዋጋ የያዙ ጽሁፋዊ መማሪያዎችን በተለያዩ የተነባቢነት ደረጃዎች ከተማሪዎችህ ችሎታ አንፃር አዘጋጅ፣

3. የመማሪያው የተነባቢነት ደረጃና የተማሪዎቹ የንባብ ችሎታ ቅፅበታዊ የመረዳት ውጤት ያስገኛል ብለህ አትገምት::

ከተነባቢነት ቀመሮች ውጭ የሚነበብ ክብደትን የሚጉዱ ሌሎች ምክንያቶች መኖራቸውን አስታውሰ፣

4. እንደተነባቢነቱ መስፈርት ጽሁፋዊ መማሪያውን ማሻሻሉ ቅጽበታዊ ቅለት ያስከትላል ብለህ አትገምት:: ጽሁፋዊ መማሪያውን እንደገና አሻሽሉ ለማዘጋጀትን፣ ለመተንተንና ብቃቱን ለመቆጣጠር ጊዜ ላላቸው ለምን ለሰን ሰዎች፣ ለተመራማሪዎችና ለአቀናባሪዎች ተወው፣

5. የተነባቢነት ቀመር መጠቀም ማስተማርን እንደማይተካ ተረዳ፤ ይህንንም መተገበር ማስተማር አይደለም:: የትምህርት መስጫ መጽሀፍት በገለ ለመነበብ የተዘጋጁ አይደሉም:: ....

እነዚህ አምስት ነጥቦች ቀመሮቹ ፍፁም የሆነ መለኪያነት እንደሌላቸው ያመለክታሉ:: ቀመሮቹ ሊያገለግሉ የሚችሉት እንደድጋፍ ሰጪ የመምረጫ መማሪያ እንጂ ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጣልባቸው አለመሆናቸውን ያስገነዝባሉ:: በአጠቃቀም ጊዜም ቀላሉን የቀመር ዓይነት መምረጥ አስፈላጊ መሆኑንና የተመረጠው ቀመርም ቢሆን ቅፅበታዊ ለውጥ የማያስገኝ መሆኑን የማጤንን አስፈላጊነት ከነጥቦቹ መረዳት ይቻላል:: በአጠቃላይ ቀመሮቹ ለተነባቢነት መለኪያ ፍፁማዊ ብቃት እንደሌላቸው፣ በአጠቃቀም ጊዜም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግና በቀመሮቹ መጠቀም የመማር—ማስተማርን ሂደት ሊያጉለብት እንደማይችል ማሳሰቢያዎቹ ያስረዳሉ::

ጠሪሰንም /1989፣ 109—110/ እንደኔለሰን ሁሉ በተነባቢነት ቀመር በሚጠቀሙበት ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችና አደጋዎች እንዳሉ በሚከተሉት አምስት ነጥቦች መሠረትነት ያስረዳሉ፤

1. የተነባቢነት ነጥብ ጠቀሜታ የሚኖረው አለኪሱ ትክክለኛ ከሆነና ስድ ንባቡ ለትንተና አመቺ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2. የንባብ ደረጃ ነጥብ ትክክለኛ የሚሆነው ቀመሩ አስተማማኝ ሆኖ በተገበው ጽሁፋዊ ናሙና ውስጥ የተገለፁት ሥነ ልሣናዊ ባሕርያት በትክክል ከተቆጠሩ ብቻ ነው፡፡

3. የተነባቢነት ነጥብ ተሰሚ ክብደት የሚያሳየው ትክክለኛነት ሲደመር አንድ ወይም ሲቀነስ አንድ /+1 ወይም –1/ ዓመት ወይም የአሜሪካን የክፍል ደረጃ ነው፡፡

4. በአጠቃላይ አነጋገር ሕፃናት ከራሳቸው የማንበብ ደረጃ እስከ ሁለት ዓመት የሚበልጡዋቸውን ጽሁፎች ለማንበብ እንደሚችሉ መገመቱ ትክክል መሆን የሚችለው የመምህሩ የቅርብ ድጋፍ ካለ ወይም የሕፃኑ የማንበብ ፍላጎት ከፍተኛ ከሆነ ነው፡፡

5. የቀመርን ውጤት ወይም ነጥብ በፍፁም፣ ሕፃናት ምን ለማንበብ እንደሚፈልጉና የሚያነቡበትን ዘዴ ለማስተባበል አትጠቀምበት፤ ይልቁንም በተመዘገበው ከፍተኛ ነጥብ ወይም ወጤት ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን ክብደት ለማቋቋም እንደሚያስችል ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ተጠቀምበት::

የጠሪስን አምስቱ የማሳሰቢያ ነጥቦች የሚጠቁሙት፡ የተነባቢነት ቀመሮች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት የተመረጠው ናሙና ምንባብ ለትንተና የሚያመች ከሆነና የናሙናው ሥነ ልሳናዊ ተለዋዋጮች( linguistic variables ) በትክክል ከተቆጠሩ ብቻ መሆኑን ነው:: ከዚህ ሌላ ከቀመሮቹ የሚገኙት ነጥቦች ተሰሚ ክብደት ሊያሳዩ የሚችሉት

ትክክለኛነት ውጤቱ ሲደመር አንድ ወይም ሲቀነስ አንድ /1 ወይም -1/ ዓመት ከሆነ፣ አለበለዚያ የአሜሪካን የክፍል ደረጃ ማመለከት ሲችሉ ነው:: እንደዚሁም ሕፃናት ከደረጃቸው እስከሁለት ዓመት የሚበልጡ ጽሁፎችን ማንበብ ይችላሉ የሚል ግምት ቢኖርም ይህ ግምት ትክክለ የሚሆነው የመምህሩ የቅርብ ድጋፍ ካለ ወይም የሕፃኑ የማንበብ ፍላጐት ከፍተኛ ከሆነ ብቻ መሆኑን ከጠሪሰን አስተያየት መገንዘብ ይቻላል::

ጠሪሰን እነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ቢችሉም ቀመሮቹን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ያምናሉ:: ጠሪሰን የተነባቢነት ቀመሮች ፍፁምነት ባይኖራቸውም የአጠቃቀምና የጥንቃቄ ጉዳይ መሆኑን "አንዳንድ ጊዜ የምንባቦችን ክብደት ለመለካት ቀመሮች አስተማማኝ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ይህ ማለት ግን ቀመሮቹ ጥቅም የላቸውም ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ተጠቃሚው የቀመሮቹን ውጤት በመተርጎሙ ረገድ ጥንቃቄ መውሰድ አለበት::" ሲሉ /1980፣ 43/ ያሰስባሉ:: ይህም የቀመሮቹ አስተማማኝነት የሚጓደለው ከተጠቃሚው የውጤት አተረጓጎም ሁኔታ የመነጨ እንጂ ውጤቶቹን በሚገባ መተርጎም ከተቻለ ቀመሮቹ አስተማማኝ ናቸው ማለትን ያመለክታል::

እስከሁን ከተፈጠረት ቀመሮች የትኛውን መምረጥ እንደሚቻል ቢያዳግትም፣ ተነባቢነትን ለመለካት ለንገለገለባቸው እንደሚገባ የብዙዎች ምሁራን ምክር ነው:: በተቻለ መጠን ግን ተጠቃሚው የሚቀለውን ቀመር መጠቀም እንዳለበትም ያስረዳሉ::

ጠሪሰን /1980/ ዘጠኝ የተነባቢነት መለኪያ ቀመሮችን-የነፓወር፣ ሱምነርናኬርለ /1958/፣ የስፓቼ /1953/፣ የጉንፍርድ ሠንጠረዥ /1970/፣ የፍሪገራፍ /1977/፣ የቲቼ /1973/፣ የዴለቻለ /1948/፣ የፍለሽ /1948/፣ የማክላገሊን ስሞግ /1969/ እና የጋኒንግ ፎግ /1952/ ቀመሮችን-በምሳሌነት በመዘርዘር፣ ከነዚህ ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ በተለይም ለቋንቋ ማስተማሪያ ምንባብ መምረጫ የዴለቻለ፣ የፍለሽ፣ የጉንፍርድ ቀመሮችና የኤድዋርድ ፍሪገራፍ ተስማሚ መሆናቸውን ያስረዳሉ::

በዚህ ጥናት ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ የሚያገለግሉ የአራቱ ቀመሮች መሠረታዊ ባሕርያት ይብራራሉ:: ይሁን እንጂ በምዕራፍ ሦስት እንደሚገለፀው ለጥናቱ በጥቅም ላይ የሚውሉት ከአራቱ ሁለቱ /የፍለሽ ቀመርና የፍሪገራፍ/ ብቻ ናቸው::

### 2.5.1.1. የዳለቻል ቀመር /ጪሪስን 1980፤ 74–77/

የዳለቻል ቀመር የቃላትን ክብደት ለመለካት የቃላትን ዝርዝር በመሠረትነት ይጠቀማል:: የዳለቻል 3,000 የቃላት ዝርዝር በጥናት የተገኘና ስምንት ዓመት ዕድሜ ባላቸው አሜሪካውያን ሊታወቁ የሚችሉትን ቃላት ዝርዝር የያዘ ነው:: ከእነዚህ ዝርዝር የአሜሪካውያን ቃላት ውስጥ ጥቂቶቹ በእንግሊዞች ተቀባይነት ባይኖራቸውም እንግሊዞች እንደሚፅፉት የተጻፉ ቃላት ተቀባይነት ያላቸው ናቸው:: ምንም እንኳን ቀመሩ አስሌት ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም አስተማማኝነት ስላለው ስሌቱ የሚከሄደው እንደሚከተለው ነው፤

የአሜሪካ የክፍል ደረጃ፤ = /0.1579 × ያልተለመዱ ቃላት አማካይ/ + /0.0496 × በየዐረፍተ ነገሩ ውስጥ ያሉ ቃላት/ + 3.0365

የእንግሊዝ የንባብ ደረጃ = የአሜሪካ የክፍል ደረጃ + 5

የተለያዩ ምንባቦችን ክብደት በመለካት ካገኙትና ከባለሙያዎች ለምድ በመነሳት የቀመሩ ውጤት ከባዱን የማስተማሪያ መሣሪያ ቀላል አድርጉ ስለሚያሳይ ዳለናቻል ቀመሩን እንደገና ለመመርመር ተገደዱ:: በዚህም መሠረት የቀመሩን ውጤት ወደተስተካከለ የዕድሜ ደረጃ ለመለወጥ የሚያስችል አስተያየት ሰጡ:: ከዚህ በታች የቀረበው ሠሌዳ የቀመሩን ውጤት ወደተስተካከለ የዕድሜ ደረጃ ለመለወጥ በዳለናቻል የተዘጋጀ ሲሆን፤ የእንግሊዝ የንባብ ደረጃን ከአሜሪካ የክፍል ደረጃ ጋር ለማመጣጠን በአሜሪካ የክፍል ደረጃ ላይ 5 መደመር ያስፈልጋል::

| የዳለናቻል የቀመር ውጤት | የተስተካከለ የዕድሜ ደረጃ |
|---|---|
| 4.9 እና በታች | 9 እና በታች |
| 5.0 – 5.9 | 10 – 11 |
| 6.0 – 6.9 | 12 – 13 |
| 7.0 – 7.9 | 14 – 15 |
| 8.0 – 8.9 | 16 – 17 |

| የሚለናቻለ የቀመር ውጤት | የተስተካከለ የዕድሜ ደረጃ |
|---|---|
| 9.0 – 9.9 | ኮሌጅ |
| 10.0 እና በላይ | ድህረ ምረቃ |

ከዚህም ሌላ ቀመሩ አንድ ቃለ የተለመደ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችሉ ብዙ ደንቦችና ሕጎች አሉት::

2.5.1.2 <u>የፍለሽ ቀመር</u>

ይህ ቀመር በብዛት የተለመደ የተነባቢነት መለኪያ ሲሆን የቀመሩ ስሌት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይከሄዳል /ጤሪስን 1980፣ 77–79/::

የንባብ ቅለት ነጥብ = 206.835 – /0.846 × የቃለ ርዝመት/
– /1.015 × የዐረፍተ ነገር ርዝመት/

በዚህ ስሌት ውስጥ የቃለ ርዝመት የሚገለፀው በ100 ቃላት ውስጥ ባሉት <u>ቀለሞች</u> ብዛት ሲሆን፣ የዓረፍተ ነገር ርዝመት የሚገለፀው በ 100 ቃላት ውስጥ በሚገኙት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባሉት አማካይ የቃላት ብዛት ነው (ለስሌቱ ምዕራፍ አራት ይመለከቷል)::

2.5.1.3. የጉኒፎርድ ሠንጠረዥ

የሊዮናርድ ጉኒፎርድ ሠንጠረዥ የብዙ ዘመናት የምርምርና የክፍል ውስጥ ሙከራዎች ውጤት ነው:: ሠንጠረዡ ብዙ ቀመሮች የማያዩትን ( ንቀው የሚያልፏትን ) ባለብዙ ቀለሞች ያለሆኑትን ፊደሎች ( ሆሄያት ) ብዛት እንደ አንድ የተነባቢነት መስፈርት ባሕርይ ከግምት ውስጥ ማስገባቱ የቀመሩን ጠንካራ ጐን ያመለክታል (ጤሪስን 1980፣ 68 – 71 ያወዳድሩ)

2.5.1.4. የሊዮናርድ ፍሬ ግራፍ

[illegible]

መገመት ይቻላል /ኔ ፖል 1982/:: ግራፉን በመመልከት ጸሀፊ ለየትኛው የክፍል ደረጃ ሊመጥን እንደሚችልና እንደተዘጋጀ መናገር ይቻላል:: በግራፉ መጠቀሙ /ግራፉን ከአባሪ ሀ ይመለከቷል/ ከሰሌት ከሚጻኑም በላይ በግልፀ የሚታዩ መረጃዎችን ይሰጧል::

## 2.6. የገንዘቤ ሙከራ /ጤሪሰን 1980፣ 84 –106 /

ሌላው ተነባቢነትን ለመለካት የሚያገለግለው ባዶ ቦታ በመሙላት የሚመለስ የገንዘቤ ሙከራ ነው:: የገንዘቤ ሙከራን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙት አሜሪካዊው ዊለሰን ታይለር ሲሆኑ፣ ይህም የአንድን አንባቢ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የጸሁፉን ተነባቢነት በመለካት በተወሰኑ ርቀቶች (ብዙውን ጊዜ 5ኛውን ቃል) ቃላትን ከምንባቡ ውስጥ በማጉደል የመፈተን አዲስ ዘዴ ነው:: በተተወት ባዶ ቦታዎች ላይ በትክክል የተሞሉ ቃላት የአንባቢውን የመረዳት ችሎታ ያመለክታሉ:: ከዚህ አንፃር የገንዘቤ ሙከራ የአንባቢን አንብቦ የመረዳት ደረጃና የጸሁፉን ተነባቢነት ለመለካት ያገለግላል ማለት ነው::

የገንዘቤ ሙከራ ተነባቢነትን ይለካል እንጂ እንደ ቀመሮች ክብደትን ለመገመት አይረዳም:: ከዚህ አንፃር ቀደም ሲል ከተገለፁት የተነባቢነት ቀመሮች መሠረታዊ ለዩነት አለው:: እንደዚሁም የገንዘቤ ሙከራ ከምርጫ ጥያቄዎች ( Multiple choices ) በሦስት ነጥቦች እንደሚለይ ጤሪሰን (1980) ያስረዳሉ::

እነዚህም ነጥቦች:

1. የገንዘቤ ሙከራ የሚለካው የራሱን የምንባቡን ክብደት እንጂ የቀረቡትን ጥያቄዎች ክብደት አይደለም፤ በምርጫ ጥያቄ ግን ከምንባቡ ይልቅ ጥያቄዎቹ የበለጠ ክብደት ሊኖራቸው ይችላል፤ ስለበለዚያ የአንባቢውን የመረዳት ችሎታ አያመለክቱም ይሆናል፤

2. የገንዘቤ ሙከራ አንባቢው ካካበተው ዕውቀትና ከምንባቡ አውድ በመረዳት ምንባቡን የተሟላ ያደርገዋል፤ በተቃራኒው የምርጫ ጥያቄ መልስ የሚመለሰው ተፈታኙ ምንባቡን ካነበበ በኋላ ስለሆነ ምንባቡን [illegible] ለማድረግ ዕውቀት ይኑረው አይኑረው አይታወቅም፤

3. የገንዘቤ መከራ ከምንባቡ ውስጥ የተጎደሉትን ቃላት፣ ጠረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ክብደት ያሳያል፤ በምርጫ ጥያቄ ግን በዓረፍተ ነገር ትርጉምና በቃል ፍች መካከል ያለውን የክብደት ደረጃ ከጥያቄው መረዳት አይቻለም::

በገንዘቤ መከራ አንባቢው የጎደሉትን ቃላት እንዲሞላ የሚጠየቀው ጽሁፉን ካነበበ በኋላ ወይም ከማንበቡ በፊት ሊሆን ይችላል:: የጎደሉትን ቃላትም መገመት የሚችለው ከአውደ — ንባቡና ከአጠቃላይ የምንባቡ መንፈስ በመረዳት ነው::

ለመከራው የሚመረጡት ናሙና ምንባቦች ሦስት ሲሆኑ የሚገኙትም በመጽሀፉ መጀመሪያ፣ መካከሉና መጨረሻ ነው:: የሚተው ባዶ ቦታዎች እስከ 50 ቢደርሱ ይመረጣል:: በእያንዳንዱ ናሙና ምንባብ ውስጥ 35 ክፍት (ባዶ) ቦታዎችን መተው የሚቻል ቢሆንም የክፍት ቦታዎች መብዛት የመከራውን ውጤት ትክክለኝነት ይጨምራል:: ስለዚህ ከ40 — 50 ክፍት ቦታዎች በመተው ተፈታኙ እንዲሞላ ማድረጉ የበለጠ አስተማማኝ ውጤት ለማስገኘት ይረዳል:: በፈተናው ሊሳተፉ የሚችሉት የተማሪዎች ብዛት ከ20 — 30 መሆን ይችላል::

ክፍት በተተወት ባዶ ቦታዎች እንዲሞሉ የሚፈለጉት ቃላት የጽሁፉ ደራሲ ወይም ፀሀፊ የተጠቀመባቸው ቃላት ብቻ ናቸው:: ተመሣሣይ ቃላት መጠቀም የፈተናውን ውጤት ለማስላት ጊዜ ከመውሰዱም ባሻገር የቃላቱን ተመሳሳይ ማግኘት ይቸገራል፤ ቢገኝም አስተማማኝነት ላይኖረው ይችላል:: ስለዚህም የፀሐፊውን ቃላት ብቻ እንደትክክለኛ መልስ መውሰዱ ይመረጣል::

የገንዘቤ መከራው ውጤት የሚተረጎመው በትክክል የተሞሉ (የተመለሱ) ቃላትን በሁለት አባዝቶ ወደ መቶኛ (%) በመለወጥ ነው:: በዚህ ዓይነት የተገኙ ውጤቶች በሦስት ደረጃ በመከፈል ትርጉም ይሰጣቸዋል:: ይኸውም ከ39 እና በታች የሚያገኙ ተማሪዎች ትምህርቱን መቀጠል ከማይችሉበት ( frustration level ) ደረጃ፣

ከ40 — 50 የሚያገኙ ተማሪዎች በድጋፍ የሚማሩበት ( instructional level ደረጃና ከ50 ከመቶ በላይ የሚያገኙ በግላቸው ሊማሩ የሚችሉበት ( independent level ) ደረጃ ተብለው ይተረጎማሉ (በርሄ 1989፣ 39)::

እስካሁን በኢትዮጵያ የተሠሩ የመረዳት ችሎታዎችና የክብደት መለኪያ መስፈርቶችንም ማየቱ አስፈላጊ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በነዚህ ርዕሰ — ጉዳዮች ላይ የተደረጉት ጥናቶች ጥቂት ናቸው:: ጆምስሊ በ1967 የዲቪስ ቴስትና የፍለሽ ቀመርን በመጠቀም ጥናት አድርገዋል:: ፀጋዬ ወልደየሱስ በ1982 ባዶ ቦታ በመሙላት የሚመለሰውን የገንዘቤ መስፈርና ፍገ ኢንዲክስን በመጠቀም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂዷል:: ጥበበ ዓለማየሁ (1987) ባዶ ቦታ በመሙላት የሚመለሰውን የገንዘቤ መስፈርና ፍገ ኢንዲክስን በመጠቀም በመንግሥት ትምህርት ቤቶችና በሚሽን ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መካከል ያለውን የማንበብ ብቃት ልዩነት አስተበታለ:: ወንዲዳ በርኪሳ ከባሕር ዳር የመምህራን ትምህርት ክሌጅ ከአንደኛ ዓመት ተማሪዎች የሚጠበቀውና ያላቸውን የማንበብ ችሎታ ለመለካት ተጠቅሞበታል:: የመጨረሻው በርሄ ከህሳይ በ1989 ያካሄደው ጥናት ነው:: ጥናቱ የፍሪ ግራፍንና ባዶ ቦታ በመሙላት የሚመለሰውን የገንዘቤ መስፈሪ በመጠቀም የተካሄደ ሲሆን፣ የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፎችና የተጠቃሚ ተማሪዎች የመረዳት ችሎታን በመለካት ላይ ያተኮረ ነበር::

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች የተገኙት ውጤቶች በሙሉ አዎንታዊ አይደሉም:: የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በሚመለከት የተገኙ ውጤቶች በሙሉ ከሚጠበቀው ደረጃ ከፍ ወይም ዝቅ ብለው መገኘታቸውን ያመለክታሉ:: የተጠቃሚ ተማሪዎች ደረጃም እንደዚሁ ትምህርቱን መቀጠል ከማይችሉበት ደረጃ የሚወደቡ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤቶች ያሳያሉ::

ከነዚህ በእንግሊዝኛ ቋንቋና በእንግሊዝኛ በተጻፉ የመማሪያ መጽሀፎች ላይ ከተካሄዱት ጥናቶች ውጭ በአማርኛ ቋንቋና በአማርኛ መማሪያ ጽሁፎች ላይ የተካሄደ ጥናት የለም::

# ምዕራፍ 3

## የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱን ለማካሄድ ምን ምን ዘዴዎች በእንዴት ዓይነት ሁኔታና መንገድ ተገባራዊ እንደሆነ ለማቅረብ ይሞከራል::

### 3.1 የመርሀ–ትምህርቱ ዓላማና የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ግንኙነት

የማስተማሪያ መጽሐፍና መርሀ–ትምህርት የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ቀደም ሲል ተገልጿል:: ከተገለጹት የሁለቱ መማሪያዎች ግንኙነት አንፃር የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሀፍ ምንባቦችና የክፍሉ መርሀ–ትምህርት ምን ያህል እንደተገናኙ ለመመርመር ጥረት ተደርጓል::

የሁለቱን መማሪያዎች ግንኙነት ለመመርመር ይረዳ ዘንድ የመርሀ–ትምህርቱን የተለያዩ ክፍሎች (ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ምዘናዎች) በአበይ የትምህርት ዓላማዎች መመደብ አስፈላጊ ነው:: ከዚህ በታች የመርሀ–ትምህርቱ አራት ክፍሎች በዘጠኝ የተለያዩ አበይ የትምህርት ዓላማዎች ተመድበው ቀርበዋል::

<u>ሠንጠረዥ 1</u>፣ የአሥረኛ ክፍል መርሀ–ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ምዘናዎች

| ተ.ቁ. | አበይ የትምህርት ዓላማዎች | ዝርዝር ዓላማዎች | % | ይዘቶች | % | ክንውኖች | % | ምዘናዎች | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 1 | 5.3 | 6 | 85.7 | 7 | 2.5 | 4 | 25.2 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 0 | 0 | 3 | 4.3 | 20 | 7.1 | 6 | 3.3 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 4 | 21.0 | 10 | 14.5 | 38 | 13.5 | 22 | 12.2 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 5 | 26.3 | 11 | 15.9 | 23 | 8.2 | 27 | 15.0 |
| 5 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 5 | 26.3 | 14 | 20.3 | 91 | 32.4 | 52 | 28.9 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 3 | 15.8 | 12 | 17.4 | 27 | 9.6 | 29 | 16.1 |
| 7 | የመናገር/የመጻፍ ክሂል | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 3.6 | 3 | 1.7 |
| 8 | የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም | 0 | 0 | 2 | 2.9 | 3 | 1.1 | 0 | 0 |
| 9 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 1 | 5.3 | 11 | 15.9 | 62 | 22.1 | 37 | 20.6 |
| | ድምር | 19 | 100 | 69 | 100 | 281 | 100 | 180 | 100 |

| ተራ ቁ. | አቢይ የትምህርት ዓላማዎች | የመልመጃዎች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 4 | 3.3 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 6 | 5.0 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 41 | 34.2 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 8 | 6.7 |
| 5 | የሥነልሳን ትምህርት | 38 | 31.7 |
| 6 | የሥነጽሑፍ ትምህርት | 11 | 9.1 |
| 7 | የመናገር/የመጻፍ ክሂል | 2 | 1.7 |
| 8 | ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 3 | 2.5 |
| 9 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 7 | 5.8 |
| | **ድምር** | **120** | **100** |

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው ዘጠኝ አቢይ የትምህርት ዓላማዎች ተዘርዝረዋል:: ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ መሠረታዊ ክሂሎች በመሆናቸው፣ ሥነልሳንና ሥነጽሑፍም የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች አካል በመሆናቸው ራሳቸውን የቻሉ ዓላማዎች ሆነው ቀርበዋል:: መናገር/መጻፍ በሚል ርዕስ የቀረበው ከሁለቱ በአንዱ ለመመደብ ያልተቻሉ ሁለቱንም በአማራጭነት ለመጠቀም የሚያስችሉ ሆነው የተገኙ ነጥቦች የተካተቱበት ነው:: የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ከመጽሐፉ የመልመጃ ይዘቶች አንዱ ሲሆን ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች የሚለው ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ውስጥ ከመመደብ ገለፅነት የጐደላቸው ናቸው::

የመርሀ–ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሀፉን ግንኙነት ለመመርመር እንዲረዳ አራት ሠንጠረዦች ቀርበዋል:: ቀደም ሲል በሠንጠረዥ 1 የተገለፁትን የመርሀ–ትምህርቱን አራት ክፍሎች አንድ በአንድ በመውሰድ ከአማርኛ የመማሪያ መጽሀፉ መልመጃዎች ይዘቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተዛምዶ ቀመር ለመመርመር ተሞክሯል:: በተዛምዶ ቀመሩ አማካኝነት ለተገኙት ውጤቶች በአባሪ ለ ላይ በተገለፀው መሠረት ትርጓሜ ተሰጥተቷቸዋል::

በመጨረሻም በነዚህ የተዛምዶ ትርጓሜዎች መሠረትነት በመርሀ–ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖች፣ ግምገማዎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ይዘቶች መካከል የሚዘገቡት የግንኙነት ውጤቶች እን [illegible]

## 3.2 የማስተማሪ መጽሐፍ ምንባቦችና የተማሪዎች ፍላጎት

ጥናቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ነው:: ከክልል 14 መስተዳድር የትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት 22 የመንግሥት ትምህርት ቤቶች አሉ:: እነዚህ ትምህርት ቤቶች በአስተዳደራዊ ብቃታቸው፣ በአደረጃጀታቸው፣ በቤተ—መጻሕፍት ይዞታቸውና በመሳሰሉት መስፈርቶች ተመዝነው በሦስት ደረጃዎች ይመደባሉ:: በተገኘው መረጃ መሠረት የተሻለ አደረጃጀት ያላቸው ትምህርት ቤቶች 6፣ በመካከለኛ ደረጃ የተመደቡት 7 ሲሆኑ ዝቅተኛ አደረጃጀት ያላቸው 9 ትምህርት ቤቶች ናቸው::

ለጥናቱ ያመች ዘንድ ከሦስቱም የተለያዩ ደረጃዎች ሁለት፣ ሁለት በጠቅላላው 6 ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል:: ከየደረጃዎቹ ሁለት፣ ሁለት ትምህርት ቤቶችን ለመምረጥ እንዲያመች በየደረጃዎቹ የሚገኙት ትምህርት ቤቶች በዝርዝር ተጽፈዋል:: በዝርዝሩ መሠረት ከተራ ቁጥር አንድ ተነስቶ ሁለት ተራ ቁጥሮችን በማለፍ ለአንደኛው ደረጃ በተራ ቁጥር 1 እና 4 የተመዘገቡ፣ ለሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን በማለፍ በተራ ቁጥር 3 እና 6 የተመዘገቡ እንደዚሁም ለሦስተኛ ደረጃ ሦስት፣ ሦስት ትምህርት ቤቶችን በማስለፍ በተራ ቁጥር 4 እና 8 የተመዘገቡ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል:: በዚህ ዘዴ መሠረት ለአንደኛው ደረጃ አየር ጤና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና አዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ፣ ለሁለተኛው ደረጃ ገነቦት ሃያ ሁለተኛ ደረጃና ወንድይራድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ ለሦስተኛው ደረጃ ኢስ.ኦ.ኢስ ከፍተኛ ሃያ ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና አቃቂ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል::

<u>ሠንጠረዥ 3</u>፣ የናሙና ትምህርት ቤቶች የአሥረኛ ክፍል ምድቦችና የተማሪዎች ብዛት

. . . /

| ተራ ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የምድቦች ብዛት | የተማሪዎች ብዛት (አማካይ) | የተመረጡ ምድቦች | % | ተጠኚዎች ተማሪዎች | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አየር ጤና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 18 | 1170 | 5 | 27.5 | 81 | 25 |
| 2 | አዲስ ከተማ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 16 | 1040 | 4 | 25.0 | 65 | " |
| 3 | ኢስ.ኦ.ኢስ ከፍተኛ 23 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 6 | 390 | 2 | 33.3 | 32 | " |
| 4 | ወንደይራድ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 10 | 650 | 3 | 30.0 | 49 | " |
| 5 | ገንቦት ሃያ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 15 | 975 | 4 | 20.7 | 65 | " |
| 6 | አቃቂ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 11 | 715 | 3 | 27.3 | 48 | " |
| | **ድምር** | **76** | **4940** | **21** | | **340** | |

በየትምህርት ቤቱ ከሚገኙት ምድቦች ውስጥ በጥናት እንደታቀፉ የተመረጡት ምድቦች ስም ዝርዝራቸው ከተፃፈ በኋላ የተወሰኑ ቁጥሮችን በመዝለል (በማለፍ) ነው:: ለምሳሌ ከአየር ጤና 18 ምድቦች መካከል 5ቱቱ ምድቦች ሊመረጡ የቻሉት በተራ ቁጥር 1፣ 5፣ 9፣ 13 እና 17 የተመዘገቡ ምድቦች ነው::

ከየትምህርት ቤቱ የተማሪዎች የስም ዝርዝር መዝገብ ላይ በተገኘው መረጃ መሠረት በየምድቡ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር (ብዛት) በአማካይ ከ61–70 የሚደርሱ ሲሆን፣ በየምድቡ በአማካይ 65 ተማሪዎች እንደሚኖሩ በመገመት ናሙናው ተወስኗል::

በየምድቡ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል በጥናቱ እንዲታቀፉ የተደረጉት ተማሪዎች 25% ናቸው:: የተመረጡት ተማሪዎች ከተመዘገቡበት የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ስም ዝርዝር መዝገብ ላይ የተወሰደ ሲሆን፣ የተመረጡትም ከተራ ቁጥር አንድ በመጀመር አራት፣ አራት ተማሪዎችን በመዝለል ነው:: ከሁሉም ናሙና ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቹ የተመረጡት በተመሳሳይ ሁኔታ ነው::

በጥናቱ እንዲሳተፉ የተደረጉት የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መምህራንም ጥምር ናቸው:: ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ የመምህራንን ናሙና መውሰድ አላስፈለገም:: የመም፡ህራኑ ቁጥር እንዲበዛ በማሰብ አምና (1985 ዓ.ም.) በአዲሱ መጽሀፍ [illegible] ያስተማሩ መምህራንም በተሰባሰበ ሁኔታ የቀረበውን መጠይቅ [illegible] [illegible]::

ትምህርት ቤቶች፣ ሞዱሎችና ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ ጥና[illegible] ሳተፉ የተመረጡት ተማሪዎችና መምህራን መጠይቆች ታድሏቸዋል:: ተማሪዎች የታደሉት መጠይቆች ከአማሽ ጥናት የተመረጡ ሆነው ባለ 24 ጥያቄዎችና ባለ 4 ክፍሎች ናቸው:: የተመረጡት ተማሪዎች ለብቻቸው ከተለዩ በኋላ ስለመጠይቆቹ ዓላማና አሞላል ገለፃ ተደርጉላቸዋል:: መጠይቁ በአግኙው አየተነበበላቸው ተማሪዎቹ እንዲሞሉ ተደርጓል:: በመጨረሻም መጠይቆቹ ተሰብስበው ሲቆጠሩ 337 ሆነው ተገኝተዋል::

በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የአሥረኛ ክፍለ የአማርኛ መምህራንና በመጽሐፉ የተጠቀሙ የአማርኛ መምህራን እንዲሞሉ የታደላቸው መጠይቅ 26 ጥያቄዎችን የያዙ 4 ክፍሎች አሉት:: መጠይቆቹ በታደሏቸው በማግስቱ ሲሰበሰቡ ከ18 መጠይቆች መካከል አንዱ ሲቀር 17ቶቹ ሊሰበሰቡ ችለዋል::

## 3.3 የምንባቦቹ ተነባቢነት

የምንባቦቹ ተነባቢነት የሚለካው በቀመሮቹ መሆኑ ተገልጿል:: ጤሪሰን ከጠቀሷቸው 9 የተነባቢነት ቀመሮች ለሁለተኛ ደረጃ ምንባቦች ተነባቢነት መለኪያ ሊያገለግሉ የሚችሉት ቀመሮች 4ቱ ብቻ መሆናቸውም ተገልጿል::

ለዚህ ጥናት የተመረጡት 2 ቀመሮች ብቻ ሲሆኑ፣ እነዚህም የፍለሽ ቀመርና የኤድዋርድ ፍሪ ግራፍ ናቸው:: ከቀሩት 2ቱ ቀመሮች መካከል እነዚህ ሊመረጡ የቻሉት ቀላልና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያመቹ ሆነው በመገኘታቸው ነው::

ለሁለቱ ቀመሮች በናሙናነት እንዲያገለግሉ የተመረጡት ምንባቦች 3 ሲሆኑ እነዚህም ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከለና መጨረሻ ላይ የተወሰዱ ናቸው::

### 3.3.1 የፍለሽ ቀመር

ይህ ቀመር በብዛት ጥቅም ላይ የሚውልና ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል ቀመር ሲሆን፣ የቀመሩን ውጤት ለማስላት የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፤

ሀ) 3 ባለ 100 ቃላት ናሙና ምንባቦችን ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከለና መጨረሻ መውሰድ፣

ለ) በ100 ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቀለሞች መቁጠር፣

ሠ) በ100 ቃላት ውስጥ በሚገኙት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን የሦስቱን ናሙና ምንባቦች የቃላት ብዛት አማካይ ማውጣት፣

ጠ) ቀመሩን ተግባራዊ ማድረግ

ከላይ በተገለፁት ዘዴዎች አማካይነትየተገኘው ውጤት በሚከተለው ቀመር መሠረት ሊሰላ ይችላል፤

$$\text{የንባብ ቅለት ነጥብ} = 206.835 - /0.846 \times \text{የቃላ ርዝመት}/ - /1.015 \times \text{የዓረፍተ ነገር ርዝመት}/$$

- የቃለ ርዝመት የሚገለፀው በ100 ቃላት ውስጥ ባሉት ቀለሞች ብዛት ነው፣
- የዓረፍተ ነገር ዝርመት የሚገለፀው በ100 ቃላት ውስጥ በሚገኙት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባሉት አማካይ የቃላት ብዛት ነው::

በዚህ ዓይነት ስሌት የተገኘው ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ አማካኝነት ይተረጎማል (ስለስሌቱ ውጤት ሠንጠረዥ 29 ይመለከቷል)::

ሠንጠረዥ 4፣ የፍለሽ ቀመር የንባብ ቅለት ትርጉም

| የንባብ ቅለት ነጥብ | የክብደት ደረጃ መግለጫ | የተገመተው የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|
| 90 – 100 | በጣም ቀላል | 5ኛ ክፍል |
| 80 – 89 | ቀላል | 6ኛ ክፍል |
| 70 – 79 | በመጠኑ ቀላል | 7ኛ ክፍል |
| 60 – 69 | ተገቢ (መካከለኛ) | 8ኛና 9ኛ ክፍል |
| 50 – 59 | በመጠኑ ከባድ | ከ10ኛ – 12ኛ ክፍል |
| 30 – 49 | ከባድ | ከ13ኛ – 16ኛ ክፍል |
| 0 – 29 | በጣም ከባድ | የድህረ ምረቃ ደረጃ |

የ100 ቃላትን ቀለሞችና በቃላቱ ውስጥ የሚገኙት ዓረፍተ ነገሮች የያዟቸው አማካይ የቃላት ብዛት ወስደ ቀመሩን ተግባራዊ በማድረግ የሚገኘው ውጤት የንባብ ቅለት ነጥብ ሲያሳይ፣ ይህም የምንባቡን የክብደት ደረጃ አመልካች ነጥብ ነው:: ለምሳሌ

ሁሉ፣ የሚገኝ ነጥብ ከ90 – 100 ባለው ርቀት መካከል በሆነ በጣም ቀላል የሚል መገለጫ የሚሰጠውና ለ5ኛ ክፍል የሚመጥን ምንባብ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ቀመሩ ምንባቦች ያላቸውን የክብደት ደረጃና የሚመጥኑትን የክፍል ደረጃ እስከ ድህረ – ምረቃ ደረጃ ድረስ ይገልጻል፡፡

### 3.3.2 የኤድዋርድ ፍሪ ግራፍ

የፍሪ የተነባቢነት ግራፍን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን መመሪያዎች በመከተል የአንድን ጽሁፍ የክፍል ደረጃ መገመት ይቻላል፤

ሀ) 3 ባለ 100 ቃላት ምንባቦችን ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ መምረጥ፣

ለ) በእያንዳንዱ ባለ 100 ቃላት ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ጠቅላላ የዓረፍተ ነገር ብዛት ቁጥር (ከ100 ቃላት የተረፉትን የመጨረሻውን የዓረፍተ ነገር ቃላት ወደ 1/10ኛ አጠጋጋ)፤ የ3ቱን አማካይ አውጣ፣

ሐ) በ3ቱ ባለ100 ቃላት ናሙና ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን ቀለሞች ብዛት ቁጠር፤ የ3ቱን ናሙና ምንባቦች ቀለሞች ጠቅላላ አማካይ አውጣ፣

መ) ከላይ የተጠቀሱትን ዘዴዎች (በ'ለ'ና በ'ሐ' የተገለፁትን) ውጤቶች በግራፉ ላይ አመልክት፡፡ በአብዛኛው እነዚህ ቁጥሮች የሚያርፉበት ሁለቱ ቀጥተኛ መስመሮች በጉልህ በሚተላለፉበት ቦታ ላይ ሲሆን፣ ይህም ግምታዊ የክፍል ደረጃውን ያመለክታል፡፡

## 3.4 የግንዛቤ መከራ

የግንዛቤ መከራ ተነባቢነትንና የመረዳት ደረጃን ለለኩ ከሚችሉና ሁለንተናዊ ተቀባይነትን እያገኙ ከመጡት ዘዴዎች መካከል አንዱ በመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

### 3.4.1 የናሙና ምንባቦች አመራረጥ

በማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ካሉት 16 ምንባቦች ውስጥ 3 ምንባቦች ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ተመርጧል፡፡ እነዚህም በፍላሽ ቀመርና ግራፍ የተመረጡት ምንባቦች ናቸው፡፡

### 3.4.2 የናሙና ተማሪዎች አመራረጥ

ለገንዘቤ ሙከራው 90 ተማሪዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ እነዚህም መጠይቁን እንዲሞሉ ከተደረጉት 340 ተማሪዎች መካከል የተመረጡ ናቸው:: ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለገንዘቤ ሙከራው የተመረጡት ተማሪዎች መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ብዛት አንፃር ነው:: ስለዚህ ከአየር ጤና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 21፣ ከአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 17፣ ከማንቦጅ ሃያ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 17፣ ከአቃቂ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 13፣ ከወንድይራድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 13 እና ከኤስ.ኦ.ኤስ. ከፍተኛ ሃያ ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 9 ተማሪዎች ናቸው::

ከየትምህርት ቤቱ ለመጠይቁ የተመረጡት ተማሪዎች ስም ዝርዝር ከተፃፈ በኋላ የተማሪዎቹ ቁጥር የተፈለገውን ያህል እስኪሆን ድረስ የተወሰኑ ተማሪዎችን በማለፍ (በመዝለል) እንዲመረጡ በመደረጉ የአመራረጣቸው ሁኔታ ሥርዓት የተከተለ ነው::

### 3.4.3 የሙከራው አደረጃጀት

ተማሪዎቹ የናሙና ምንባቦቹን ጠሰቦች ለመገመት እንዲረዳቸው ከየናሙናዎቹ ምንባቦች የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ቃላት አለተጉደሉም:: ከ2ኛው ዓረፍተ ነገር ጀምሮ ግን በየ4ቱ ቃላት በኋላ (በ5ኛው ቃል) ክፍት ቦታዎች በመተው ተዘጋጅተዋል:: ለእያንዳንዱ ናሙና ምንባብ 50፣ 50 ክፍት ቦታዎች የተተው ሲሆን፣ ተማሪዎቹ ለ3ቱ ምንባቦች 150 ቃላት እንዲሞሉ ተደርጓል::

### 3.4.4 የሙከራውአሰጣጥ

ተፈታኞች ሳይረበሹና ሳይደናገጡ በተረጋጋ መንፈስ መሥራት እንዲችሉ በማሰብ የሚከተሉት ማብራሪያዎች የተሰጡ ሲሆን፣ ሙከራው የተሰጠው ከሚማሩበት ፈረቃ ውጭ በትርፍ ጊዜያቸው ነው፤

ሀ) የፈተናው ዓላማ ለተፈታኝ ተማሪዎች፣ ለፈታኝ መምህራንና ለርዕሳነ መምህራን ተገልጿል።

ለ) ሙሉ በሙሉ ሠርተው እስኪጨርሱና ራሳቸው በቃን እስኪሉ ድረስ በቂ ገዜ እንዳላቸው ተነግሯቸዋል።

ሐ) ፈተናውን ከመሥራታቸው በፊት በደንብ እንዲያነቡት ተነግሯቸዋል።

መ) ለአንድ ክፍት ቦታ አንድ ቃል ብቻ እንዲመለሱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል።

ሠ) ግልጽ ያልሆኑና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙ ወዲያውኑ አርሞ ለማስተካከል እንዲረዳ እስከሙከራው ፍጻሜ ድረስ በአጥኚው በኩል ጥብቅ ክትትል ተደርጓል።

### 3.4.5. የነጥብ አሠጣጥና አተረጓጎም ዘዴ

በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ላይ የተሞሉ ትክክለኛ ቃላትን በ2 ማባዛት። የተገኙትን ውጤቶች በገጽ 39 በተገለፀው መሠረት ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል::

# ምዕራፍ 4

## የመረጃና የጥናቱ ዉጤት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተገኙትና የተሰበሰቡት መረጃዎች ይቀርባሉ፤ ከመረጃዎቹ የተገኙት ዉጤቶች እየተተነተኑ ይብራራሉ::

### 4.1 የመረጃ ትንተና

#### 4.1.1 ከመርሀ — ትምህርትና ከመማሪያ መጽሀፍ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከመርሀ ትምህርቱም ሆነ ከመማሪያ መጽሀፉ የተገኙ መረጃዎችን ለመተንተን እንዲያመች የተለያዩ ሠንጠረዦች ቀርበዋል:: ከ6—8 የቀረቡት አራት ሠንጠረዦች የመርሀ—ትምህርቱን ሁኔታዎች የሚያመለክቱ ሲሆኑ፤ የሚቀጥለው ሠንጠረዥ /9/ የማስተማሪያ መጽሐፉን ይዘት የሚያመለክት ነው::

ከነዚህ ሠንጠረዦች በተጨማሪ የመርሀ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፉን ግንኙነት ለመተንተንና ለማብራራት ሌሎች አራት ሠንጠረዦች /ከ10 — 13/ በቅደም ተከተል ቀርበዋል::

**<u>ሠንጠረዥ 5</u>፤ የአምረኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ—ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች መገለጫ**

| ተራ ቁ | አቢይ የትምህርት ዓላማ | የዝርዝር ዓላማዎች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 1 | 5.3 |
| 2 | የማንበብ ክሂል | 4 | 21.0 |
| 3 | የመጻፍ ክሂል | 5 | 26.3 |
| 4 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 5 | 26.3 |
| 5 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 3 | 15.8 |
| 6 | ልዩ ልዩ የትምህርት ይዘቶች | 1 | 5.3 |
| | ድምር | 19 | 100 |

ሠንጠረዡ እን ሚያመለክተው ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ለመጻፍ ክሂልና ለሥነ ልሳን የቋንቋ ዘርፍ ነው:: በሁለተኛነቱ ትኩረት የተሰጠው ለማንበብ ክሂል ሲሆን ለሥነ ጽሁፍ የተሰጠው ግምት የአራተኛነት ደረጃ ነው:: ለማዳመጥ የመጨረሻ ግምት ተሰጥቶታል፤ ሌሎች ክሂሎችና የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ተረስተዋል:: ከ1 – 5 ከተዘረዘሩት አበይ ነጥቦች ውስጥ ሊገባ ያልቻለ አንድ ጉዳይ ብቻ አጋጥሟል:: የመርሀ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች ለሁሉም ክሂሎችና የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ተመጣጣኝ ሥርጭት የላቸውም:: ለአንዱ አበይ ነጥብ ከሌላው አበይ ነጥብ የበለጠ ግምት ተሰጥቶታል:: ከመርሀ ትምህርቱ ዓላማ አንፃር ሲታይ ደግሞ ምንም ግምት ያልተሰጣቸው ነጥቦች አሉ::

**ሠንጠረዥ 6፤ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ – ትምህርት ይዘቶች መገለጫ**

| ተራ ቁ | አበይ የትምህርት ዓላማ | የይዘቶች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 6 | 8.7 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 3 | 4.3 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 10 | 14.5 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 11 | 15.9 |
| 5 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 14 | 20.4 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | ሠ 12 | 17.4 |
| 7 | የቤተ መጻህፍት አጠቃቀም | 2 | 2.9 |
| 8 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 11 | 15.9 |
| | ድምር | 69 | 100 |

ሥነ ልሳን ከሁሉም የበለጠ ብዛት ተሰጥቶታል:: ሥነ ጽሁፍ፣ ማንበብና መጻፍ እንደቅደም ተከተላቸው በሁለተኛነት፣ በሦስተኛነትና በአራተኛነት ከሌሎች የተሻለ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል::

ከነዚህ ከተዘረዘሩት አበዩ ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች ውጭ የሆኑ 11 የመርሀ ትምህርቱ ይዘቶች የተመዘገቡ ሲሆኑ፣ እነዚህ ግልጽነት የጎደላቸው ይዘቶች ናቸው:: በዚህ ሠንጠረዥ ላይ በሰፈረው ደረጃ መሠረት ከፍተኛ ግምት የተሰጠው [illegible] የትምህርት ዘርፍ ነው::

.../

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ 7፡ የአማረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ክንውኖች መግለጫ

| ተራ ቁ | አቢይ የትምህርት ዓላማ | የክንውኖች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 7 | 2.4 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 20 | 7.1 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 38 | 13.5 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 23 | 8.2 |
| 5 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 91 | 32.4 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 27 | 9.6 |
| 7 | የመናገርና የመጻፍ ክሂል | 10 | 3.6 |
| 8 | የቤተመጻህፍት አጠቃቀም | 3 | 1.1 |
| 9 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 62 | 22.1 |
| | ድምር | 281 | 100 |

በሠንጠረዥ 7 ላይ እንደተመለከተው ግለጸነት የጐደላቸው አቢይ የትምህርት ርእሶች 22.1% ይዘዋል:: ይህ ሁሉ ነጥብ ለየትኛው ክሂልና የትምህርት ዘርፍ እንደተዘጋጀ አይታወቅም:: ለትምህርትነት ከቀረቡት 281 ክንውኖች ውስጥ የሥነ ልሳን ትምህርት 91 ጊዜ ያህል ሲጠቀስ በሁለተኛነት የቀረበው የማንበብ ክሂል 38 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል:: የቀሩት ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች እየቀነሱ እንደሚሄዱ ሠንጠረዡ ያሳያል:: በዚህም መሠረት ሥነ ጽሁፍ 27፣ የመጻፍ ክሂል 23፣ የመናገር ክሂል 20፣ ... ጊዜ በትምህርትነት እንዲቀርቡ ተደርገው ተዘጋጅተዋል:: ይህም የሚያሳየን ግለጸነት ከጐደላቸው ነጥቦች ውጭ የሥነ ልሳን ትምህርት ከፍተኛውን ግምት እንዳገኘ ነው::

ሠንጠረዥ 8፡ የአማረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ግምገማዎች መግለጫ

.../

| ተራ ቁ. | አቢይ የትምህርት ዓላማ | የገምጋሚዎች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማጻወጥ ክሂል | 4 | 2.2 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 6 | 3.3 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 22 | 12.2 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 27 | 15.0 |
| 5 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 52 | 28.9 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 29 | 16.1 |
| 7 | የመናገር/መጻፍ ክሂል | 3 | 1.7 |
| 8 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 37 | 20.6 |
| | **ድምር** | **180** | **100** |

በሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች ለመወደብ ገለጸነት የጎደላቸው ነጥቦች በርከታውን ነጥብ በይዞም ለትምህርት ከቀረቡት 180 የገምገማ ነጥቦች ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት 17.2% ጊዜ ያህል ተመቅሏል:: ለሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች በሰንጠረዥ ላይ የተመለከተውን ያህል ትኩረት ተሰጥቶታል::

በአጠቃላይ በአራቱም ሰንጠረዦች ላይ በተመዘገቡት መረጃዎች መሠረት በክሂሎችና በትምህርት ዘርፎች ለመወደብ ገለጸነት ከጎደላቸው አቢይ ትምህርቶች በስተቀር ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለሰዋሰው የትምህርት ክፍል ነው:: ለሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የተሰጧቸው ግምት አምብዛም ነው:: በሌላ አባባል ሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የሰዋሰው ትምህርትን ያህል ለትምህርትነት እንዲቀርቡ ሆነው አልተዘጋጁም:: ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ለአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ከአጠቃቀም ይልቅ ለአወቃቀር ከፍተኛ ግምትና ትኩረት መስጠቱን ነው::

<u>ሠንጠረዥ 9፣</u> **የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ መለመጃዎች ይዘቶች መግለጫ**

.../

| ተራ ቁ. | አበይ የትምህርት ዓላማ | የመለመጃ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂል | 4 | 3.3 |
| 2 | የመናገር ክሂል | 6 | 5.0 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 41 | 34.1 |
| 4 | የመጻፍ ክሂል | 8 | 6.7 |
| 5 | የሥነ ልሳን ትምህርት | 38 | 31.7 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 11 | 9.1 |
| 7 | የመናገር/መጻፍ ክሂል | 2 | 1.6 |
| 8 | የሥርዓተ — ነጥብ አጠቃቀም | 3 | 2.5 |
| 9 | ልዩ ልዩ የትምህርት ይዘቶች | 7 | 5.8 |
| | ድምር | 120 | 100 |

ከሠንጠረዡ ላይ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የንባብ ክሂል ከሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የበለጠ ነጥብ ተሰጥቶታል:: ለሌሎችም ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የተሰጧቸውን የቁጥር ብዛት ሰንጠረዡ ያመለክታል::

ቀደም ሲል በመርሀ ትምህርቱ ላይ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለሰዋሰው ትምህርት መሆኑን አይተናል:: አሁን ደግሞ የመማሪያ መጽሀፉን መለመጃዎች ይዘቶች ስንመለከት የበለጠ ትኩረት የተሰጠው ለንባብ ክሂል ነው:: ይህም በሁለቱም መማሪያዎች ላይ ከሁለቱ በስተቀር ለሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የተመጣጠነ ግምት አለመሰጠቱን ያሳያል:: በሌላ አባባል በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ላይ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለሰዋሰው ትምህርት ሲሆን የመማሪያ መጽሀፉ የመለመጃዎች ይዘቶች ትኩረት በንባብ ክሂል ላይ ነው:: ከዚህም የመርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሀፉ የትኩረት አቅጣጫ የተለያየ መሆኑን እናያለን::

በተጨማሪም በአንዱ መጽሀፍ ላይ የተገለፀው አበይ የትምህርት ርእስ በሌላው መጽሀፍ ላይ አለተገለፀም:: ለምሳሌ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተገለፀው የቤተመጻህፍት አጠቃቀም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አልተመለከተም:: ከነዚህም በመማሪያ መጽሀፉ ላይ በመወከል ሀ

የተገለፀው የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም በመርሀ ትምህርቱ ላይ ምንም ቦታ አለተሰጠውም:: ይህም ሀሉቱ መማሪያዎች ለተለያዩ ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የተመጣጠነ ቦታ አለመስጠታቸውንና የሁለቱ ግንኙነት የሰፋ መሆኑን ይጠቁማል::

<u>ሠንጠረዥ 10</u>፤ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ መለመጃዎች ይዘቶችና የመርሀ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች ግንኙነት መግለጫ

| ተራ ቁ | አቢይ የትምህርት ርዕስ | መርሀ ትምህርቱ/ሀ/ | የመማሪያ መጽሐፉ/ለ/ | $ሀ^2$ | $ለ^2$ | ሀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂለ | 1 | 4 | 1 | 16 | 4 |
| 2 | የመናገር ክሂለ | 0 | 6 | 0 | 36 | 0 |
| 3 | የማንበብ ክሂል | 4 | 41 | 16 | 1681 | 164 |
| 4 | የሥነ ለሳን ትምህርት | 5 | 38 | 25 | 1444 | 190 |
| 5 | የመጻፍ ክሂለ | 5 | 8 | 25 | 64 | 40 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 3 | 11 | 9 | 121 | 33 |
| 7 | የመናገር/መጻፍ ክሂለ | 0 | 2 | 0 | 4 | 0 |
| 8 | የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 9 | የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 1 | 7 | 1 | 49 | 7 |
| | ድምር | 19 | 120 | 77 | 3424 | 438 |

በተዛምዶ ስሌት (ስለተዛምዶ ስሌትና አተረጓጎም አባሪ <u>ለ</u> ይመለከቷል) የተገኘው ውጤት 0.5 ነው:: ይህ ውጤት <u>በ'ቲ' ቴስት</u> ሲፈተን መማሪያ መጽሀፉና መርሀ ትምህርቱ በ8 ግንኙነት የላቸውም:: ምክንያቱም <u>የ'ቲ' ወሰኘ ዋጋ</u> በ0.05 <u>የአጋጣሚ ደረጃና</u> በ8 <u>የነጻነት ደረጃ</u> መሆን የሚገባው 1.86 ሲሆን <u>የ'ቲ' ስሌት ዋጋ</u> 1.63 ነው:: የ'ቲ' ስሌት ዋጋ ከ'ቲ' ወሰኘ ዋጋ የሚያንስ በመሆኑ በመማሪያ መጽሀፉ በመሆኑም የ'ቲ' ስሌት ዋጋ ከ'ቲ' ወሰኘ ዋጋ የሚያንስ በመሆኑ በመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶችና በመርሀ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች መካከል ግንኙነት የለም:: ስለዚህ የ'ቲ' ፈተናው ውጤት መጽሀፉና መርሀ ትምህርቱ ለየብቻቸው መሆናቸውን አረጋግጧል::

**ሠንጠረዥ 11፣** የአሥረኛ ክ.ለ የአማርኛ ቋንቋ ወርሀ ትምህርት ይዘትና የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መግለጫ

| ተራ ቁ | አቢይ የትምህርት ርእስ | ወርሀ ትምህርቱ/ሀ/ | የመማሪያ መጽሐፉ/ለ/ | $ሀ^2$ | $ለ^2$ | ሀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሠ 1 | የማዳመጥ ክሂለ | 6 | 4 | 36 | 16 | 24 |
| 2 | የመናገር ክሂለ | 3 | 6 | 9 | 36 | 18 |
| 3 | የማንበብ ክሂለ | 10 | 41 | 100 | 1681 | 410 |
| 4 | የመጻፍ ክሂለ | 11 | 8 | 121 | 64 | 88 |
| 5 | የሥነ ለሳን ትምህርት | 14 | 38 | 196 | 1444 | 532 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 12 | 11 | 144 | 121 | 132 |
| 7 | የመናገር/መጻፍ ክሂለ | 0 | 2 | 0 | 4 | 0 |
| 8 | የቤተመጻህፍት አጠቃቀም | 2 | 0 | 4 | 0 | 0 |
| 9 | የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 0 | 3 | 0 | 9 | 0 |
| 10 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 11 | 7 | 121 | 49 | 77 |
| | ድምር | 69 | 120 | | 3424 | 1281 |

የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶችና የወርሀ ትምህርቱ ይዘቶች ግንኙነት በተዛምዶ ቀመር ሲሰላ 0.30 ይሆናል:: ይህ ግንኙነት በ'ቲ' ቴስት ሲፈተን 0.89 የ'ቲ'ስሌት ዋጋ ያስገኛል:: ይህም የመማሪያ መጽሐፉ መለመጃዎች ይዘቶችና ወርሀ ትምህርቱ ይዘቶች ግንኙነት እንደሌላቸው ያሳያል:: በዚህ መሠረት የመማር ማስተማሩ ሂደት በብዙ መንገድ ተጳክሟል ማለት ነው:: ምክንያቱም የወርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች አይመሳሰሉም ወይም አይጣጣሙ:: ወርሀ ትምህርቱ እንድናስተምር የሚያዘውን ይዘት መጽሀፉ ውስጥ አናገኝም፤ ወይም በመጽሀፉ ላይ የሰፈረው አቢይ ይዘት በወርሀ ትምህርቱ ላይ አለተገለፀም::

**ሠንጠረዥ 12፣** በአሥረኛ ክፍለ የአማርኛ ቋንቋ ወርሀ ትምህርትና ክንውኖችና የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መግለጫ

| ተራ ቁ | አቢይ የትምህርት ይዘት | ወርሀ [illegible] | የመማሪያ [illegible] | $ሀ^2$ | $ለ^2$ | ሀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂለ | 7 | 4 | 49 | 16 | 28 |

| ተራ ቁ | ! አቢይ የትምህርት ይዘት | መርሀ ትምህርቱ/ሀ/ | የመማሪያ መጽሀፉ/ለ/ | $ሀ^2$ | $ለ^2$ | ሀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የመናገር ክሂለ | 20 | 6 | 400 | 36 | 120 |
| 3 | የማንበብ ክሂለ | 38 | 41 | 1444 | 1681 | 1558 |
| 4 | የመጻፍ ክሂለ | 23 | 8 | 529 | 64 | 184 |
| 5 | የሥነ ለሳን ትምህርት | 91 | 38 | 8281 | 1444 | 3458 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 27 | 11 | 729 | 121 | 297 |
| 7 | የቤተ መጻህፍት አጠቃቀም | 3 | 0 | 9 | 0 | 0 |
| 8 | የመናገር/መጻፍ ክሂለ | 10 | 2 | 100 | 4 | 20 |
| 9 | የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ለዩ ለዩ የትምህርት ይዘቶች | 62 | 7 | 3844 | 49 | 434 |
| | ድምር | 281 | 120 | 15385 | 3424 | 6099 |

በተዘምደ ስሌት መሠረት የመርሀ ትምህርቱ ክንውኖችና የማስተማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት –0.4 ነው:: ይህ ውጤት በ'ቲ' ስሌት ሲሰላ –1.23 ይሆናል:: ይህም ከ'ቲ' ወሳኝ ዋጋ በታች በመሆኑ የመርሀ ትምህርቱ ክንውኖችና የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት እንደሌላቸው ያሳያል:: ለዚህ ዓይነቱ የተቃራኒ ግንኙነት መከሰት ምክንያቱ የክንውናቱና የይዘቶቹ ግንኙነት አለመቀራረብ ብቻ ሳይሆን በአንዱ መማሪያ ውስጥ የሚገኘው አቢይ የትኩረት ነጥብ በሌላው መማሪያ ውስጥ አለመኖር ነው:: ለምሳሌ የቤተ መጻህፍት አጠቃቀም በመርሀ ትምህርቱ ላይ ብቻ ሲገለፅ የሥርዓተ ነጥብ አገለገሉት የተገለፀው በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ብቻ ነው:: ይህም የሁለቱን መማሪያዎች ግንኙነት ከማቀራረብ ይልቅ የማለያየት ሁኔታን ያሳያል::

<u>ሠንጠረዥ 13፣</u> የአሥረኛ ክፍለ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ግምገማዎችና የመማሪያ መጽሀፉ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት መገለጫ

.../

| ተራ ቁ | አበይ የትምህርት ርዕስ | ወርሀ ትምህርቱ/ሀ/ | የመማሪያ መጽሀፉ/ለ/ | $ሀ^2$ | $ለ^2$ | ሀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሂለ | 4 | 4 | 16 | 16 | 16 |
| 2 | የመናገር ክሂለ | 6 | 6 | 36 | 36 | 36 |
| 3 | የማንበብ ክሂለ | 22 | 41 | 484 | 1681 | 902 |
| 4 | የመጻፍ ክሂለ | 27 | 0 | 729 | 64 | 216 |
| 5 | የሥነ ለሳን ትምህርት | 52 | 38 | 2704 | 1444 | 1976 |
| 6 | የሥነ ጽሁፍ ትምህርት | 29 | 11 | 841 | 121 | 316 |
| 7 | የመናገር/መጻፍ ክሂለ | 3 | 2 | 9 | 4 | 6 |
| 8 | የቤተ መጻህፍት አጠቃቀም | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 9 | የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 |
| 10 | ለዮ ለዮ የትምህርት ይዘቶች | 37 | 7 | 1369 | 49 | 259 |
| | ድምር | 180 | 120 | 6188 | 3424 | 37.30 |

በተዛምደ ቀመር ስሌት መሠረት የግንኙነቱ ዋጋ 0.4 ነው:: የዚህም ግንኙነት የ'ቲ' ስሌት ዋጋ 1.23 ነው:: ስለዚህ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ወርሃ ትምህርት ግምገማዎችና የክፍሉ የመማሪያ መጽሀፍ መለመጃዎች ይዘቶች ግንኙነት እንደሌላቸው መረዳት ይቻላል::

### 4.1.2 ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ክፍል የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ለተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ ያላቸውን ቅርበት ለማወቅ ተዘጋጅቶ ለመምህራንና ለተማሪዎች በታደላቸው መጠይቆች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ይተነተናሉ:: ትንታኔው በመጠይቆቹ መሠረትነት ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች በሚሉ ሁለት ርዕሶች ሥር በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ቀርበዋል::

#### 4.1.2.1 ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ትንታኔ

በተማሪዎቹ የተሞላው መጠይቅ 4 ክፍሎች ያሉት ሲሆን በነዚህ ክፍሎች [illegible]

24 ጥያቄዎች የተሰጡት ትንታኔዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል:: .../

### 4.1.2.1.1 በክፍል አንድ ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

ሠንጠረዥ 14፣ ስለተማሪዎች የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ

| ጾታ | | ዕድሜ በአማካይ | የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | ሴት | | አማርኛ | ኦሮምኛ | ጉራጌኛ | ትግርኛ | ወላይትኛ | አገውኛ | እንግሊዝኛ |
| 182 | 150 | 15.5 | 290 | 20 | 9 | 7 | 1 | 1 | 1 |

ክፍል አንድ የተማሪዎቹን ጾታ፣ ዕድሜና የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚመለከት ነው:: ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው የመለሱት ተማሪዎች ብዛት 332 ሲሆን መጠይቁ ከታደላቸው 340 ተማሪዎች አንፃር ሲታይ 97.6% የሚሸፍኑ ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ 182 ወንዶች ሲሆኑ 150 ሴቶች መሆናቸውን ከሰንጠረዡ ላይ የተመዘገበው መረጃ ያሳያል:: ይህ ቁጥር ጥናቱን ለማካሄድ መጠይቁን የሞሉና የመለሱ ተማሪዎች በቂ መሆናቸውን ያስረዳል:: በክፍል አንድ ለተጠየቁት ጥያቄዎች 8 ተማሪዎች ተገቢውን መረጃ አልሰጡም::

ዕድሜን አስመልክቶ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ አማካይ ዕድሜ 16.5 ነው:: በተገኘው መረጃ መሠረት የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ ወላይትኛ፣ ጉራጌኛ፣ አገውኛና እንግሊዝኛ ናቸው:: አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆነው ተማሪዎች ብዛት 290 (87.3%) በመሆኑ ብዙዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል::

### 4.1.2.1.2 በክፍል ሁለት የተማሪዎችን ፍላጎት በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

ተማሪዎቹ የአማርኛ ትምህርትን በሚገባ ለመከታተል እንዲችሉ የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ፍላጐታቸውን ማሟላት አለማሟላቱን ለማወቅ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ሠንጠረዠ 14 ይህንኑ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጐት እንዴት እንደገለፁት ያሳያል::

## ሠንጠረዥ 15፣ ፍላጎትን በሚመለከት የተማሪዎች መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ | ጥ ያ ቄ ዎ ች | አ ማ ራ ጮ ች[3] | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | % | ሠ | % |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ትገኛለህ/ትገኛለሽ? | 310 | 92.0 | 24 | 7.1 | 3 | 0.9 | – | – | – | – |
| 2 | ለአንደኛው ጥያቄ መልስህ /መልስሽ/ በፍፁም አለገኝም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | 14 | 4.2 | 6 | 1.8 | 12 | 3.6 | 8 | 2.5 | 4 | 1.0 |
| 3 | ለሁለተኛው ጥያቄ መልስህ /መልስሽ/ አማርኛን መማር ስለማለወድ ነው የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | 6 | 1.8 | 7 | 2.1 | 4 | 1.2 | 9 | 2.7 | 23 | 6.8 |
| 5 | ለስስተኛው ጥያቄ መልስህ /መልስሽ/ ምንም ምክንያት የለኝም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከሚከተሉት የትኛው ነው? | 8 | 2.4 | 22 | 6.5 | 22 | 6.5 | 15 | 4.5 | 13 | 3.9 |
| 9 | የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የክፍል ውስጥ ተሳትፍህን /ተሳትፍሽን/ የሚያመለክቱት እንዴት ነው? | 143 | 42.4 | 1 7 | 43.6 | 47 | 13.9 | – | – | – | – |

በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚካሄድበት ጊዜ 310 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዘውትረው እንደሚገኙ ያሳያል:: ይህም መጠይቁን ከመለሱት ተማሪዎች ብዛት አንፃር ሲታይ 92.0% የሚሸፍን በመሆኑ ብዙዎቹ ትምህርቱ በሚሰጥበት ክፍለ ጊዜያት እንደሚገኙ ያሳያል::

ሁለተኛው ጥያቄ መመለስ ያለበት ለአንደኛው ጥያቄ 'በፍፁም በክፍል ውስጥ አለገኝም' የሚለውን በመለሱ ተማሪዎች ነው:: ይሁን እንጂ ለአንደኛው ጥያቄ

. . . /

'በፍፁም አላገኘም' የሚለውን አማራጭ የመለሱ ተማሪዎች 3 ብቻ በመሆናቸው መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ብዛት ጋር ሲወዳደር ሁለተኛው ጥያቄ ምንም መልስ እንዳላገኘ መገመት ይቻላል::

የሶስተኛው ጥያቄ መልስ የሚመሰረተው በሁለተኛው ጥያቄ ላይ ነው:: ለሁለተኛው ጥያቄ 'አማርኛን መማር ስለማለወድ ነው' የሚለውን በመለሱ 14 ተማሪዎች መመለስ የሚገባ ጥያቄ ነው:: ይሁን እንጂ ሶስተኛውን ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች 49 ተማሪዎች ሲሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥ 23 ተማሪዎች አማርኛን መማር የሚጠሉበትን ምክንያት እንኳን እንደማያውቁ ሰንጠረዡ ላይ የሰፈረው መረጃ ያሳያል::

አምስተኛው ጥያቄ የሚመለሰው ከሶስተኛው ጥያቄ አንፃር ነው:: ሆኖም ለአምስተኛው ጥያቄ የተገኙት መልሶች ከተጠያቂዎቹ ብዛት ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ በመሆናቸው ከግምት ውስጥ የሚገቡ አይደሉም::

ለዘጠነኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች ብዙዎቹ አዎንታዊ ናቸው:: በሰንጠረዡ ላይ የሰፈረው መረጃ እንደሚያሳየው 143 ተማሪዎች ምንባቦቹ ተሳትፏአቸውን የሚያመለክቱት አያስደስቱዋቸው እንደሆኑና 147 ተማሪዎች ደግሞ ምንባቦቹ በመጠኑ አያስደስቱዋቸው እንደሚያሳትፏአቸው ያመለክታል:: ይህም የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ተማሪዎቹን አያስደስተ እንደሚያሳትፏአቸው ይጠቁማል::

<u>ሠንጠረዥ 16</u>፤ ስለመጽሀፉ ምንባቦች የተማሪዎች መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ | ጥ ያ ቄ ዎ ች | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | ሠ % | ሠ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ አማርኛን የምትማረው /የምትማሪው/ በምንድን ነው? | 39 | 11.6 | 124 | 36.8 | 53 | 15.7 | 111 | 32.9 | 10 | 3.0 |

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

| ተራ ቁ | ጥ ያ ቄ ዎ ች | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | % | ሠ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች አንብበህ ምን ያህል ትረዳ ለህ/ትረጃለሽ? | 78 | 23.1 | 124 | 36.8 | 104 | 30.9 | 31 | 9.2 | – | – |
| 7 | ለስድስተኛው ጥያቄ መልስህ /መልስሽ/ ምንም አልረዳም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | 6 | 1.8 | 19 | 5.6 | 22 | 6.5 | 16 | 4.7 | 19 | 5.6 |
| 8 | ከማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የሚተላለፉት መልእክቶች ፤ | 144 | 42.7 | 164 | 48.7 | 22 | 6.5 | – | – | – | – |
| 10 | መምህሩ በማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦችን ምን ያህል ይጠቀሙባቸዋል? | 187 | 55.5 | 142 | 42.1 | 8 | 2.4 | – | – | – | – |
| 11 | የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ይዘቶች፤ | 99 | 29.4 | 159 | 47.2 | 79 | 23.4 | – | – | – | – |
| 12 | የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች አዳዲስ ነገሮችን ምን ያህል ያስተምራሉ? | 99 | 29.4 | 170 | 50.4 | 69 | 20.5 | – | – | – | – |

በተራ ቁጥር 4 ሥር የቀረበው ጥያቄ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ በምን ዓይነት የትምህርት መርጃ መሳሪያ እንደሚጠቀሙ የሚጠይቅ ነው:: በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ተማሪዎች አማርኛን የሚማሩት በመማሪያ መጽሀፉ ነው:: መምህሩ አዘጋጅተው በሚያቀርቡት መማሪያ መሆኑን የመለሱት 32.9% ሲሆኑ፤ ውሉ በውሉ ከመማሪያ መጽሀፉ ውጭ ነው ያሉት 3.0% ናቸው:: ይህም ለአማርኛ ትምህርት የመማሪያ መጽሀፉ በአብዛኛው በጥቅም ላይ እንደሚውል ያሳያል::

ተማሪያዎቹ ምንባቦቹን አንብበው ምን ያህል እንደሚረዱ ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ አንብበው እንደሚረዷቸው መለሰዋል:: 'ጥቂቶቹን እረዳለሁ' እና 'ምንም አልረዳም' የሚለውን መለሰ የሰጡት ተማሪዎች 40.1% ናቸው::

የሰባኛው ጥያቄ መልስ የሚመሰረተው በስድስተኛው ጥያቄ መልስ ላይ ነው:: ምንባቦቹን አንብበው ምንም እንደማይረዱ የመለሱ ተማሪዎች 9.2% ብቻ በመሆናቸው ከመላሾቹ ብዛት አንፃር ሰባተኛው ጥያቄ ሊታለፍ ይችላል::

ለስምንተኛው ጥያቄ 91.4% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከምንባቦቹ የሚተላለፉት መልእክቶች ግልጽነት ይጎድላቸዋል የሚለውን መልስ የሰጡት ተማሪዎች 6.5% ብቻ ናቸው:: በዚህ መረጃ መሠረት ከማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የሚተላለፉት መልእክቶች በመጠኑም ቢሆን ግልጽ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል::

ሐምሀሩ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ምን ያህል ይጠቀሙባቸዋል? ለሚለው አሥረኛው ጥያቄ፣ 'አብዛኛውን ጊዜ ነው' ያሉት ብዛት 55.5%፣ 'አልፎ አልፎ' ያሉት 42.1% ሲሆኑ 'በጭራሽ አይጠቀሙባቸውም' የሚለውን መልስ የሰጡት 2.4% ተማሪዎች መሆናቸውን ሰንጠረዥ 15 ላይ የሰፈረው መረጃ ያሳያል::

ተማሪዎቹ የማስተማሪያ መጽሀፉን ምንባቦች ይዘቶች ወቅታዊነት አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጥያቄ የመለሱት ምንባቦቹ ወቅታዊ እንደሆኑ በማመልከት ነው:: ምንባቦቹ ወቅታዊነት እንደሌላቸው የመለሱት መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 23.4% ብቻ ናቸው:: የተማሪዎቹ መልሶች የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ወቅታዊ መሆናቸውን ያሳያሉ::

በክፍል ሁለት ለተማሪዎቹ የቀረቡላቸው የመጨረሻው ጥያቄ 'የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች አዳዲስ ነገሮችን ምን ያህል ያስተምራሉ' የሚለው ነው:: ሠንጠረዥ 15 ላይ እንደተመለከተው ለዚህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ የሰጡት 20.5% ተማሪዎች ናቸው:: ብዙዎቹ ተማሪዎች /50.4%/ ምንባቦቹ አዳዲስ ነገሮችን በመጠኑ እንደሚያስተምሩ ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ /29.4%/ ተማሪዎቹ ደግሞ ምንባቦቹ በከፍተኛ ደረጃ አዳዲስ ነገሮችን እንደሚያስተምሩ መልሰዋል:: በአጠቃላይ ሲታይ መረጃው የሚጠቁመው አብዛኛቹ ተማሪዎች (79.8%) የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች አዳዲስ ነገሮች እንደሚያስተምሩ መመለሳቸውን ነው::

. . . /

4.1.2.1.3 በክፍል ስስት ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

በዚህም ክፍል በተለያዩ መመዘኛዎች በመጠቀም ተማሪዎቹ በማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ላይ ያላቸውን አስተያየት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል::

<u>ሠንጠረዥ 17፣</u> ፍላጎትን በሚመለከት የተማሪዎች መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ. | ጥ ያ ቄ ዎ ች | መ መ ዘ ኛ ዎ ች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መጠነኛ (መካከለኛ) | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 2 | የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ፍላጎትህን/ፍላጎትሽን የሚያሟሉበት ደረጃ፣ | 42 | 12.5 | 76 | 22.6 | 523 | 36.5 | 63 | 18.7 | 30 | 8.9 |
| 3 | የተለያዩ ምንባቦችን ለማንበብ ያለህ/ያለሽ/ ፍላጎት፣ | 160 | 47.5 | 88 | 26.1 | 51 | 15.0 | 25 | 7.4 | 12 | 3.6 |
| 4 | የመጽሀፉን ምንባቦች ለማንበብ ያለህ /ያለሽ/ ፍላጎት፣ | 89 | 26.4 | 98 | 29.1 | 94 | 27.9 | 30 | 8.9 | 25 | 7.4 |
| 12 | የመጽሀፉ ምንባቦች የማንበብ ፍላጎትህን /ፍላጎትሽን/ የሚያነሳሱትና የሚያበረታቱበት ደረጃ፣ | 76 | 22.6 | 82 | 24.3 | 87 | 25.8 | 57 | 16.9 | 35 | 10.4 |

ሠንጠረዥ 17 የሚያመለከተው የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት በማሟላት ረገድ ያለውን ብቃት ለማወቅ የቀረቡትን 4 ጥያቄዎች ነው:: ለጥያቄ 2 የተሰጡት ብዙዎች መልሶች እንደሚያመለከቱት የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት በመካከለኛ ደረጃ እንደሚያሟሉ ነው:: ለጥያቄው 'ዝቅተኛ' እና 'በጣም ዝቅተኛ' የሚሉ መልሶች የ መለሱት ከሌሎቹ አማራጮች አንፃር ሲታዩ ጥቂት ናቸው:: በሌላ አባባል የመጽሀፉ ምንባቦች የተማሪዎቹን ፍላጎት ለያሟሉ እንደሚችሉ ከተማሪዎቹ የተገኙት መረጃዎች ያረጋግጣሉ::

. . ./

ለስስተኛውና ለአራተኛው ጥያቄዎች ከቷሚሪዎቹ መልሶች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ተማሪዎቹ የተለያዩ ምንባቦችን ለማንበብ ፍላጎትና ጉጉት እንዳላቸው ብዙዎቹ (88.6%) አረጋግጠዋል:: እንደዚሁም የመጽሀፉን ምንባቦች ለማንበብ ፍላጎት እንዳላቸው ብዙዎቹ (83.4%) ተማሪዎቹ መልስ ሰጥተዋል:: ይህ ማለት ግን ለሁለቱ ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች ቁጥር እኩል ነው ማለት አይደለም:: የተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሀፉን ምንባቦች የማንበብ ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም ሌሎች ምንባቦችን ለማንበብ ካላቸው ፍላጎት አንፃር ሲታይ በ5.2% ዝቅተኛ መሆኑን ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል::

የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የማንበብ ፍላጎትህን /ፍላጎትሽን/ የሚያነሳሱትና የሚያበረታቱበት ደረጃ ምን ያህል ነው? ' ለሚለው አሥራ ሁለተኛ ጥያቄ በርካታ ተማሪዎች ምንባቦቹ በከፍተኛ ደረጃ የማንበብ ፍላጎታቸውን እንደሚያነሳሱና እንደሚያበረታቱ አመልክተዋል:: ምንባቦቹ የንባብ ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱትና የሚያበረታቱት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን የመለሱት 27.3% ተማሪዎች ብቻ ናቸው::

<u>ሠንጠረዥ 18፡</u> ምንባቦቹ ለችሎታቸው ስላላቸው ቀረቤታ የተማሪዎች መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ. | ጥ ያ ቄ ዎ ች | መ መ ዘ ኛ ዎ ች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መጠነኛ/ መካከለኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 5 | የመጽሀፉ ምንባቦች ከችሎታህ/ከችሎታሽ/ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ያህል ነው? | 32 | 9.5 | 88 | 26.1 | 133 | 39.5 | 63 | 18.7 | 21 | 6.2 |
| 10 | የመጽሀፉ ምንባቦች የዓረፍተ ነገር አስካክ (ግልጽነት፡ ደብዛዛነት ...) ከችሎታህ/ከችሎታሽ/ ጋር የሚስማማበት ደረጃ፡ | 29 | 8.6 | 75 | 22.3 | 136 | 40.4 | 62 | 18.4 | 34 | 10.4 |

. . . /

| ተራ | ጥ ያ ቄ ዎ ች | መ መ ዘ ኛ ዎ ች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መጠነኛ/ መካከለኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 11 | የምንባቦቹ የክብደት ደረጃ /የቃላቱ አዲስነት የሀሳብ ጥልቀት .../ ምን ያህል ነው? | 49 | 14.5 | 77 | 22.8 | 106 | 31.5 | 68 | 20.8 | 37 | 11.0 |

የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር መቀራረብ አለመቀራረባቸውን ለማወቅ የቀረቡት በሠንጠረዥ 18 ላይ የተመለከቱት 3 ጥያቄዎች ናቸው:: ለ3ቱም ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች አዎንታዊ ናቸው:: እንደጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል 75.1%፣ 71.3% እና 68.8% ያህል ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከዚህ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የመማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር በከፍተኛ ደረጃ ቀረቤታ ወይም ተስማሚነት ያላቸው መሆናቸውን ነው::

<u>ሠንጠረዥ 19</u>፣ ምንባቦቹ ከዕድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት የተማሪዎች መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ. | ጥ ያ ቄ ዎ ች | መ መ ዘ ኛ ዎ ች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መጠነኛ/ መካከለኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 1 | የማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች ከዕድሜህ/ከዕድሜሽ/ ጋር የሚመጣጠኑበት ደረጃ፣ | 35 | 10.4 | 80 | 23.7 | 155 | 46.0 | 46 | 13.6 | 21 | 6.2 |
| 6 | ምንባቦቹ ከኑሮ ለምድህ/ለምድሽ እና ከአካባቢህ/ከአካባቢሽ ጋር ያላቸው ቀረቤታ ምን ያህል ነው? | 42 | 12.5 | 69 | 20.5 | 108 | 32.0 | 68 | 20.1 | 50 | 14.8 |
| 7 | ከማስተማሪያ መጽሀፉ ምንባቦች የሚገኘው ዕውቀት በተፈለገው አካባቢ ሁኔታና ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት ደረጃ ምን ያህል ነው? | 36 | 10.7 | 105 | 31.2 | 97 | 28.8 | 60 | 17.8 | 39 | 11.6 |

.../

ተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከዕድሜያቸው ጋር የሚመጣጠኑበት ደረጃ ለሚጠይቀው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች በከፍተኛ ደረጃ እንደሚመጣጠኑ ይመለከታሉ:: ለዚህ ጥያቄ /ለአንደኛው/ የተሰጡት አሉታዊ ምላሾች 19.8% ያህል ብቻ ናቸው:: ይህም አብዛኛቹ ተማሪዎች /80.1%/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦቹ ከዕድሜያቸው ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ያስረዳል::

ስድስተኛውና ሰባተኛው ጥያቄዎች ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ለምድና አካባቢ ያላቸውን ቀረቤታና ከምንባቦቹ የሚገኘው ዕውቀት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ የሚጠይቁ ናቸው:: ለስድስተኛው ጥያቄ 65.0% አዎንታዊ ምላሾች የተሰጡ ሲሆን ለሰባተኛው ጥያቄ ደግሞ 70.7% አዎንታዊ ምላሾች ተሰጥተዋል:: የሁለቱም ጥያቄዎች መልሶች፣ ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ የኑሮ ለምድና አካባቢ መካከለኛ ቀረቤታ እንዳላቸውና ከምንባቦቹ የሚገኘው እውቀትም በተፈለገው አካባቢ፣ ሁኔታና ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታሉ::

<u>ሠንጠረዥ 20፤</u> ስለምንባቦቹ ይዘትና ገለጻነት በተማሪዎች
**የተሰጡ መልሶች መግለጫ**

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍ ተኛ | % | መጠነኛ/ መካከለኛ | % | ዝቅ ተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 8 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ሕብረተሰቡ የሚገለገለባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች /ቅኔ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ተረትና ምሳሌዎች.../ ምን ያህል ይዘዋል? | 35 | 10.4 | 56 | 16.6 | 83 | 24.6 | 98 | 29.0 | 65 | 19.3 |
| 9 | የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የመልዕክት አቀራረብ /ምሳሌ አሰጣጥ፣የሃሳብ ዝርዝርነት./ገለጻነት ምን ያህል ነው? | 43 | 12.8 | 60 | 17.8 | 119 | 35.3 | 77 | 22.8 | 38 | 14.3 |

. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ሕብረተሰቡ የሚገለገለባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች ምን ያህል ይዘዋል ? ለሚለው ጥያቄ የተመለሱት መልሶች አዎንታዊ ናቸው:: ከሠንጠረዡ መመለከት እንደሚቻለው፣ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮች...

[illegible] 48.3% [illegible]

የወለሱት ደግሞ 51.8% ናቸው::

እንደዚሁም ለዘጠነኛው ጥያቄም የተሰጡት መልሶች አያንታዊ መሆናቸውን በሠንጠረዥ 20 የሠፈረው መረጃ ያሳያል:: 65.9% ተማሪዎች የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከፍተኛ ገለጻነት እንዳላቸው መለሰዋል::

4.1.2.1.4 በክፍል አራት ተማሪዎች የሰጡዋቸው አስተያየቶች

ይህ ተማሪዎች የራሳቸውን ነፃ አስተያየት የሚሰጡበት ክፍል ነው:: በሌሎች ክፍሎች ከቀረቡላቸው 24 ጥያቄዎች በተጨማሪ ስለመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የሚሰማቸውን ማንኛውንም ዓይነት አስተያየት እንዲሰጡ ዕድል የሚሰጥቸው ክፍል ነው::

በዚህ ክፍል በ6ቱም ናሙና ትምህርት ቤቶች ናሙና ተማሪዎች የተሰጡት አስተያየቶች በርካታ ቢሆኑም አስተያየት ያለሰጡ ተማሪዎች የበለጠውን ቁጥር ይዘዋል:: ከነዚህ አስተያየት ካለሰጡ ተማሪዎች በተጨማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ጋር ግንኙነት የሌላቸውን አስተያየቶች የሰጡ ተማሪዎችም አጋጥመዋል:: ቀሪዎቹ ተማሪዎች ደግሞ በክፍል ውስጥ የምንማረው ሌላ የምንፈተነው ሌላ /ፈተናውና ትምህርቱ አይገናኝም/፣ መጽሐፉ ከችሎታችን በታች ነው ፣ ምንባቦቹ ከለምዳችን ጋር ቀረቤታ የላቸውም፣ ተከታታይነት የሌላቸው ምንባቦች ናቸው፣ መጽሐፉ ጥሩ ነው፣ ምንባቦቹ ገለጻነትና ለበለድ ጽሑፎች ይጉድላቸዋል፣ መጽሐፉ ከባድ ቃላት ይበዙበታል፣ መምህሩ ደካማ ናቸው የሚሉና የመሳሰሉ አስተያየቶች በምሳሌነት የሚጠቀሱና ብዙ ተማሪዎች ያስፈሩዋቸው አስተያየቶች ናቸው::

አስተያየት የሰጡ ተማሪዎች በሙሉ ሳይጠቅሱ ያላለፉት በክፍል 3 በስምንተኛ ጥያቄ ከቀረበው ሃሳብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው አስተያየት ነው:: አስተያየቱ የመማሪያ መጽሐፉ ቅኔ ፣ ተረትና ምሳሌ ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮችና የመሳሰሉ የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች እንደሚጐድሉት ያስረዳል፣ የነዚህ ዘርፎች መጉደል አማርኛን የመማር ፍላጐታቸውን እንደቀነሰባቸው አስተያየት ሰጥተዋል:: በአጠቃላይ ሲታይ በክፍል አራት አስተያየታቸውን የሰጡት ተማሪዎች የመጽሐፉን ምንባቦች ጥሩነት

የሚቀበሉ ቢሆኑም ነብረተሰቡ የሚገለገልበቸው የቀንድ አጠቃቀም ዘርፎች ስላላካተቱ ሊታሰብበት እንደሚገባ አስረድተዋል::

#### 4.1.2.2. ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች

ለመምህራን የታደለው መጠይቅም 4 ክፍሎች አሉት:: በ4ቱ ክፍሎች መምህራኑ ለ26 ጥያቄዎች መለስና ተጨማሪ አስተያቶችንም እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል:: ከመጠይቁም መልሶችና ከመምህራን አስተያቶች የተገኙ መረጃዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ይቀርባሉ::

##### 4.1.2.2.1 በክፍል አንድ ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች ስለመምህራን አጠቃላይ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሲሆኑ የመምህራኑን ዕድሜ፣ የሥልጠና ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ በአሁኑ ጊዜ የሚያስተምሩትን የክፍለ ጊዜ ብዛት የሚጠይቁ ናቸው::

ሠንጠረዥ 21: በክፍል አንድ ከመምህራን የተገኙ አጠቃላየ መረጃዎች መግለጫ

| ጾታ | | የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነትና ሁኔታ | | | | | | የትምህርት ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን /በአማካይ/ | የክ/ጊዜ ብዛት /በአማካይ/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አ ቢ ይ | | | ን ዑ ስ | | | | | |
| ወንድ | ሴት | አማርኛ | እንግሊዝኛ | ፔዳጎጂ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | ዲግሪ | ዲኘሎማ | | |
| 13 | 4 | 15 | 1 | 1 | 2 | 1 | 11 | 6 | 14.9 | 19 |

ለመምህራን ከታደሉት 18 መጠይቆች መካከል 17 ተሞልተው ሲመለሱ አንድ መጠይቅ ሳይመለስ ቀርቷል:: ከመጠይቆቹ ተሰብስበው በሠንጠረዥ 21 ላይ የተመዘገቡት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት 13 ወንዶችና 4 ሴቶች በጥናቱ ተካተዋል:: መምህራኑ በሙሉ አማርኛን የማስተማር ሥልጠና ያገኙ ሲሆኑ 11 የድግሪና 5 የዲኘሎማ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆኑን ከሠንጠረዡ መመልከት ይቻላል:: መረጃው እንደሚጠቁመው አማርኛን፣ እንግሊዝኛንና ፔዳጎጂን ዓቢይ

../

የትምህርት ወሰክ በማድረግ የሰለጠኑት እንደ ቅደም ተከተላቸው 5፣ 14፣ 1 ናቸው:: አማርኛን በንዑስ የትምህርት ወስክ ያጠኑት 2 መምህራን ናቸው:: የመምህራኑ የአገልግሎት ዘመን በአማካይ 14.9 ዓመት ሲሆን የያንዳንዱ መምህር አማካይ ሳምንታዊ የክፍለ ጊዜ ብዛት 19 መሆኑን መረጃው ያመለክታል::

4.1.2.2.2. በክፍል ሁለት ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች 5 ሲሆኑ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር ስላላቸው ግንኙነት የሚጠይቁ ናቸው::

ሠንጠረዥ 22: ፍላጎትን በሚመለከት የመምህራን መልሶች መግለጫ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | % | ሠ | % |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ይገኛሉ? | 16 | 94.1 | 1 | 5.9 | = | = | = | | = | = |
| 2 | ተማሪዎቹ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የማይገኙ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል? | = | = | 3 | 17.6 | = | = | = | | = | = |
| 8 | ተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ለማንበብ ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው? | 1 | 5.9 | 8 | 47.1 | 7 | 41.2 | | = | = = | = |
| 9 | ለሰምንተኛው ጥያቄ መለስዎ "ዝቅተኛ ነው" የሚል ከሆነ ከሚከተሉት ውስጥ ምክንያቱ የትኛው ነው? | 1 | 5.9 | = | = | 6 | 35.3 | | = | = | = |
| 10 | የመጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎቹን የክፍለ ውስጥ ተሳትፍ የሚያነሳሱት እንዴት ነው? | 2 | 11.8 | 14 | 82.4 | = | = | = | | = | = = |

ከላይ በሚገኘው ሠንጠረዥ ላይ የሰፈረት የአንደኛው ጥያቄ መለሶች፣ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደሚገኙ ያመለክታሉ:: በክፍል ውስጥ አይገኙም የሚለውን ጥያቄ የመለሱት አንድ መምህር /5.9%/ ብቻ ናቸው:: በዚህ መረጃ መሠረት ተማሪዎቹ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደሚገኙ መረዳት ይቻላል::

ሁለተኛው ጥያቄ የሚመለሰው በአንደኛው ጥያቄ ላይ ተመሥርቶ ነው:: ለአንደኛው ጥያቄ ሁለተኛው አማራጭ /በክፍል ውስጥ አይገኙም/ በመለስነት ከተመረጠ ጥያቄ ሁለት መልስ ማግኘት አለበት:: ለአንደኛው ጥያቄ ሁለተኛውን አማራጭ የመለሱት መምህር አንድ ብቻ ቢሆኑም ለሁለተኛው ጥያቄ የ3 መምህራን መልሶች ተመዝግበዋል:: የነዚህ 3 መምህራን መልሶች ተማሪዎቹ ቢማሩም ባይማሩም የአማርኛን ፈተና የሚያልፉ ስለሚመስላቸው በክፍል ውስጥ እንደማይገኙ ይጠቁማሉ:: ይሁን እንጂ ሁለተኛው ጥያቄ መመለስ ያለበት በአንድ ሰው ብቻ መሆን ስለሚገባው ጥያቄውን የመለሱት የ2ቱ መምህራን መልሶች ከግምት ውስጥ አይገቡም::

ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ለማንበብ ያላቸው ፍላጐት ምን ያህል ነው? ለሚለው ለስምንተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች እንደሚያመለክቱት የተማሪዎቹ ምንባቦቹን የማንበብ ፍላጐት መካከለኛ መሆኑን ነው:: ይሁን እንጂ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት መምህራን ቁጥርም የማናቅ አይደለም:: 41.2% መምህራን የተማሪዎቹ ምንባቦቹን የማንበብ ፍላጐት ዝቅተኛ መሆኑን የሚያመለክቱ መልሶች ሰጥተዋል:: ለዚህም የሰጡት ምክንያት ለዘጠነኛው ጥያቄ የቀረበውን "ተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብበው መረዳት ስለማይችሉ ነው" የሚለውን አማራጭ ነው::

ምንባቦቹ የተማሪዎቹን የክፍል ውስጥ ተሳትፍ የሚያመለክቱት እንዲት እንደሆነ ለማወቅ የቀረበው ጥያቄ በብዙዎቹ መምህራን /82.4%/ የተሰጡት መልሶች በመካከለኛ ደረጃ የሚያስደስቱ መሆናቸውን ያሳያል:: አያስደስቱዋቸው እንደሚያሳትፏቸው የመለሱት 11.8% መምህራን ናቸው::በአጠቃላይ ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት መልሶች የምንባቦቹ የማስደሰት ደረጃ መካከለኛ መሆኑን ያመለክታሉ::

.../

ሠንጠረዥ 23: ስለምንባቦቹ አጠቃቀም የመምህራን መልስች መግለጫ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | % | ሠ | % |
| 4 | በክፍል ውስጥ አማርኛን የሚያስተምሩት በምንድን ነው? | 1 | 5.9 | 11 | 64.7 | 2 | 11.8 | 1 | 5.9 | = | = |
| 5 | ለአራተኛው ጥያቄ መልስዎ "ሠ" ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | = | = | = | = | = | = | = | = | = | = |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦቹ ምን ያህል ይጠቀሙባቸዋል? | 15 | 88.2 | 2 | 11.8 | = | = | = | = | = | = |
| 7 | ስድስተኛው ጥያቄ መልስዎ "ሠ" ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | = | = | = | = | = | = | = | = | = | = |

መምህራን የማስተማሪያ መጽሐፉንም ሆነ ምንባቦቹን እንደሚጠቀሙባቸው የመምህራኑ መልስች ያመለክታሉ:: በሠንጠረዥ 23 ላይ የሰፈረው መረጃ እንደሚያሳየው መምህራን የመማሪያ መጽሐፉን የሚጠቁሙት አብዛኛውን ጊዜ መሆኑንና ምንባቦቹንም ሙሉ በሙሉ እንደሚጠቀሙባቸው ነው:: በዚህ መረጃ መሠረት መጽሐፉም ሆነ ምንባቦቹ ለአማርኛ ማስተማሪያነት በአገልግሎት ላይ እንደሚውሉ መረዳት ይቻላል::

ሠንጠረዥ 24: ስለምንባቦቹ ይዘት፣ ክብደትና ምጣኔ ለተጠየቁት ጥያቄዎች ከመምህራን የተገኙ መልስች መግለጫ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | % | ለ | % | ሐ | % | መ | % | ሠ | % |
| 11 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ይዘቶች፣ | 3 | 17.6 | 11 | 64.7 | 2 | 11.8 | = | = | = | = |
| 12 | ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ዕድሜ ምን ያህል ይመጥናሉ? | 1 | 5.9 | 7 | 41.2 | 8 | 47.1 | = | = | = | = |
| 13 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የክብደት ደረጃ፣ | 1 | 5.9 | 13 | 76[illegible] | 1 | 5.9 | | | | |

ለአሥራ አን.ኛው ጥያቄ መለስ ከሰጡት 10 መምህራን መካከለ ብዙዎቹ /64.7%/ የመጽሐፉ ምንባቦችን ይዘቶች በመጠኑ ወቅታዊ መሆናቸውን የሚገለፁ መለሶች ሲሰጡ፣ 17.6% መምህራን ደግሞ የምንባቦቹ ይዘቶች ወቅታዊነት የሚያመለክቱ መለሶች መስጠታቸውን መረጃው ያሳያል::

ለአሥራ ሁለተኛው ጥያቄ የተሰጡት የመምህራን መለሶች አዎንታዊና አሉታዊ ሲሆኑ ለሁለቱም የተሰጡት መለሶች ተመሳሳይ ናቸው:: የተማሪዎቹን ዕድሜ በከፍተኛ ደረጃ ይመጥናሉ የሚለውን መለስ የመለሱት መምህራን 5.9%፣ በመጠነኛ ደረጃ ይመጥናሉ ያሉት 41.2% ሲሆኑ በዝቅተኛ ደረጃ መመጠናቸውን የመለሱት ደግሞ 47.1% ናቸው::

ለአሥራ ስስተኛው ጥያቄ የተሰጡት መለሶች እንደሚያመለክቱት የመጽሐፉ ምንባቦች የክብደት ደረጃ በመጠኑ አየጨመረ ይሄዳል የሚለው መለስ በአብዛኛቹ መምህራን /82.4%/ ተመለሷል::

4.1.2.2.3. በክፍል ስስት ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ትንተና በ13 ጥያቄዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለ13ቱም ጥያቄዎች 5፣5 ተመሳሳይ መመዘኛዎች ተሰጥተዋቸዋል:: መምህራኑ በነዚህ መመዘኛዎች በመጠቀም የመለሱዋቸው መለሶች ከነትንታኔያቸው ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ 25: ተማሪዎች ስለምንባቦቹ ያላቸውን አመለካከት በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች መምህራን የሰጡዋቸው መለሶች መግለጫ

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | መ መ ዘ ኛ ዎ ች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መካከለኛ መጠነኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
| 1 | ምንባቦቹ ተማሪዎቹን ለማስደሰት ያላቸው ብቃት፣ | | | 2 | 11.8 | 6 | 35.3 | 4 | 23.5 | 4 | 23.5 |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦቹ የቀረቡት ትምህርቶችና ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጎት የሚስማሙበት ደረጃ፣ | | | 4 | 23.5 | = | = | 8 | 47.1 | 2 | 11.8 |
| 13 | የመጽሐፉ ምንባቦች [illegible] የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳት ምን ያህል ያግዛሉ? | | | 1 | 5.9 | 7 | 41.2 | 3 | 17.6 | 5 | 29.[illegible] |

በዚህ ክፍል ምንባቦቹ በተማሪ ቹ ፍላጎት ላይ የሚያስከትሉትን ሁኔታ ለማወቅ የቀረቡት ጥያቄዎች 3 ናቸው::3ቱንም ጥያቄዎች የመለሱት መምህራን ቁጥር የተለያየ ነው:: አንደኛውን ጥያቄ የመለሱት መምህራን 16 ሲሆኑ በሁለቱም አቅጣጫ /አዎንታዊና አሉታዊ/ ተመሳሳይ ቁጥር ተመዝግቧል:: ምንባቦቹ ተማሪዎቹን ምን ያህል እንደሚያስደስቱ ያላቸው ብቃት "ከፍተኛና መካከለኛ ነው" ያሉት መምህራን ቁጥር 47.1% ሲሆን፣ "ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው" ያሉት ደግሞ 47.0% ናቸው:: በዚህ መረጃ መሠረት በአዎንታዊና አሉታዊ መልሶች መካከል ከግምት ውስጥ የሚገባ ለዩነት አይታይም::

ሦስተኛው ጥያቄ የተመለሰው በ14 መምህራን ሲሆን 23.5% መምህራን የምንባቦቹ ይዘቶችና ትምህርቶች ለተማሪዎቹ ፍላጐት የሚስማሙት በከፍተኛ ደረጃ ነው የሚሉ መልሶችን ሰጥተዋል:: 58.9% መምህራን ደግሞ የምንባቦቹ ትምህርቶችና ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጐት የሚስማሙት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መሆኑን አመልክተዋል:: ይህ መረጃ በምንባቡ የቀረቡት ትምህርቶችና ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጐት የሚስማሙት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ያሳያል::

ለአሥራ ስስተኛው ጥያቄ እንደ አንደኛው ጥያቄ ተመሳሳይ ውጤት ተገኝቷል:: በመረጃው መሠረት የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪዋቹን የማንበብ ፍላጐት ለማነሳሳት የሚችሉት በመካከለኛ ደረጃ ነው የሚለውን የመሰሉት መምህራን 47.1% ሲሆኑ በዝቅተኛ ደረጃ ነው ያሉት ደግሞ 47.0% ናቸው::

<u>ሠንጠረዥ 26:</u> ምንባቦቹ ለተማሪዎች ለምድ ስላላቸው ቀረቤታ የመምህራን መልሶች መግለጫ

.../

| ተራ ቁ | ጥ ያ ቄ ዎ ች | በጣም ከፍ ተኛ | % | ከፍተኛ | % | መካከለኛ መጠነኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅ ተኛ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ውስጥ የተሰጡት ምሳሌዎች ከተማሪዎቹ አከባቢና ልምድ ጋር ያላቸው ማንፃፃሮች | | | 1 | 5.9 | 11 | 64.7 | 3 | 17.6 | 2 | 11.8 |
| 5 | የመጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ የቋንቋ ልምድ ያላቸው ቀረቤታ፣ | | | 6 | 35.3 | 8 | 47.0 | 3 | 17.6 | | |
| 7 | የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ አከባቢና ሁኔታ አስማሙ የሚችሉ የይዘት ለዩነቶች የያዙበት ደረጃ፣ | | | 3 | 17.6 | 3 | 17.6 | 7 | 41.2 | 4 | 23.5 |

የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ልምድ ጋር ያላቸውን ቅርበትና ግንኙነት ለማወቅ የቀረቡት ጥያቄዎች 3 ናቸው:: ለአራተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች እንደሚያመለክቱት በምንባቦቹ ውስጥ የተሰጡት ምሳሌዎች ከተማሪዎቹ አከባቢና ልምድ ጋር ያላቸው ግንኙነት በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን የሚጠቁም ነው:: ለተማሪዎቹ የቋንቋ ልምድ ያላቸው ቀረቤታም ከፍተኛና /35.3%/ መካከለኛ /47.0%/ መሆኑን ለአምስተኛ ጥያቄ ተሰጥቶ በሠንጠረዥ 26 ላይ የሰፈረው መረጃ ያመለክታል:: በአጠቃላይ ለሁለቱም ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ አከባቢና የቋንቋ ልምድ ጋር ያላቸው ግንኙነት መካከለኛ ነው::

በአንጻሩ ለሰባተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች ምንባቦቹ የይዘት ለዩነትየያዙበት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል:: ምንባቦቹ የተለያየ ዕድሜና ፍላጎት ላላቸው፣ የአከባቢና የሁኔታዎች ለዩነት ለሚታይባቸው ተማሪዎች ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉ የይዘት ለዩነቶች አለመያዛቸውን በሠንጠረዥ 26 ላይ ከሰፈረው መረጃ መገንዘብ ይቻላል::

ሠንጠረዥ 27 : ስለምንባቦቹ ግለፅነት፣ ምጥኑና ይዘት ለቀረቡ ጥያቄዎች የመምህራን መልሶች መግለጫ

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መካከለኛ መጠነኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የግልፅነት ደረጃ ፤ | | | 10 | 58.8 | 7 | 41.2 | | | | |
| 6 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ክሂሎችን/ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብን፣ መጻፍን/አመጣጥነው የሚያቀርበበት ደረጃ፣ | | | 6 | 35.3 | 4 | 23.5 | 6 | 35.3 | 1 | 5.9 |
| 8 | ምንባቦቹ ሕብረተሰቡ የሚገለገል ባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች /ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌ፣ ግጥም../ ምን ያህል ነው? | | | 1 | 5.9 | 4 | 23.5 | 3 | 17.6 | 9 | 52.9 |
| 9 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የመልዕክት አቀራረብ/ምሳሌ አሰጣጥ፣ የሃሣብ ዝርዝርነት፣../ ግልፅነት ምን ያህል ነው? | 1 | 5.9 | 4 | 3.5 | 11 | 64.7 | 1 | 5.9 | | |

በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስለሚገኙ ምንባቦች ሁኔታ ለማወቅ 4 ጥያቄዎች ለመምህራን ቀርበዋል:: የምንባቦቹን የግልፅነት ደረጃ ለሚጠይቁት ለሁለተኛና ዘጠነኛ ጥያቄዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 58.8% ና 94.1% መምህራን ከፍተኛና መካከለኛ ግልፅነት እንዳላቸው ሲያመለክቱ፤ 41.2% ና 5.9% መምህራን ደግሞ የመካከለኛና የዝቅተኛነት ደረጃ አዎንታዊ ምላሽ እንደተሰጠው ያሳያል:: እንደዚሁም መምህራኑ ስድስተኛውንም ጥያቄ የመለሱት በአዎንታዊ ነው:: ምንባቦቹ የተለያዩ ክሂሎችን የሚያቀርቡት በመካከለኛ ደረጃም ቢሆን አመጣጥነው እንደሆነ ከመምህራኑ የተገኙ መልሶች ያስረዳሉ::

መምህራኑ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ለስምንተኛው ጥያቄ ነው:: ስምንተኛው ጥያቄ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ኅብረተሰቡ የሚገለገልባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች

.../

/ቅኔ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮች..../የያዙት ምን ያህል እንደሆነ የሚጠይቅ ነው:: ለዚህ ጥያቄ 70.5% መምህራን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን የሚያመለክቱ መልሶችን ሰጥተዋል::

<u>ሠንጠረዥ 28:</u> ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ለተጠየቁት ጥያቄዎች መምህራን የሰጧቸው መልሶች

| ተራ ቁ. | ጥ ያ ቄ ዎ ች | በጣም ከፍተኛ | % | ከፍተኛ | % | መካከለኛ መጠነኛ | % | ዝቅተኛ | % | በጣም ዝቅተኛ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የዓረፍተነገር አስከክ/ግልፅነት፣ ደብዛዛነት፣../ጋር ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ምን ያህል ይመጥናል? | | | 7 | 41.2 | 7 | 41.2 | 3 | 17.6 | | |
| 12 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ምን ያህል ያሰድጋሉ? | | | 1 | 5.9 | 7 | 41.2 | 8 | 47.0 | 1 | 5.9 |

በዚህ ሠንጠረዥ ላይ ለሰፈሩት ሁለት ጥያቄዎች ተቃራኒ መልሶች ተመዝግበዋል:: አስረኛው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሲያገኝ፣ አሥራ ሁለተኛው ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ አግኝቷል:: በዚህም መሠረት አሥረኛው ጥያቄ በ41.2% መምህራን "ከፍተኛ ደረጃ" ና በ41.2% መምህራን "መካከለኛ ደረጃ" የሚል መልስ አግኝቷል:: ይህም መምህራኑ የምንባቦቹ የዓረፍተነገር አስከክ ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር የሚስማማበት ደረጃ መካከለኛ መሆኑን እንዳመለከቱ ያሳያል:: ለአሥራ ሁለተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች እንደሚያመለክቱት 52.9% የሚሆኑ መምህራን ምንባቦቹ የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ብቻ እንደሚያሳድጉ መረዳት ይቻላል::

### 4.1.2.2.4. በክፍል አራት ከተሰጡት የመምህራን አስተያየቶች የተገኙ መረጃዎች

በክፍል አራት መምህራን በቀደሙት ሁለት ክፍሎች /ክፍል ሁለትና ሶስት/ ከቀረቡት 26 ጥያቄዎች [illegible] ስለምንባቦቹ [illegible] ስለተማሪ መጽሐፍ [illegible]

አስተያየት እንዲሰጡ ሚጋብዝ ነው:: በዚሁ መሠረት ብዙዎቹ መምራን የራሳቸውን ነፃ አስተያየት ሲሰጡ 3 መምህራን ደግሞ መጠይቁን ሳይሞሉ መለሰዋል:: መምህራን ከሰጡዋቸው አስተያየቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣

=ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ገጠመኞች ጋር ተቀራራቢነት የላቸውም፣ ለተማሪው ዕድሜ፣ አካባቢና ለምድ የተመጠኑ ይዘቶች በምንባቦቹ ውስጥ አይገኙም፣

- የማስተማሪያ መጽሐፉ ለብወለዶች፣ ቀኒዎች፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችና የመሳሰሉት ይጐድሉታል፣ በዚህም ምክንያት የተማሪዎቹን የመማር ፍላጐት አይስብም፣ ለመማርም አያጓጓም፣

- በተለያዩ ስለቶችና የጥናት ዘዴዎች የተገኙ ምርምራዊና ጥናታዊ ውጤቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባልመረ፣

- የመምህሩ መምሪያ ባለመኖሩ ለአንድ ዓይነት ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ስለሚሰጡ የመምህሩ መምሪያ ቢዘጋጅ፣

- ምንባቦቹና ከምንባቦቹ የሚከተሉት መልመጃዎች ግንኙነት የላቸውም፣

- በዘጠነኛ ክፍል የተሰጡ የመማሪያ ርዕስ ጉዳዮች /ለምሳሌ ደብዳቤ/ ያለምንም ልዩነት ተደጋግመው ስለሚቀርቡ ተማሪዎቹን ያሰለቻሉ፣ የአሥረኛን ክፍል ጊዜም እንዲጠሉ ያደርጓቸዋል፣

- ከየምንባቡ በኋላ አስፈላጊነት ያላቸው መመሪያዎች አይሰጡም፣

- የሰዋሰውን ትምህርት ለማስተማር የሚረዱ መመሪያዎችና ሰዋሰዋዊ የትምህርት ይዘቶች ተሟልተው አልቀረቡም::

ከመምህራኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች አጠቃላይ ይዘቶች ከላይ የተገለፁት ፍሬ ሃሣቦች የሚመስሉ ሲሆን የነዚህ ሁኔታዎች ተስተካክሎ መቅረብ የምንባቦቹን የይዘት ሁኔታ እንደሚያሻሽል ጠቁመው በዚህም መሻሻል ምክንያት ተማሪዎቹ በፍላጐትና በስሜት ቋንቋውን ለመማር እንደሚያነሳሳቸው አምነታቸውን ገልፀዋል::

. . . ./

### 4.1.3. ከተነባቢነት ቀመሮች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የምንባቦችን ተነባቢነት ለመለካት ከሚያገለግሉ ቀመሮች መካከል ለዚህ ጥናት ባለቸው ተገቢነት የተመረጡት ሁለት ቀመሮች ሲሆኑ እነሱም የፍለሽ ቀመርና የፍሪ ግራፍ ናቸው:: በዚህ ንዑስ ክፍል በነዚህ ሁለት ቀመሮት በመጠቀም የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው ይተነተናሉ::

#### 4.1.3.1. ከፍለሽ ቀመር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የሚከተለው ሠንጠረዥ በፍለሽ ቀመር ስሌት የተገኘውን ውጤት ለመተንተን የሚያገዝ ሠንጠረዥ ነው:: /ለቀለም አቆጣጠር አባሪ ሠ ይመለከቷል/::

ሠንጠረዥ 29: በፍለሽ ቀመር መሠረት የተገኘው የስስቱ ናሙና ምንባቦች ውጤት መግለጫ

| ናሙና ምንባቦች | የቀለሞች ብዛት | በ100 ቃላት የዓ.ነገሮች ብዛት | በዓ.ነገር አማካይ የቃላት ብዛት | የንባብ ቅለት ነጥብ | ናሙናዎቹ የተገመቱለት ክፍል | አማካይ የቃላት ነጥብ | መጽሐፉ የተገመቱለት ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 290 | 6 | 16.7 | -55.1 | ከድህረ ምረቃ በላይ | -51.5 | ከድህረ-ምረቃ በላይ |
| 2 | 269 | 12.1 | 8.3 | -29.2 | " | | |
| 3 | 313 | 8.3 | 12.0 | -70.1 | " | | |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የያንዳንዱ ናሙና ምንባብ የቅለት ነጥብ ውጤት እንደቅደም ተከተላቸው -55.1፣ -29.2፣ እና -70.1 ነው:: ይህም በቀመሩ ውጤት አተረጓጎም አንጻር ሲታይ ምንባቦቹ በተናጠል ሲተረጐሙ ለድህረ ምረቃና ከድህረ ምረቃ በታች ለሚገኙ የክፍል ደረጃዎች የሚመጥኑ አይደሉም:: ምንባቦቹ ለፍለሽ ቀመር ውጤት አተረጓጎም እንዲረዳ ተብሎ ከተዘጋጀው የክብደት ደረጃ መለኪያ/መመዘኛ ነጥብ በላይ ሆነው ይገኛሉ:: የቀመሩን ውጤት አተረጓጎም በሚያሳየው ሠንጠረዥ መሠረት / ሠንጠረዥ 4 ገጽ 46 "በጣም ከባድ" የሚባለውና ለድህረ ምረቃ ደረጃ ይሆናል ተብሎ የተገመተው የንባብ ቃለት ነጥብ ከ0-29 መሆን አለበት:: ከዚህ አተረጓጎም አንጻር የናሙናዎቹ የንባብ ቅለት ነጥብ የክብደት ደረጃ ከሚታሰበው በላይ ነው::

የ3ቱ ናሙና ምንባቦች አማካይ የቅለት ነጥብ -51.5 መሆኑንም ሠንጠረዥ 27 ያመለክታል:: ከ3ቱ ናሙናዎች የሚገኘው አማካይ ውጤት የመጽሐፉን የክብደት ደረጃ የሚያሳይ ነው:: በዚህ መሠረት ይህ አማካይ ውጤት መጽሐፉ ለአሥረኛ ክፍል ቀርቶ ለድህረ ምረቃ የትምህርት ደረጃ እንኳን እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን ያስረዳል::

4.1.3.2. የፍሪ ግራፍ ውጤት ትንታኔ

የፍሪ ግራፍ የሁለተኛ ደረጃ ማስተማሪያ ምንባብ ተነባቢነትን ለመለካት ከሚያገለግሉ መሣሪያዎች አንዱ ነው:: የፍሪ ግራፍ ውጤት ለመተንተን የሚያስችሉን 2ቱ መሠረታዊ ሃሣቦች የቃልና የዓ.ነገር ርዝመት የሚመለከቱ ናቸው::

የዓ.ነገር ርዝመት የሚገለፀው በ3ቱ ባለ100 ቃላት ናሙና ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን የዓ.ነገር ብዛት በመቁጠር ድምር ለ3 በማካፈልና አማካይ በማውጣት ነው:: የቃል ርዝመትም የሚገለፀው በ3ቱ ባለ100 ቃላት ናሙናዎች ውስጥ የሚገኙትን የቀለሞች ብዛት ቆጥርና ድምር ለ3 በማካፈል በሚገኝ አማካይ ውጤት ነው::

የዓ.ነገርና የቃል ርዝመት በምንባብ ተነባቢነት ላይ ተጽዕና አላቸው:: የፍሪ ግራፍ፣ አጭር ዓ.ነገሮችና ቃላት ከረዛዥም ዓ.ነገሮችና ቃላት በበለጠ ለግንዛቤ አመቺ መሆናቸውን፣ ወይም ለመረዳት የማይከብዱ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባል:: ሠንጠረዥ 30 ናሙና ምንባቦቹ በፍሪ ግራፍ ተለክተው የተገኙትን የዓረፍተ ነገርና የቃል ርዝመት፣ እንደዚሁም ናሙና ምንባቦቹ የተገመቱለትን የክፍል ደረጃ ያመለክታል:: የተገመተውን የክፍል ደረጃ ለማወቅ የ3ቱን ናሙና ምንባቦች አማካይ የቃልና የዓ.ነገር ርዝመት በፍሪ ግራፍ ላይ ማስፈር ያስፈልጋል:: /ስለፍሪ ግራፍ አባሪ ሀን ይመለከቷል/

.../

ሠንጠረዥ 30: የናሙና ምንባቦቹ የቀለም ብዛት፣ የዓ.ነገር ርዝመትና የተገመቱለት የክፍል ደረጃ

| ናሙና ምንባቦች | የቀለም ብዛት | የዓ.ነገር ብዛት | ለናሙናዎቹ የተገመተው የክፍል ደረጃ | የቀለም ብዛት /አማካይ/ | የዓ.ነገር ርዝመት /አማካይ/ | ለመጽሐፉ የተገመተው የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 290 | 6 | 17⁺ በላይ | 290.7 | 8.8 | 17⁺ በላይ |
| 2 | 269 | 12.1 | " " | | | |
| 3 | 313 | 8.3 | " " | | | |

በሠንጠረዡ ላይ የተመዘገቡትን የያንዳንዱን ናሙና ምንባብ የዓ.ነገርና የቃል ርዝመት በፍሪ ግራፍ ላይ ብናሰፍር ከ17⁺ በላይ የሆነ የክፍል ደረጃ እናገኛለን:: ይህ ማለት የምንባቦቹ የክብደት ደረጃ 17ኛ ክፍል በላይ ያለ ሰው አንብቦ የሚረዳቸው ናቸው ማለት ነው:: በሌላ አባባል ናሙናዎቹን ምንባቦች ከ17⁺ የክፍል ደረጃ በታች ያለ ተማሪ አንብቦ መረዳት አይችልም::እንደዚሁም የ3ቱን አማካይ ውጤት በግራፉ ላይ ብናሰፍር የምናገኘው ውጤት ለያንዳንዱ ናሙና ምንባብ ከተገመተው የክፍል ደረጃ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል:: የሶስቱም አማካይ ውጤት የሚያሳየው የመጽሐፉን የክብደት ደረጃ ነው::

የናሙናዎቹም ሆነ የመጽሐፉ የክብደት ደረጃ ይህን ያህል ከባድ ሊሆን የቻለበት 2 ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ከነዚህ አንደኛው ምክንያት በ100 ቃላት ውስጥ የሚገኙት የቀለሞች ብዛት ከፍተኛ መሆኑ ነው:: የቀለሙ በዝቶ መገኘት የቃላቱን ርዝመት የሚወስን ነው:: በፍሪ ግራፍ ገፃት ደግሞ የቀለም መብዛት የምንባቡ የክብደት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ከገፃት ውስጥ ያስገባል:: እንደዚሁም የዓ.ነገር ርዝመት የምንባቡን የክብደት ደረጃ ከፍተኛ እንደሚያደርገው የፍሪ ግራፍ ገፃት ነው:: በነዚህ 2 ምክንያቶች የናሙና ምንባቦቹም ሆነ የመማሪያ መጽሐፉ የተገመቱለት የክፍል ደረጃ 17⁺ በላይ ሆና ተገኝቷል::

.../

### 1.1 4. ከገንዘቤ ሙከራ የተገኙ ውጤቶች

የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መጽሐፋቸውን ምንባቦች መረዳት መቻላቸውን ለመገመት 3 ምንባቦች ከመማሪያ መጽሐፉ መጀመሪያ፣ መካከለና መጨረሻ ተወስደው ከአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተመረጡ የ6 ናሙና ትምህርት ቤቶች 90 ተማሪዎች በፈተና መልክ ተሰጥተዋል:: /ለገንዘቤ ሙከራው ውጤት አባሪ ሸን ይመለከቷል/:: የሙከራው ውጤት ከታወቀ በኋላ ተማሪዎቹ ባገኙት ውጤት መሠረት በጥንቀት፣ በአርዳታና በገለ የማንበብ ደረጃ ለመለየት የያንዳንዱ ናሙና ውጤት የድግግሞሽ ሥርጭት እንደሚከተለው ተሰልቷል::

ሠንጠረዥ 31: የናሙና ተማሪዎች የገንዘቤ ሙከራ ውጤት የድግግሞሽ ሥርጭት ( Friquency distribution)

| የናሙና ተማሪዎች ውጤት | ድ ግ ግ ሞ ሽ | | |
|---|---|---|---|
| | ናሙና አንድ | ናሙና ሁለት | ናሙና ሶስት |
| 70 – 76 | 0 | 1 | 0 |
| 63 – 69 | 0 | 0 | 0 |
| 56 – 62 | 0 | 0 | 0 |
| 49 – 55 | 0 | 3 | 0 |
| 42 – 48 | 11 | 7 | 0 |
| 35 – 41 | 8 | 6 | 4 |
| 28 – 34 | 20 | 20 | 17 |
| 21 – 27 | 19 | 16 | 16 |
| 14 – 20 | 16 | 22 | 38 |
| 7 – 13 | 11 | 10 | 11 |
| 0 – 6 | 5 | 5 | 4 |
| ድምር | 90 | 90 | 90 |
| አማካይ ውጤት | 25.2 | 25.2 | 20.3 |

የናሙና ምንባቦቹ ውጤት የድግግሞሽ ሥርጭት እንደሚያሳየው ለናሙና አንድ 25.2፣ ለናሙና ሁለት 25.2 እና ለናሙና ሶስት 20.3 አማካይ ውጤቶች ተመዝግበዋል:: ለገንዘቤ ሙከራ በተሰጠው የአተረጓጎም ሠሌዳ መሠረት የተማሪዎቹ አንበብ የመረዳት

.../

ደረጃ በጥንቀት በሚያነቡበት ደ.ጃ ላይ ይገኛሉ:: ይህም ተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሐፋቸውን በመምህር እርዳታ እንኳን አንብበው መረዳት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ያሳያል::

ሠንጠረዥ 32: በየናሙና ትምህርት ቤቶች የናሙና ተማሪዎች የመረዳት ደረጃ

| ተራ ቁ. | የትምህርት ቤቱ ስም | ትምህርቱን መቀጠል የማይችሉ | | በድጋፍ የሚማሩ | | በግል የሚማሩ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | አየር ጤና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 21 | 100 | = | = | = | = |
| 2 | አዲስ ከተማ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 17 | = | = | = | = | = |
| 3 | ገንቦት ሃያ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 17 | 94.1 | 1 | 5.9 | = | = |
| 4 | አቃቂ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 13 | 84.6 | 2 | 15.4 | = | = |
| 5 | ወንድራድ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 13 | 100 | = | = | = | = |
| 6 | ኤስ ኦ ኤስ ከፍተኛ ሃያ ስስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | 9 | 88.9 | 1 | 11.1 | = | = |
| | **ድምር** | **90** | = | **4** | = | = | = |

ከሠንጠረዡ በመመለከት የ6ቱም ናሙና ትምህርት ቤቶች የአብዛኛዎቹ /95.6/ የገንዘቤ መከራ ናሙና ተማሪዎች ትምህርቱን መቀጠል ከማይችሉበት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል:: በመምህሩ ድጋፍ አንብበው መረዳት የሚችሉት ተማሪዎች 4.4% ብቻ ናቸው::

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

### 4.2.1 የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ ግንኙነት

የተገኘው መረጃና በግንኙነት ቀመር ስሌት የተመዘገበው ውጤት እንደሚያመለክተው የመጽሐፉ መለመጃዎች ይዘቶችና የመርሐ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች ፣ ክንውኖችና ግምገማዎች ግንኙነት የላቸውም።

እያንዳንዳቸው የመርሀ ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች /ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ግምገማዎች / ከመጽሐፉ መለመጃዎች ይዘት አንፃር በተናጠል ሲታዩ እንደቅደም ተከተላቸው 19፣69፣281ና 180 ሲሆኑ የመጽሐፉ ይዘት 120 ነው:: በሁሉም የመርሀ ትምህርቱ ክፍሎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የሰዋሰው የትምህርት ዘርፍ መሆኑን ከ5-8 ሠንጠረዦች ላይ የሰፈሩት መረጃዎች ያመለክታሉ:: የመጽሐፉን የመለመጃዎች ይዘት ለማመለከት የተዘጋጀው ሠንጠረዠ እንደሚያሳየው ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለንባብ ክሂል መሆኑን ነው:: ይህም በሁለቱ የማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ግንኙነት አለመኖሩን ያስረዳል:: ሌሎቹም ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች ሲነፃፀሩ የተሠጧቸው ሥርጭት የተመጣጠነ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል::

የመርሐ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች ክንውኖችና ግምገማዎች ከመጽሐፉ መለመጃዎች ይዘቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት በተዛምዶ ቀመር ሲሰላ 0.5፣ 0.3፣ -0.4፣ 0.4 ውጤቶች ተመዝግበዋል:: የተዛምዶ ስሌቱን ውጤቶች በ"ቲ" ቴስት ሲፈተኑ የመርሀ ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎችና የመለመጃዎቹ ይዘቶች ግንኙነት የላቸውም:: በተለይም ለመማር ማስተማር ሂደት የሁለቱ ግንኙነት መሳ ለመሳ ወይም እኩል በእኩል መሆን ሲገባው ከግምት ውስጥ የሚገባ ግንኙነት አለማሳየታቸው የመማር ማስተማሩን ውጤታማነት ሊጐዱ እንደሚችሉ በምዕራፍ ሁለት የሰፈሩት የምሁራን ትንታኔዎችና መረጃዎች /ከኒንገወርዝ፣ ግራንትና ዱቤን/ ያስረዳሉ::

በመሠረቱ የመርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ግኙነት እኩል መሆን ይገባዋል:: ይሁን እንጂ የተዘምደ ስሌቶቹ ዉጤት ፍቺነት የመማሪያ መጽሐፉ መለመጃዎች ይዘቶችና የመርሀ ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ያሳያል:: ለሁለቱ ልዩነቶች መከሰት ምክንያቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ::

አንደኛው ምክንያት የማስተማሪያ መጽሐፉና የመርሀ ትምህርቱ የትኩረት አቅጣጫ የተለያየ መሆኑ ነው:: በመርሀ ትምህርቱ ላይ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለስዋስው የትምህርት ዘርፍ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ደግሞ ለንባብ ክሂል ነው::

ሌላው ምክንያት በአንዱ የመማሪያ መሣሪያ ውስጥ የሠፈረው አቢይ የትምህርት ዘርፍ በሌላኛው የትምህርት መሣሪያ ውስጥ አለመጠቀሱ ነው:: በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሥርዓተ ነጥብ አገልግሎት በትምህርትነት ሲቀርብ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ አለተካተተም:: እንደዚሁም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቤተ መጻሕፍት አጠቃቀም የተካተተ ሆና ሳለ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አለተወሰ ም::

ሦስተኛው ምክንያት በመርሀ ትምህርቱ ላይ ገለጸነት የጐደላቸውና በየትኛውም አቢይ የትምህርት ርዕስ ላይ መጠመር ያስቸግሩ ይዘቶች ብዛት ከፍተኛ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ግን ብዛታቸው አነስተኛ መሆኑ ነው::

ለመርሀ ትምህርቱና ለመጽሐፉ ግንኙነት መለያየት አራተኛው ምክንያት በመርሀ ትምህርቱ ላይ አሻሚ አጠያየቆች/ ይዘቶች ሲበዙ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ግን ቁጥራቸው አነስተኛ መሆናቸው ነው:: ለምሳሌ በመናገር ወይም በመጻፍ ሊመለሱ የሚችሉ ክንውኖች በመርሀ ትምህርቱ ላይ ከፍተኛ ሲሆኑ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ግን አነስተኛ ናቸው::

ከላይ የተጠቀሱት አራቱ ነጥቦች በሁለቱ መሣሪያዎች መካከል ግንኙነት

. . . /

እንዳይኖር ምክንያት ሆነዋል:: ይህም የመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀው መርሀ ትምህርቱን መሠረት አድርጐ እንዳልሆነ ያመለክታል:: በሌላ አባባል መርሀ ትምህርቱ ለመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት እንደምንጭነት አለማገልገሉን የተገኘው የስሌት ውጤት ያስረዳል::

## 4.2.2 የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦችና የተማሪዎች ፍላጐት

የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጐት ምን ያህል እንደሚያረኩ ለማወቅ በተደረገው ጥረት የተገኘው ውጤት አበረታች ነው:: ተማሪዎች በየመጠይቁ ክፍሎች የቀረቡትን ጥያቄዎች የመለሱት ምንባቦቹ ከፍላጐታቸው ጋር ሊስማሙ እንደሚችሉ ያስረዳል::

አማርኛን መማር ፍላጐት ስላላቸው በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ መገኘታቸው የመማሪያ መጽሐፉ ስለሚያስደስታቸው ነው:: ይህ ባይሆን ኖር ተማሪዎቹ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመማርያ ክፍሉ ውስጥ አይገኙም ነበር:: በክፍል ውስጥ መገኘት ብቻ ሳይሆን ምንባቦቹ አያስደስቱዋቸው ስለሚያሳትፏዋቸው በክፍል ውስጥ ተገኝተው በመማሪያ መጽሐፉ በመጠቀም ትምህርቱን ለመከታተል እንደሚጥሩ መልሶቻቸው ያመለክታሉ:: ትምህርታቸውንም የሚከታተሉት በመማሪያ መጽሐፉ ሲሆን፣ የመጽሐፉን ምንባቦች በሙሉ አንብበው ይረዳሉ:: የምንባቦቹ መልዕክቶች ግልጽ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አዳዲስ ነገሮችን ያስተምሩዋቸዋል:: በነዚህ መሰል ምክንያቶች ምንባቦቹ የተማሪዎችን ስሜት የመማረክ፣ ፍላጐታቸውን የማነሳሳት ትምህርቱን በፍላጐት የመማር ፍቅር እንዲያሳድርባቸው በክፍል ሁለት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡዋቸው መልሶች አረጋግጠዋል::

በክፍል ሦስት በቀረቡት ጥያቄዎችም የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ጥሩ እንደሆኑና ከፍላጐታቸውና ከዝንባሌያቸው ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል:: ተማሪዎቹ ምንባቦቹን የማንበብ ፍላጐት ያላቸው ቢሆንም የተለያዩ ምንባቦችን ለማንበብ ካላቸው

ፍላጐት በታች መሆኑም ታውቋል:: ምንባቦቹ የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጐትም እንደሚያነሳሱ መገንዘብ ተችሏል:: ምንባቦቹ ከትምህርቱ ተቀባዮች እድሜ፣ አካባቢና ለምድ ጋር ከፍተኛ የሆነ የመጣጣም ባሕርያት እንዳላቸውና የመልዕክት አቀራረባቸውም ግልጽነት ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ተችሏል:: የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ምንባቦቹ በተማሪዎቹ እንዲወደዱና የመማር ፍላጐት እንዳሳደሩባቸው በመልሶቻቸው አረጋግጠዋል::

በነፃ አስተያየታቸውም እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች አንፀባርቀዋል:: ምንባቦቹ ፍላጐታቸውን እንዲያሟሉላቸው፣ አቀራረባቸው ግልጽ እንደሆነ፣ የማንበብ ፍላጐታቸውን እንዲያነሳሱ፣ ከለምዳቸውም ሆነ ከዕድሜያቸው ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው መሆናቸውን በሰጧቸው አስተያየቶች ጠቁመዋል::

ከመጠይቆቹ ከተሰበሰቡት መረጃዎች አማርኛን የመማር ፍላጐታቸው ዝቅተኛ መሆኑን የገለፁ ተማሪዎችም አጋጥመዋል:: ፍላጐታቸው ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ውስጥ ቅኔ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ተረትና ምሳሌዎች ወዘተ በበቂ ሁኔታ አለመያዛቸው እንደሆነ አስረድተዋል:: እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች በተሟላ ሁኔታ በምንባቦቹ ውስጥ ቢካተቱ ኖሮ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጐት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ከአስተያየቶቻቸው መረዳት ይቻላል::

ይህ የመጨረሻው የተማሪዎች አስተያየት የመምህራንም አስተያየት ነው:: የመምህራኑ አስተያየት በጠቆመው መሠረት የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባቦች የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎችን ባለመያዛቸው የተማሪዎችን አማርኛ የመማር ፍላጐት በአጅጉ እንደጐዱት መረዳት ተችሏል:: ስለዚህ ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ፍላጐት እንዲስማሙና ቋንቋውን የመማር ዝንባሌያቸውን እንዲያዳብሩ ከተፈለገ እነዚህ ሕብረተሰቡ የሚገለገልባቸው የተለያዩ ስልቶች በምንባቡ ውስጥ ተሟልተው መገኘት ይገባቸዋል::

. . . :

ሌላው ከመምህራን መልሶች ሊተኮርበት የሚገባው በክፍል ሁለት የተመለከተው ዘጠነኛው ጥያቄ ነው:: የተማሪዎቹ ምንባቦቹን የማንበብ ፍላጎት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረገው የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አነስተኛ መሆን ነው:: ከመምህራን በዚህ መለክ የተመለሱት መልሶች አነስተኛች ቢሆኑም ወደፊት እንደምናየው የግንዛቤ ሙከራ ውጤት የመምህራኑን መልሶች የሚያጠናክር ሆና ተገኝቷል:: ምንም እንኳን ተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች አንብበው እንደሚረዱ ቢገልጹም፣ በግንዛቤ ሙከራ ውጤትና በመምህራን አስተያየቶች ሲገመገም የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው:: አንብቦ በመረዳት ተገቢውን መረጃ ከምንባቦቹ ውስጥ ማግኘት እንደሚችሉ በግንዛቤ ሙከራ ውጤት ተረጋግጧል::

ከዚህም በተጨማሪ የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት አያነሳሱም፣ እንደተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ልምድና የኑሮ ገጠመኝ የተለያየ የይዘት ልዩነቶችን አልያዙም:: በሌላ አባባል የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተለያዩ ዕድሜዎች፣ ልምዶችና ገጠመኞች የተለያዩ ይዘቶች የላቸውም:: ለሁሉም ገጠመኞች፣ ልምዶችና አካባቢዎች አንድ አይነት ይዘትና ደረጃ ያላቸው ምንባቦች ተመርጠው የቀረቡ በመሆናቸው ለተለያዩ ተማሪዎች ፍላጎት ተስማሚ ሆነው አልተገኙም:: ከዚህም የተነሳ ለተማሪዎቹ ችሎታ የተመጠኑ ሊሆኑ አልቻሉም፣ ለአንዳንዶቹ ይቀላሉ፣ ለሌሎቹ ደግሞ ይከብዳሉ:: ይህም የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ዝቅ ማድረጉ አልቀረም::

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሐሳቦች በስተቀር ከመምህራኑ ለሌሎች ጥያቄዎች የተሰጡት አስተያየቶችና መልሶች ለምንባቦቹ መካከለኛ ደረጃ ይሰጧሉ:: የምንባቦቹ የግልጽነት ደረጃ፣ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ልምድና አካባቢ ጋር ያላቸው ቅርበት ደረጃቸው፣ በምንባቦቹ የሚጠቀሙባቸው ደረጃ ፣ በሙሉ የመካከለኛነት ደረጃ ተሰጥቶቸዋል:: ይህም ሐሳብ ሲጠቃለል የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተማሪውን

ፍላጐት የሚያሟሉት በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን ያረጋግጧል::

### 4.2.3 የምንባቦቹ ተነባቢነት

ምንባቦች ተነባቢነት ከሌላቸውና ከአንባቢው ችሎታ ጋር ተቀራራቢነት ከጐደላቸው ለማስተማሪያነት ብቁ ስለማይሆኑ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባቦች ያላቸውን ተነባቢነት ብቃት ለመለካት ተሞክሯል::

ከፍለሽ ቀመር ስሌት በተገኘው ውጤት መሠረት ምንባቦቹ ተነባቢነት የላቸውም:: ሊገለጽ በማይችል ደረጃ ከባድ ምንባቦች ናቸው:: የፍለሽ ቀመር ውጤት አተረጓጐም እንደሚያሳየው "በጣም ከባድ" ነው የሚባለው የስሌቱ ውጤት ከ0-29 የሆነ ምንባብ ነው:: ይህም ለድህረ ምረቃ ደረጃ የሚያገለግል ምንባብ መሆኑን የፍለሽ ቀመር ውጤት አተረጓጐም ያስረዳል::

ከአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ የተመረጡት ናሙና ምንባቦች የስሌት ውጤት የሚጠቁመው ምንባቦቹ ከባድ መሆናቸውን ነው:: በየናሙናዎቹ የተመዘገቡት የስሌቱ ውጤቶች እንደቀደም ተከተላቸው -55.1፣ -29.2 እና -70.1 ናቸው:: እነዚህም ውጤቶች ሲተረጐሙ በድህረ ምረቃ ደረጃ ከሚሰጠው ምንባብ በላይ ክብደት ያላቸው ናቸው::

የናሙናዎቹ የርስ በርስ የክብደት ደረጃ ሲነፃፀር ናሙና ሁለት ቀላል፣ ናሙና አንድ መካከለኛ ናሙና ሦስት ከባድ መሆናቸውን ያሳያል:: ናሙና አንድ ከመጽሐፉ መጀመሪያ፣ ናሙና ሁለት ከመካከለና ናሙና ሦስት ከመጨረሻ የተወሰዱ ናቸው:: የክብደት ደረጃቸው ግን ቀደም ተከተሉ ተዘበራርቋል:: ይህ ደግሞ የትምህርት ሂደት ከቀላል ወደከባድ መጓዝ አለበት የሚለውን መርህ ያፋልሳል:: በአጠቃላይ በዚህ ቀመር ስሌት መሠረት የ3ቱም ናሙና ምንባቦች የየተናጠል የተነባቢነት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ሆኖ ተገኝቷል:: በቀላል አባባል ናሙና ምንባቦቹ ተነባቢነት የላቸውም::

.../

የመማርያ መጽሐፉ ምንባቦች ተነባቢነት በፍሪ ግራፍም ተለክቷል ፡ ይሁን እንጂ ውጤቱ ከፍላሽ ቀመር ውጤት የተለየ አይደለም:: የምንባቡን ተነባቢነት ለመለካት እንደፍሌሽ ቀመር የፍሪ ግራፍም የዓ.ነገርንና የቃል ርዝመትን ይጠቁማል:: በፍሪ ግራፍ ስሌት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ናሙና ምንባቦቹም ሆኑ መጽሐፉ ተነባቢነት የላቸውም:: ውጤታቸው በፍሪ ግራፍ ላይ ከሰፈረው 17ተ በላይ ሆና መገኘቱ ምንባብቹም ሆኑ በአጠቃላይ መጽሐፉ ተነባቢነት እንደሌላቸው ያሳያል:: የምንባቦቹ ተነባቢነት ግቧት ተማሪዎቹን የማያስደስቱ በቀላሉ የማይነበቡላቸውና የማይስቡዋቸው /ካርተር ጉድ፣1973፣ ድሬዋር 1980፣ ዳይ 1974/ ስለሚሆኑ የመማር-ማስተማርን ሂደት ይጐዳሉ::

ለሁለቱ የተነባቢነት መለኪያ መሣሪያዎች ውጤት በዚህ ደረጃ መገኘት ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁለቱም መሣሪያዎች የዓረፍተነገርና የቃል ርዝማኔ ይጠቀማሉ:: የቃል ርዝመት የሚወሰነው በየቃላቱ ውስጥ በሚገኙት የቀለሞች ብዛት ነው:: በተነባቢነት መለኪያ መሣሪያዎቹ ግምት መሠረት በቃል ውስጥ የሚገኙት የቀለሞች ብዛት የቃሉን ክብደት ያሰያል:: በዚህ ግምት መሠረት የአማርኛን ባሕርይ መመርመር ያስፈልጋል::

አማርኛ ቀለማዊ ቋንቋ ነው፣ በየቃላቱ ውስጥ የሚገኙት ፊደሎች በሙሉ /አንዳንድ ጊዜ ያለቀለም ከሚጻፈው ሳድስ ድምጽ በስተቀር/ ከነቀለማቸው ይጻፋሉ:: ይህም በናሙናነት የሚወሰዱትን የ100 ቃላት ቀለሞች ቁጥር ያበዛዋል:: የቀለሞች መብዛት የቃሉን ክብደት የሚያሳይ በመሆኑ የቀመሮቹ ውጤቶች ከባድ ሆነው ሊገኙ ችለዋል::

ሌላው ምክንያት ቀመሮቹ ለአንድ ዓይነት ቋንቋ ብቻ የተዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ:: ቀመሮቹ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በተለይም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ በመዘጋጀታቸው ለአማርኛ ቋንቋ የተነባቢነት መለኪያ ላይሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: በነዚህ ምክንያቶች የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተነባቢነት

...../

ደረጃ ዝቅ ብሎ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም ከዚህ ዓይነቱ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በጥናት የተደገፈ ውጤት መኖር አለበት::

4.2.4 የገንዘቤ መከራ ውጤት ትንተና

ከገንዘቤ መከራው በተገኘው ውጤት መሠረት የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ዝቅተኛ ነው:: በክፍል ሁለት ለቀረበው 6ኛ ጥያቄ የተማሪዎቹ መልስ አዎንታዊ ነበር:: 59.9% ተማሪዎች ምንባቦቹን አንብበው እንደሚረዱ መመለሳቸው ይታወሳል:: ለዚሁ ጥያቄ "ጥቂቶቹን እረዳለሁና ምንም አልረዳም" ያሉት ተማሪዎች 40.1% ያህል ነበሩ:: እነዚህም አንብበው እንደሚረዱ ከመለሱት ተማሪዎች በ19.8% ያንሳሉ:: ይሁን እንጂ የገንዘቤ መከራውን የተጠበቀውን ያህል መመለስ አልቻሉም:: ውጤቱ የሚያመለክተው የአብዛኛቹ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት በጥንቀት ደረጃ ላይ ይገኛል:: በመምህር ድጋፍና እርዳታ እንኳን አንብበው መረዳት ከሚችሉበት ደረጃ ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ይበዛሉ::

ውጤቱ ሲገመገም ተማሪዎቹ "አንብበን እንረዳለን" ሲሉ የአንብቦ መረዳትን እሳቤ ቢወጉ ያወቁት አይመስለም:: ቋንቋን መናገርና ምንባቦችን ማንበብ እንደመረዳት ቀጥረውት ካልሆነ በስተቀር የገንዘቤ መከራውን ውጤት አንብበው መረዳት አለመቻላቸውን ያረጋግጧል:: ተማሪዎቹ መጠይቆቹን ሲሞሉት ገድየለሽ ነበሩ፣ አለበለዚያ የገንዘቤ መከራውን አስበውበት አለሰሩትም:: ይህ ባይሆን ኖሮ የሁለቱ ውጤት የተለያየ ሊሆን አይችልም ነበር::

ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው ዘጠኝ አቢይ የትምህርት ዓላማዎች አሉ:: በመርሀ-ትምህርቱ ላይ ማዳመጥና መናገር በአንድ ላይ ተያይዘው መቅረባቸው ትክክል አለመሆኑን በማመን ለየብቻቸው እንዲታዩ ተደርገዋል:: ማንበብ፣ መጻፍ፣ ሥነልሳንና ሥነጽሁፍ የመርሀ-ትምህርት ዓላማዎች በመሆናቸው ለየብቻቸው አቢይ የትምህርት ዓላማዎች ሆነው ቀርበዋል:: "የመናገር/መጻፍ" ክሂል የሚለው አቢይ የትምህርት ዓላማ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ለሁለቱም ክሂሎች አንዱን ወይም ሌላውን በሚመለከት ሁኔታ በአማራጭነት ስለቀረቡ ከመጻፍና ከመናገር ክሂሎች እንደተለየ አቢይ የትምህርቱ ዓላማ ሆና ተወስዷል:: የቤተ መጻሕፍት አጠቃቀም ሌላው የመርሀ-ትምህርቱ አቢይ የትምህርት ዓላማ ሲሆን "ልዩ ልዩ የትምህርት ይዘቶች" በሚል የቀረበ አቢይ ዓላማም በሠንጠረዡ ላይ ሠፍር ይገኛል::'ልዩ ልዩ የትምህርት ይዘቶች' የሚለው ዓላማ በመርሀ ትምህርቱ ላይ አልተገለፀም ወይም የለም:: ይሁን እንጂ ከ1 – 8 ተራ ቁጥሮች ከተገለፁት ርዕሶች ለመመደብ አስቸጋሪ የሆኑትን ወይም ከሌሎች ስምንት አቢይ የትምህርት ዓላማዎች በየትኛው ውስጥ መመደብ እንደሚቻል ግልፅነት የጐደላቸው ነጥቦች ሆነው በመገኘታቸው እንደ አንድ ዓላማ ለብቻው ሊቀርብ ችሏል::

የመማሪያ መጽሀፉ መልመጃዎች ይዘቶች የተመሠረቱት በመጽሀፉ ምንባቦች ላይ ነው:: እነዚህ ይዘቶች የመርሀ-ትምህርቱን ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ግምገማዎች ለማስፈፀም የሚያገዙ በመሆናቸው ከመርሀ-ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች ጋር ተመሣሣይነትና ተቀራራቢነት ሊኖራቸው ይገባል:: በዚህም ምክንያት የመጽሀፉ መልመጃ ይዘቶች በተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች ተመድበው ቀርበዋል::

<u>ሠንጠረዥ 2፣</u> የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይዘቶች-

. . . /

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የማስተማሪያ መሣሪያዎች በተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: በተግባር ላይ ከዋሉም በኋላ ስለብቃታቸው መገምገምና ጠንካራ ጎናቸው የበለጠ እንዲጎለብት፣ ደካማ ጎናቸው እንዲጠናከር በየወቅቱ ጥናት ሊደረግባቸው ይገባል::

አማርኛ በትምህርት ዓይነትነት መሰጠትና በማስተማሪያ ቋንቋነት ማገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1984 ዓ.ም. ድረስ የነበሩት የማስተማሪያ መጻሕፍት ብቁ እንዳልነበሩ መምህራንና ሌሎችም የትምህርት ባለሙያዎች ሲተቹዋቸው ቆይተዋል:: የመለወጡ ምክንያት ባይታወቅም ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩት የማስተማሪያ መጻሕፍት ተቀይረው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ መዋላቸው ቀርቷል:: በምትካቸውም በ1984 ዓ.ም. ታትመው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ በማገልገል ላይ የሚገኙ የማስተማሪያ መጻሕፍት ለሁለተኛ ጊዜ ተዘጋጅተዋል::

የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች ብቃት ለመመርመር እንዲቻል የቀረቡት መሠረታዊ ጥያቄዎች 4 ሲሆኑ፣ እነዚህም የመማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች ጋር ያለው ግንኙነት፣ ለማስተማሪያነት የተመረጡት ምንባቦች ለተማሪዎች ፍላጎት፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ለምድና አካባቢ ያላቸው ቀረቤታ፣ የምንባቦቹ ተነባቢነትና የተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብቦ የመረዳት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ የሚጠይቁ ናቸው::

የመማሪያ መጽሐፉና መርሀ ትምህርቱ ያላቸውን ግንኙነት ለመመርመር የመማሪያ መጽሐፉን መለመጃዎች ይዘቶች ከመርሀ-ትምህርቱ የተለያዩ ክፍሎች /ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና ግምገማዎች/ ጋር በተዛምዶ ቀመር በማስላትና በ"ቲ" ቴስት ፈትና በመመርመር በመካከላቸው ግንኙነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል:: በሁለቱ መሣሪያዎች ግንኙነት አለመኖር ምክንያት ከሆኑት አንዱ የመሣሪያዎቹ የትኩረት አቅጧ

መለያየት ነው:: በአንዱ መማሪያ ላይ የቀረበው አቢይ የትምህርት ርዕስ በሌላው መማሪያ ላይ አለመቅረቡ ሁለቱ መማሪያዎች እንዳይጣጣሙ አድርጎዋቸዋል:: ይህም መጽሐፉ ከመርሐ-ትምህርቱ ያለመነጨ ወይም በመርሀ ትምህርቱ መሠረትነት ያልተዘጋጀ መሆኑን ያሳያል::

የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎች ፍላጐት ያላቸውን ብቃት ለማወቅ ለተማሪዎች ታድለው ከተሞሉት መጠይቆች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከተወሰኑ ጥያቄዎች በስተቀር አዎንታዊ መልሶች ተገኝተዋል:: ተማሪዎቹ ምንባቦቹ ለዕድሜያቸው፣ ለፍላጐታቸው፣ ለችሎታቸውና ለለምዳቸው ተስማሚነት እንዳላቸው ቢገልጹም፣ አንዳንድ የሚጐድሉት ነገሮች እንዳሉባቸውም አስረድተዋል:: የመጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎቹን ፍላጐት የሚያነሳሱ እንደቀኑ፣ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ተረትና ምሳሌ፣ ወዘተ ይጐድሏቸዋል:: እነዚህ ስልቶች ለደረጃው ተመጥነው ቢቀርቡ ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ፍላጐት በከፍተኛ ደረጃ ብቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ የጥናቱ ውጤት ያስረዳል::

ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ፍላጐት ስላላቸው ቀረቤታ ከመምህራን የተገኘው መረጃ የመካከለኛነት ደረጃ ሰጥተዋቸዋል:: ምንባቦቹ የይዘት ልዩነቶችን ካለማቅረባቸው፣ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎችን ካለመያዛቸውና ተማሪዎቹ አንብበው ካለመረዳታቸው በስተቀር ከፍላጐታቸው፣ ለአካባቢያቸውና ለዕሜደያቸው መካከለኛ ቀረቤታ እንዳላቸው ከመምህራኑ የተገኘው ውጤት ያስረዳል::

የምንባቦቹን ተነባቢነት ለመገመትና ለመለካት በፍለሽና በፍሪገራፍ ቀመሮች በመጠቀም ከሁለቱም የተገኘው ውጤት ምንባቦቹ ተነባቢነት የሌላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል:: ምንባቦቹ በፍላሽ ቀመር ከድህረ ምረቃና በፍሪገራፍ ከ17ኛ የክፍል ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች /አንባቢያች/ ካልሆኑ በስተቀር አንብበው መረዳት የማይችሉዋቸው ናቸው::

ምንም እንኳን ተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብበው እንደሚረዱ ቢገለፅም የመረዳት ደረጃቸውን ለማወቅ በተደረገው ሙከራ አንብበው መረዳት እንደማይችሉ ለመረዳት ተችሏል:: የተማሪዎቹ የማንበብ ደረጃ በጥንቀት በሚያነቡበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው:: ተማሪዎቹ አንብበን እንረዳለን ቢሉም ከገንዘቤ ሙከራ ውጤት አንፃር ሲታይ በመምህር እርዳታ እንኳን አንብበው መረዳት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ይገኛሉ::

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩና የትምህርቱን ውጤታማነት ለማጕልበት ከጥናቱ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተግባራዊ መሆን ይገባቸዋል፣

### 5.2.1 የመርሀ-ትምህርቱ ዓላማና የመማሪያ መጽሐፉ ግንኙነት

ስለሌላቸውና ግንኙነት በሌላቸው መርሀ-ትምህርትና መጽሐፍ የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ስለማይቻል፣ የመማሪያ መጽሐፉ የመልመጃዎች ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ከነውናችና ገምገማዎች አንፃር ተጠንተው እንደገና እንዲዘጋጁ ማድረግ ያስፈልጋል፣

### 5.2.2 የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ ፍላጕት በመካከለኛ

ደረጃ ተስማሚ መሆናቸው ቢገለጽም፣ እንደፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ቅኔዎች፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ ወዘተ ይጕድሉዋቸዋል:: ምንባቦቹን በበለጠና በከፍተኛ ደረጃ ከተማሪዎቹ ፍላጕት ጋር ለማስማማት እንዲቻል እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፎች ለክፍሉ ደረጃ በሚመጥን ሁኔታ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚጠመሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፣

5.2.3 የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ተነባቢነት የላቸውም፣ ይሁን እንጂ የቀመርቹ ውጤት የሚያሳየውን ያህል ክብደት እንደሌላቸው ይታመናል:: ስለዚህ፣

5.2.3.1 በዚህ ጥናት ውስጥ የፍለሽና የፍሪገሬፍ ቀመሮች ለተነባቢነት መለኪያ እንዲያገለግሉ ተደርገው የተገኘው ውጤት ተተንትና ተገልጿል፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ቀመሮች ከዚህ በፊት በአማርኛ ቋንቋ ያልተፈተሹ በመሆናቸው ይህን የመጀመሪያ ሙከራ መሠረት በማድረግ እነዚህኑ ቀመሮች ለአማርኛ ቋንቋ ተገባራዊ ለማድረግ፣ ወይም የተሻሻሉ ቀመሮችን ለመንደፍ ሰፊ ጥናት መካሄድ አለበት፣

5.2.3.2 የምንባቦቹን የተነባቢነት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ለዚሁ ተግባር ሊረዳ የሚችል ስልት መቀየስ፣

5.2.4 ተማሪዎቹ የመማሪያ መጽሐፉን አንብበው መረዳት እንደሚችሉ ቢገልፁም፣ የግንዛቤ ሙከራው ውጤት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በጣም አሳሳቢ መሆኑን ያሳያል፣ ከመምህራን የተገኘው መረጃ ይህንኑ ያረጋግጣል::
ስለዚህ፣

5.2.4.1 የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጐልበት ለንባብ ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት በሰፊው ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፣

5.2.4.2 የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች የክብደት ደረጃ አሁን ካለበት ዝቅ [illegible] የትምህርቱን ጥራት ሊጎዳ

ይችላል፣ ሆኖም የተማሪዎቹ የመረዳት ደረጃ አሳሳቢ በመሆኑ በተቻለ መጠን ከተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ጋር ለማመጣጠን መሞከር ያስፈልጋል::

## አዮደ ቃላት

| | |
|---|---|
| Adapt........................... | ማሻሻለ |
| Average......................... | አማካይ |
| Background Knowledge............ | ዳራዊ ዕውቀት |
| Cloze test...................... | የግንዛቤ መከራ |
| Communicative Phenomena......... | ተግባቦታዊ ሁኔታ |
| Communicative Syllabus.......... | ተግባቦታዊ መርሀ=ትምህርት |
| Context......................... | አውድ |
| Correlation..................... | ተዛምዶ |
| Curriculum...................... | ሥርዓተ=ትምህርት |
| Data............................ | መረጃ |
| Degree of freedom............... | የነፃነት ደረጃ |
| Formula/Formulea................ | ቀመር/ቀመሮች |
| Independent level............... | በግለ የሚማርበት ደረጃ |
| Instructional level............. | በድጋፍ የሚማርበት ደረጃ |
| Interest........................ | ፍላጐት |
| Linguistic...................... | የቋንቋ... |
| Linguistics..................... | ሥነ ልሳን |
| Organization.................... | ቅንጅት |
| Probability Level............... | የአጋጣሚ ደረጃ |
| Readability..................... | ተነባቢነት |
| Readability ease score.......... | የተነባቢነት ነጥብ |
| Readability Score............... | የተነባቢነት ቅለት/ደረጃ/ነጥብ |
| Skills.......................... | ክሂሎች |
| Syllabus........................ | ቀለሞች |
| Syllabus........................ | መርሀ=ትምህርት |
| T-Calculated.................... | የ[illegible]ስሌት ዋጋ |
| T-Critical...................... | የ[illegible]ወሰኝ ዋጋ |

## ማስታወሻዎች

1. ለተሰመረባቸው ቃላት በአምደ-ቃላት ሥር የእንግሊዝኛ አቻቸው ተሰጥቷቸዋል::

2. ዓ.ም. የሚለምህፃረ-ቃል ካለተከተላቸው በስተቀር በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙት ዓመታት ሁሉ አንደአውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው::

3. ለተማሪዎች መጠይቅ የተሰጠውን አማራጮች ከአባሪ ጠ ይመልከቱ::

4. ለመምህራን መጠይቅ የተሰጡትን አማራጮች ከአባሪ መ ይመልከቱ::

## የቢ ዎጸጠናት


Alderson, J.c.(1979). "The Cloze test procedure and Proficiency in English as a foreign language." TESOL Quarterly, 13.2:219-227

Asfaw Melaku and Simon Murison-Baulie 1976. "Language teaching materials," In Bender, M.L.and ct.al.(eds.) Language in Ethiopia. London: Oxford University Press.

Ball, G.H. (1976). "Standard for Material Selection" Journal of Reading, 20.1-B:208-211

Berhe Kahsay (1989). "A Study of the readability level of Grade ten text books and the comprehension ability of the students uSing them." MA. Thesis. presented to school of Graduate Studies, A.A.U.

Bor Muth, J.R. (1966). "Readability: a new approch." Reading research quarterly, 1.3: 79-84.

Bormuth, J.R. (1968). "The Clozereadability Procedure." Elementeary English, 45.4: 429-436.

British Council (1980). Projects in Material design: ELT documents special. London : Printing and Publishing Department.


../

_ Carrel, P.L. (1984). "Schema theory and ESL reading classroom implications and applications." The Modern Language Journal, 68.4:332-341.

Brumfit,C. (1980). Problems and Printiples in English. Bath: pergamon Institute of English, pitman press.

Cunningsworth, A.(1984). Eveluating and Selecting EFL teaching materials. London: Heinnmann Educational books Ltd.

Cunningsworth, A. (1989). Evaluating and Selecting Teaching Materials. London; Athenacum Press Ltd.

Daires, F.B. (1983). " Fundamental factors of Comprehension in reading." In Grntil, M.Lanle and Asers. Reading research revisited. Colombia: Abell and Howell comp any.

Day, R.R. (1994). "Selecting a passage for the EFL reading Class. " Forum, 32.1:20-23.

Dreyer, L.G. (1984). "Readabilty and Responsibility." Journal of Reading, 27.4: 558-565.

Dubin, F. and E.Olshtain (1990). Materials for Language learning. New York:Cambridge University Press.

Earl, W.S. (1965). "Evaluating and Adapting Language Materials, " In Allan and Cambel. Teaching English as a second Language. Los Angeles: McGraw-Hill, Inc.

Goodman, O.and et al.(1966). Choosing Materials to teach Reading. Detriot: Wayne State University Press.

Grant, N.(1989). Making the Most of Your text Book. London: Longman.

Gray,K. (1990). "Syllabus design for the general class: what happens to theory when you apply it. " ELT, 44,4:37-48.

Grellet, F.(1981). Developing Reading Skills. New York: Cambridge University Press.

Herker, W.J. (1977-78). "Selecting Instructional Materials for content Area Reading. " Journal of Reading. 21.1-8: 126-130.

Harmer, J.(1983). The Practice of English Language Teaching. New York: Langman.

Herrison, C.(1980). Reading in the Classroom. New York: Cambridge University Press.

Hartely, J. (1978). Designing Instructional Text. London: Nichole Publishing Comapny.

Hedge,T.(1987). Using Readers in Lanauge Teaching. London: McMillan Publishers Ltd,.

Hutchison, T.and A.Waters (1987). English for Specific Purpuses: A Learning Centered approch. New York: Cambridge University Press.

Keneth,S.G. and et al. (1988). Choosing Materials to teach reading. Michigan: Wayne University Press.

Klare,G.R. (1974-75). "Assessing Readability." Reading research Quaretely. 21: 101-117.

Krause, C.K. (1976). "Dos and Don'ts in Evaluating Text books." Journal of Reading. 20.1-8: 212-214.

Lee, J.A.(1967):" Reading Comprehension and text book Readability", Haile Selassie I University.

Lewis, M.and Hill,J. (1990). Practical Teachniques for Language Teaching. London: Language teaching publications.

McCarthy, M.(1991). Discourse Analysis for Language Teachers. New York: Cambridge University Press.

Mendida Berkessa (1988). "A Comparision of the reading Level of Behir Dar Teachers' College Freshman Students with the reading Levels Expected of them." MA. Thesis, Presented to School of Graduate Studies, A.A.U.

Munby, J.(1978). Communicative Syllabus Design: A Socio- Lingustic Model for defining the Context of Purpose-Specific lanauge Programmes. Cambridge:Cambridge University Press.

.../

Nelson, J.(1978). "Readability: Some Cautions for the content area Teacher." Journal of Reading, 21. 1-8:620-625.

Nunan, D.(1988). Syllabus design. Oxford: Oxford University Press.

Nunan, D.(1991) Syllabus design. Hong Kong: Oxford University Press.

Nuttall, C. (1982). Teaching Reading Skills in A Foreign Language. London: Heinemann.

Ollen, J.B. (1973). "Clozetest of Second Language Proficiency and What they measure." Language Learning, 23.1:105-118.

Richards, J.C. (1987). The Context of Language Teaching. New York: Cambridge University Press.

Tibebe Alemayehu (1987)." An Exploration of the English Proficiency Level of Government and Mission Secondary Schools Learners." MA.Thesis, Presented to School of Graduate Studies, A.A.U.

Tesgaye W/Yesus (1987). " An Investigation into the Comprehension ability of A.A.U.Freshman by using the Fog index and the Clozetest." MA. Thesis. Presented to school of Graduate Studies, A.A.U.

Williams, D. (1983). "Developing Criteria for textbook Evaluation." ELT, 37.1-4: 251-255.

Williams, E. (1990). Reading in the Classroom. London: McMillan Publishers Ltd.,

Williams, R. (1986). "Top ten" Principles for Teaching Reading." ELT, 40.1-4: 42-45.

ሥርዓተ-ትምህርት ዋና ክፍል /1970/:: የአማርኛ ሥርዓተ-ትምህርት:: አዲስ አበባ፣ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት::

ሰለሞን ገዛው/1978/:: "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ግምገማ:: " አ.አ.ዩ. የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት::

በከሬ ጌታ/1975/:: "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘት በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች::" አ.አ.ዩ. የኢትዮጵያ ቋንቋዎትና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት::

ብርሃኑ ዘሪሁን /1978/:: "የአማርኛ ማስተማሪያ መጻሕፍት በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምሳሌነት::" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት::

የአማርኛ ትምህርት ቡድን /1984/:: የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ፡ አሥረኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት::

የአማርኛ ትምህርት ቡድን /1984/:: የአማርኛ መማሪያ አሥረኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት::

አሰፋው አጥና /1975/:: "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ በሁለት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነፅሁፍ ክፍል ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ::

አይሌው አሰፋው /1985/:: "ከ1933-1983 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ በአገልግሎት የዋሉ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ዝርዝር ዓይነትና የይዘት ግምገማ":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮ.ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ::

ነጋሳ አጄታና ጉለላት አበራ /1982/:: "በ1967 ከ9-12 ላሉት ክፍሎች ስለቀረበው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዘገጃጀት ሂደት የሚገለጽ የመነሻ ጽሁፍና መምህራን ያቀረቡት የድክመት ጥቆማ ትንተና።" /ያልታተመ/

ይለማ ከበደና አሸቱ ከበደ /1982/:: "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምቤቶች የአማርኛ ሥርዓተ-ትምህርት የአሁኑና የወደፊት መሆን የሚገባው::" /ያልታተመ/

ፈቃደ አዘዘ /1982/:: "አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስለሥርዓተ-ትምህርቶች ስለመማሪያ መጻሕፍትና ስለስነጽሁፍ ግና በቋንቋ ትምህርት:: "/ያልታተመ/

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY





Figure 3.4. Fry's extended readability graph

**The Fry graph (1977; Figure 3.4)**

**This is one of the most straightforward ways of obtaining a** readability index. The graphical form is helpful for a number of reasons: it saves time on making calculations; it offers visual information when numerical results might give a spurious impression of accuracy; the user of the graph can tell at a glance **if a passage is in comparative terms more difficult than average** in vocabulary or in sentence length. This final point is not generally realised, but clearly if the curve represents normal texts, points above the line, or towards the top right quadrant, **will represent passages with higher than average vocabulary** difficulty, while points below the curve, towards the bottom left quadrant, will suggest greater than average sentence length. These are the directions for using the readability graph:

- Randomly select three sample passages and count out exactly 100 words each, beginning with the beginning of a sentence.
- Count the number of sentences in the 100 words, calculating the length of the fraction of the last sentence to the nearest one-tenth.
- Count the total number of syllables in the 100-word passage. If you don't have a hand counter available, an easy way is to simply put a

አባሪ — ለ

## የግንኙት ቀመርና አተረጓጎም

### 1/ የግንኙነት ቀመር

$$r = \frac{Nxy - (x)(y)}{\sqrt{[Nx^2-(x)^2][Ny^2-(y)^2]}}$$

### 2/ የግንኙነት ውጤት አተረጓጎም

| | |
|---|---|
| 1.0 | Perfect relationship |
| 0.7-0.9 | high relationship |
| 0.4-0.6 | moderate relationship |
| 0.1-0.3 | low relationship |
| 0 | no relationship |
| -1.0 | perfect negative relationship |
| -0.7--0.9 | high " " |
| -0.4--0.6 | moderate " " |
| -0.1--0.3 | low " " |

**አባሪ — ሐ**

## በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

## የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

ውድ የ______________ ትምህርት ቤት የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች! የዚህ መጠይቅ ዓላማ ለአሥረኛ ክፍል ተመርጦ አሁን በማገልገል ላይ የሚገኙት የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች ለቋንቋው ማስተማሪያነት ብቃት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ ለተጀመረው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው ::

ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት ለአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባብ አመራረጥ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፤ ስለዚህ ጥናቱ የተተለመለትን ግብ ሊመታ እንዲችል ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕግሥትና በጥሞና በማንበብ ትክክለኛ ናቸው የምትሉዋቸውን መልሶች እንድትመልሱልኝ እየጠየቅሁ፣ መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ ::

ማሳሰቢያ፣

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም፣ ክፍልና ተራ ቁጥር መጻፍ አስፈላጊ አይደለም፣

ለ. መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት፣ ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት ወይም ከጓደኛ አይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ አይፈቀድም ::

..../

## ክፍል አንድ

ከዚህ በታች የተተዉትን ባዶ ቦታዎች በመሙላት ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ስጪ/።

ሀ/ ጾታ ________

ለ/ ዕድሜ ________

ሐ/ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለ መልስ የሚሆነውን ወይም እንደ ጥያቄው ሁኔታ ከአንድ በላይ መልሶች በመምረጥ ትክክለኛ መልስ የሚያመለክተውን ሆሄ ወይም ፊደል /ሆሄያት ወይም ፊደሎች/ ክበብ።

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ትገኛለህ/ትገኛለሽ/?

   ሀ/ ዘወትር እገኛለሁ።

   ለ/ አልፎ አልፎ እገኛለሁ።

   ሐ/ በፍጹም አልገኝም ።

2. ለአንደኛው ጥያቄ መልስህ/መልስሽ/ 'በፍጹም አልገኝም' የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

   ሀ/ አማርኛን መማር ስለማልፈልግ ነው።

   ለ/ መምህሩን ስለምጠላ ነው።

   ሐ/ ብማርም፣ ባልማርም ፈተናውን ስለማልፍ ነው።

   መ/ የመማሪያ መጽሐፉን ስለምጠላ ነው።

   ሠ/ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ስለማጠና ነው ።

3. ለሁለተኛው ጥያቄ መልስህ/መልስሽ/ "አማርኛን መማር ስለማልወደው ነው" የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሀ/ አማርኛን ስለማውቅ ነው፤

ለ/ የማስተማሪያ መጽሐፉ ስለማያስደስተኝ ነው፤

ሐ/ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ስለምጠላው ነው፤

መ/ መምህሩ በጥሩ ሁኔታ ስለማያስተምሩ ነው፤

ሠ/ ምንም ምክንያት የለኝም ።

4. በመማሪያ ክፍል ውስጥ አማርኛን የምትማረው/የምትማሪው/ በምንድን ነው?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መጽሐፉ ነው፤

ለ/ አብዛኛውን ጊዜ በመማሪያ መጽሐፉ ነው፤

ሐ/ አልፎ አልፎ በመማሪያ መጽሐፉ ነው፤

መ/ አብዛኛውን ጊዜ መምህሩ አዘጋጅተው በሚያቀርቡት መማሪያ ነው፤

ሠ/ ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፉ ውጭ ነው ።

5. ከሦስተኛው ጥያቄ መልስህ/መልስሽ/ ምንም ምክንያት የለኝም፡ የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ/ የማስተማሪያ ምንባቦቹ ከደረጃዬ በታች ስለሆኑ ነው፤

ለ/ መምህሩ በመጽሐፉ ለመጠቀም ስለማይፈቅዱ ነው፤

ሐ/ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ተከታታይነት ስለሌላቸው ነው፤

መ/ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ስለሚያሰለቹ ነው፤

ሠ/ የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከደረጃዬ በላይ ስለሆኑ ነው ።

6. በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ምን ያህል ትረዳለህ /ትረጃለሽ/?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ አንብቤ አረዳለሁ፤

ለ/ አብዛኞቹን አንብቤ አረዳለሁ፤

ሐ/ ከፊሎቹን አንብቤ አረዳለሁ፤

መ/ አንብቤ ምንም አልረዳም ።

7. ለስድስተኛው ጥያቄ መልስህ/መልስሽ/ 'አንብቤ ምንም አልረዳም' የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሀ/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከችሎታዬ በላይ ስለሆኑ ነው፤

ለ/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ግልፅነት ስለሚጐድላቸው ነው፤

ሐ/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከፍላጐቴ ጋር ስለማይጣጣሙ ነው፤

መ/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች መልዕክቶች ተጨባጭነት ስለሌላቸው ነው፤

ሠ/ የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች በአዳዲስ ቃላት የተሞሉ ስለሆኑ ነው።

8. ከማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የሚተላለፉት መልዕክቶች፤

ሀ/ ግልፅ ናቸው፤

ለ/ በመጠኑ ግልፅ ናቸው፤

ሐ/ ግልፅ አይደሉም።

9. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የክፍል ውስጥ ተሳትፎህን /ተሳትፎሽን/ የሚያመለክቱት እንዴት ነው?

ሀ/ እያበረታቱኝ ነው፤

ለ/ በመጠኑ እያበረታቱኝ ነው፤

ሐ/ እያሰለቹኝ ነው።

10. መምህሩ በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ምን ያህል ይጠቀሙባቸዋል?

ሀ/ አብዛኛውን ጊዜ ነው፤

ለ/ አልፎ አልፎ ነው፤

ሐ/ በጭራሽ አይጠቀሙባቸውም።

11. የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ይዘቶች፤

ሀ/ ወቅታዊ ናቸው፤

ለ/ በመጠኑ ወቅታዊ ናቸው፤

ሐ/ ወቅታዊ አይደሉም።

12. የመማሪያ መጽሐፉ ^ምንባቦች ክንዋኔ ነገሮችን?^ ምን ያህል ያስተምራሉ?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ ነው፤

ለ/ በመጠኑ ነው፤

ሐ/ ምንም አዲስ ነገር አያስተምሩም ።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

ከዚህ በታች የቀረቡት ሐሣቦችና ጥያቄዎች አምስት አምስት መመዘኛ ዎች አሉዋቸው ። ለየጥያቄዎቹና ለየሐሳቦቹ በሚመጥነው መመዘኛ ሥር ካለው ሣጥን ውስጥ የዚህ ዓይነት /×/ ምልክት በማድረግ መልስ/መልሺ/ ።

| ተቁ | ጥያቄዎች/ሀሣቦች/ | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ (መካከለኛ) | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከዕድሜህ (ከዕድሜሽ/ ጋር የሚመጣጠኑበት ደረጃ፤ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 2 | የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ፍላጎትህን/ፍላጎትሽን/ የሚያሟሉበት ደረጃ፤ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 3 | የተለያዩ ምንባቦችን ለማንበብ ያለህ/ያለሽ/ ፍላጎት፤ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 4 | የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ለማንበብ ያለህ/ያለሽ/ ፍላጎት፤ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች/ሀሣቦች/ | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ (መካከለኛ) | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 5 | የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከችሎታህ/ከችሎታሽ/ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 6 | ምንባቦች ከኑሮ ልምድህ /ልምድሽ/ እና ከአካባቢህ/ከአካባቢሽ/ ጋር ያላቸው ቀረቤታ ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 7 | ከምንባቦቹ የሚገኘው ዕውቀት፣ በተፈለገው አካባቢ፣ ሁኔታና ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት ደረጃ ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 8 | ምንባቦቹ ኅብረተሰቡ የሚገለገልባቸውን ስለ ቶች/ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌ፣ ፈሊጦች...) ምን ያህል ይዘዋል? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 9 | የምንባቦቹ የመልዕክት አቀራረብ/ምሳሌ አሰጣጥ፣ የሐሳብ ዝርዝር ነት ግልፅነት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 10 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የዐረፍተ ነገር አሰካክ/ግለጸ ነት፣ ይብዛዛ ነት፣... ከችሎታህ/ከችሎታሽ/ ጋር የሚስማማበት ደረጃ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች/ሀሳቦች/ | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ (መካከለኛ) | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 11 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የክብደት ደረጃ /የቃላቱ አዲስነት፣ የፅንስ ሀሳብ ጥልቀት፣.../ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 12 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የማንበብ /ፍላጎትህን/ፍላጎትሽን/ የሚያነሳሱበትና የሚያበረታቱበት ደረጃ፣ | | | | | |

## ክፍል አራት

በማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ላይ ከተጠየቁት ጥያቄዎች የተለየ አስተያየት ካለህ/ካለሽ/ በአጭር በአጭሩ ግለጽ /ግለጭ/፣

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

ስለትብብርህ/ትብብርሽ/ በድጋሚ አመሰግናለሁ!

# አባሪ ወ

## <u>በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን</u>
## <u>የሚሞላ መጠይቅ</u>

ውድ የ ________________ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህራን !

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በአሥረኛ ክፍል ተመርጠው አሁን በማገልገል ላይ ያሉትን የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች ለቋንቋው ማስተማሪያነት ብቃት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ጥናት ለማካሄድ የሚያገዙ መረጃዎች ለመሰብሰብ ነው ::

የጥናቱ ውጤት ለአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ ምንባብ አመራረጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል :: ስለዚህ ጥናቱ ከታለመለት ግብ እንዲደርስ ተገቢና ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕግስትና በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የምትሉዋቸውን መልሶች እንድትመልሱልኝ እየጠየቅሁ፣ ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ ::

<u>ማሳሰቢያ</u>፡ በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም !

## ክፍል አንድ

### አጠቃላይ መረጃዎች

1. ፆታ ____________
2. የትምህርት ደረጃ ____________
3. አማርኛን ለማስተማር ሰልጥነዋል? ____________
4. በተራ ቁጥር ሦስት ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጡት መልስ "አዎ" የሚል ከሆነ የሰለጠኑበት መስክ፣

| ዋና | | ንዑስ | |
|---|---|---|---|
| 4.1 | አማርኛ | ሀ. | እንግሊዝኛ |
| 4.2 | እንግሊዝኛ | ለ. | አማርኛ |
| 4.3 | ፔዳጎጂ | ሐ. | አማርኛ |
| 4.4 | ሌላ ካለ ይገለጽ ____________ | | |

5. ትምህርቱን ያጠናቀቁበት ዘመን ____________
6. ጠቅላላ ያገለገሉት ዘመን ____________
7. በአሥረኛ ክፍል አማርኛን ምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል? /የአመቱን ብዛት ይጻፉ/ ____________
8. በትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ /ደረጃዎች/፣

   ሀ/ ____________ ሐ/ ____________

   ለ/ ____________ መ/ ____________

9. በአሁኑ ጊዜ የሚያስተምሩት አጠቃላይ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ____________
10. በአሁኑ ጊዜ አሥረኛ ክፍል ብቻ የሚያስተምሩበት የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ____________
11. የተካፈሉበት ወርክሾፕ / የተካፈሏቸው ወርክሾፖች/፣

| | የወርክሾፑ ስም /መጠሪያ/ | የተሳተፉበት ዘመን |
|---|---|---|
| ሀ. | ____________ | ____________ |
| ለ. | ____________ | ____________ |
| ሐ. | ____________ | ____________ |

12. ሙያዎን ለማሻሻል የሚመከሩበት ዘዴ።

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አምስት አምስት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ /መልሶች/ የሚያመለክቱትን ሆሄያት /ፊደሎች/ ይክበቡዋቸው።

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ይገኛሉ?

   ሀ. አዎ     ለ. አይገኙም

2. ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የማይገኙ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

   ሀ. አማርኛን መማር ስለማይፈልጉ ነው።

   ለ. ቢማሩም ባይማሩም ፈተናውን የሚያልፉ ስለሚመስላቸው ነው።

   ሐ. የመማሪያ መጽሐፉን ስለሚጠሉ ነው።

   መ. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ማጥናት ስለሚፈልጉ ነው።

   ሠ. ሌላ ምክንያት ስላላቸው ነው ::

3. ለሁለተኛው ጥያቄ መልስዎ "ሌላ ምክንያት ስላላቸው ነው" የሚል ከሆነ ምክንያቱን /ምክንያቶቹን/ ይግለጹ።

   ______________________________________________

   ______________________________________________

4. በክፍል ውስጥ አማርኛን የሚያስተምሩት በምንድን ነው?

   ሀ. ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መጽሐፉ ነው ።

   ለ. አብዛኛውን ጊዜ በመማሪያ መጽሐፉ ነው ።

   ሐ. አልፎ አልፎ በመማሪያ መጽሐፉ ነው።

መ. አብዛኛውን ጊዜ ራሴን አዘጋጅተው በሚያቀርቡት ነው ።

ሠ. ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፉ ውጭ ነው ።

5. ለተራ ቁጥር አራት ጥያቄ መልስዎ 'ሠ' ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሀ. መጽሐፉ ከተማሪዎች ደረጃ በታች ስለሆነ ነው ።

ለ. መጽሐፉ አርስዎን ስለማያስደስትዎ ነው ።

ሐ. የመጽሐፉ ምንባቦች ተከታታይነት ስለሌላቸው ነው ።

መ. የመጽሐፉ አቀራረብ አሰልቺ ስለሆነ ነው ።

ሠ. መጽሐፉ ከተማሪዎች ደረጃ በላይ ስለሆነ ነው ።

6. በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ምን ያህል ይጠቀሙባቸዋል?

ሀ. ሙሉ በሙሉ አጠቀምባቸዋለሁ ።

ለ. አብዛኛዎቹን አጠቀምባቸዋለሁ ።

ሐ. ከፊሎቹን አጠቀምባቸዋለሁ ።

መ. ጥቂቶቹን አጠቀምባቸዋለሁ ።

ሠ. አንዳቸውንም አልጠቀምባቸውም ።

7. ለስድስተኛው ጥያቄ መልስዎ 'ሠ' ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ?

ሀ. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከተማሪዎች ችሎታ በላይ ስለሆኑ ነው ።

ለ. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ግልጽነት ስለሚጎድላቸው ነው ።

ሐ. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት ስለማያሟሉ ነው ።

መ. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች መልዕክቶች ተጨባጭነት ስለሌላቸው ነው ።

ሠ. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች በአዳዲስ ያላት የተሞሉ ስለሆኑ ነው ።

8. ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ለማንበብ ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው ?

ሀ. ከፍተኛ ነው ። ለ. መካከለኛ ነው ። ሐ. ዝቅተኛ ነው

9. ለስምንተኛው ጥያቄ መልስ "ሐ" ከሆነ ከሚከተሉት ውስጥ ምክንያቱ የትኛው ነው ?

ሀ. የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ዝቅተኛ አድርገዋቸው ስለሚገምቱ ነው፤

ለ. የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች ምንም ጠቀሜታ ስለማይሰጡዋቸው ነው፤

ሐ. የመማሪያ መጽሐፉን ምንባቦች አንብበው መረዳት ስለማይችሉ ነው፤

መ. የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ከፍላጎታቸው ጋር ስለማይሄዱ ነው፤

ሠ. የመማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች አሰልቺዎች ስለሆኑ ነው ::

10. ምንባቦቹ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚያነሳሱት እንዴት ነው?

ሀ. አያስደሰቱ ነው፤

ለ. በመጠኑ አያስደሰቱ ነው፤

ሐ. አያሰለቹ ነው ::

11. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ይዘቶች፤

ሀ. ወቅታዊ ናቸው

ለ. በመጠኑ ወቅታዊ ናቸው፤

ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ይመጥናሉ ::

12. ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ዕድሜ ምን ያህል ይመጥናሉ ?

ሀ. በከፍተኛ ደረጃ ይመጥናሉ፤

ለ. በመጠነኛ ደረጃ ይመጥናሉ፤

ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ይመጥናሉ ::

13. የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የክብደት ደረጃ፤

ሀ. አየጨመረ ይሄዳል፤

ለ. በመጠኑ አየጨመረ ይሄዳል፤

ሐ. አየጨመረ አይሄድም : :

## ክፍል ሦስት

ከዚህ በታች የቀረቡት ሃሳቦችና ጥያቄዎች አምስት አምስት መመዘኛዎች አሉዋቸው፡፡ ለየሃሳቦቹ/ጥያቄዎቹ/ ሊስማሙ በሚችሉ መመዘኛዎች ሥር ባሉት ሳጥኖች ውስጥ ይህን /x/ ምልክት ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | አስተያየቶችና ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ /መጠነኛ/ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | ምንባቦቹ ተማሪዎችን ለማስደሰት ያላቸው ብቃት፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 2 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች መልዕክቶች የግልጽነት ደረጃ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 3 | በምንባቦቹ የቀረቡት ትምህርቶችና ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጎት የሚስማሙበት ደረጃ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 4 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ውስጥ የተሰጡት ምሳሌዎች ከተማሪዎቹ አካባቢና ልምድ ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 5 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ የቋንቋ ልምድ ያላቸው ቀረቤታ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

| ተ.ቁ | አስተያየቶችና ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ /መጠነኛ/ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 6 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ክሂሎችን /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣መጻፍ/ አመጣጥ ነው የሚያቀርቡበት ደረጃ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 7 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ለተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ አካባቢኗ ሁኔታ ሊስማሙ የሚችሉ የይዘት ልዩነቶች የያዙበት ደረጃ፣ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 8 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች ሽፈረ ተሰጡ የሚገለገሉባቸውን ስልቶች/ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌ፣ግጥም፣../ የያዙትን ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 9 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የመልዕክት አቀራረብ/ምሳሌ አሰጣጥ፣ የሃሳብ ዝርዝር ነት.../ግልጽነት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

| ተ.ቁ | አስተያየቶችና ጥያቄዎች | መመዘኛዎች: በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ /መጠነኛ/ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የዐረፍተ ነገር አሰካክ/ግልጽነት ፣ደርዝዝነት፣ .../ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ምን ያህል ይስማማል? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 11 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች አዳዲስ ነገሮችን ምን ያህል ያስተምራሉ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 12 | የማስተማሪያ መጽሐፉ ምንባቦች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ምን ያህል ያሳድጋሉ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 13 | የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳት ምን ያህል ያግዛሉ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

## ክፍል አራት

በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምንባቦች የተለየ ርዕም ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት በአጭር በኩልዎ ከዚህ በታች ይግለጹ ::

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

ስለትብብርዎ በድጋሚ አመሰግናለሁ ::

# አባሪ ሠ

## የናሙና ምንባቦች የቀለም አቆጣጠር

### ናሙና አንድ

| ተ.ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት | ተ.ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሰው | 2 | 21 | ዘዴዎች | 3 |
| 2 | ልጅ | 1 | 22 | አንዱ | 2 |
| 3 | አሁን | 2 | 23 | ምልክት | 3 |
| 4 | የምናውቀውንና | 6 | 24 | በመስጠት | 3 |
| 5 | የምንሠራበትን | 5 | 25 | በመግባባት | 3 |
| 6 | ቋንቋ | 2 | 26 | ነበር | 2 |
| 7 | ከመፍጠሩ | 4 | 27 | በእንደዚህ | 5 |
| 8 | በፊት | 2 | 28 | ያለ | 2 |
| 9 | ብዙ | 2 | 29 | ሁኔታ | 3 |
| 10 | ሚሊዮን | 3 | 30 | ብዙ | 2 |
| 11 | ዓመታት | 3 | 31 | ሺህ | 1 |
| 12 | በልዩ | 3 | 32 | ዓመታት | 3 |
| 13 | ልዩ | 2 | 33 | ካሳለፈ | 4 |
| 14 | ዘዴዎች | 3 | 34 | በኋላ | 3 |
| 15 | በመግባባት | 4 | 35 | ቀስ | 1 |
| 16 | ሲጠቀም | 3 | 36 | በቀስ | 2 |
| 17 | ቆይቷል | 2 | 37 | በድምፃዊ | 4 |
| 18 | ከነዚህ | 3 | 38 | ቋንቋ | 2 |
| 19 | ልዩ | 2 | 39 | ወደ | 2 |
| 20 | ልዩ | 2 | 40 | መግባባት | 3 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት | ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 41 | ደረጃ | 3 | 65 | መጠሪያና | 5 |
| 42 | ደረሰ | 3 | 66 | መግባቢያ | 4 |
| 43 | በየጊዜው | 4 | 67 | ዘዴ | 2 |
| 44 | ዘሚያገኛቸው | 7 | 68 | ወደ | 2 |
| 45 | ልምዶች | 2 | 69 | መፍጠሩ | 3 |
| 46 | ይበልጥ | 2 | 70 | ደረጃ | 3 |
| 47 | ወደ | 2 | 71 | ደረሰ | 3 |
| 48 | ተራ ቀቀ | 4 | 72 | በሥልጣኔው | 5 |
| 49 | ደረጃ | 3 | 73 | አዱግ | 2 |
| 50 | ለመድረስ | 3 | 74 | እየተራመደና | 7 |
| 51 | ሲጣጣር | 3 | 75 | በአስተሳሰቡ | 6 |
| 52 | ዘቀየ | 3 | 76 | በጣም | 2 |
| 53 | በኋላ | 3 | 77 | እየተራ ቀቀ | 6 |
| 54 | ለአንዳንዱ | 3 | 78 | ሲሄድ | 3 |
| 55 | ግዙፍ | 2 | 79 | የቋንቋው | 3 |
| 56 | ነገሮች | 3 | 80 | ጥበብና | 3 |
| 57 | በድምፅ | 2 | 81 | ሣይንስ | 2 |
| 58 | ኅብረት | 2 | 82 | ሥርዓትም | 4 |
| 59 | ስያሜ | 3 | 83 | አዱግ | 2 |
| 60 | ከመስጠት | 3 | 84 | ከተራ ቀቀ | 5 |
| 61 | አሌፍ | 2 | 85 | ደረጃ | 3 |
| 62 | ረቂቅ | 2 | 86 | ደርሷል | 3 |
| 63 | ለሆኑ | 3 | 87 | እንግዲህ | 3 |
| 64 | ነገሮች | 3 | 88 | የሰው | 2 |

| ተ.ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 89 | ሴጁ | 3 |
| 90 | የቋንቋ | 3 |
| 91 | ዕድገት | 2 |
| 92 | ከሥልጣኔው | 5 |
| 93 | ዕድገት | 2 |
| 94 | ጋር | 1 |
| 95 | አየር | 2 |
| 96 | የሚራመዱ | 4 |
| 97 | ሂደት | 2 |
| 98 | መሆኑን | 3 |
| 99 | መገንዘብ | 3 |
| 100 | ይኖርብናል | 3 |
| | ድምር | 290 |

ናሙና ሁለት

| ተ.ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ያለፈ | 3 |
| 2 | ነገር | 2 |
| 3 | ሲያስታውሱት | 5 |
| 4 | በጣም | 2 |
| 5 | ያስገርማል | 4 |
| 6 | እነዚያ | 4 |
| 7 | ጓደኛቹ | 4 |
| 8 | ሁሉ | 2 |
| 9 | ዛሬ | 2 |
| 10 | አጠገቤ | 4 |
| 11 | የሉም | 2 |
| 12 | ሆኖም | 2 |
| 13 | ኦሬፍ | 2 |
| 14 | አሴፍ | 2 |
| 15 | ባስታውሳቸው | 5 |
| 16 | ሥራቸው | 3 |
| 17 | ሁሉ | 2 |
| 18 | ከፊቴ | 3 |
| 19 | ጋጀ ቀናል | 4 |
| 20 | የነጮትኬ | 4 |
| 21 | ቀፊዱ | 1 |
| 22 | ትዝ | 2 |
| 23 | ሲለኝ | 2 |
| 24 | እስቃለሁ | 4 |
| 25 | የእጥናፍና | 5 |
| 26 | የታምራት | 4 |
| 27 | የኪስ | 2 |
| 28 | የርብ | 2 |
| 29 | ሲታርሰኝ | 4 |
| 30 | እነሱን | 3 |
| 31 | የሚያኒል | 3 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 32. | ተጨዋቾ | 3 |
| 33 | ከቶ | 2 |
| 34 | ያለ | 2 |
| 35 | አይመስለኝም | 4 |
| 36 | የሠፈራቸንን | 5 |
| 37 | ቡድን | 2 |
| 38 | ከገነኑት | 4 |
| 39 | ውስጥ | 1 |
| 40 | የሺጥሏ | 3 |
| 41 | ይገኝበታል | 4 |
| 42 | አንዱ | 1 |
| 43 | ፍኑ | 2 |
| 44 | የሁለት | 3 |
| 45 | ሰው | 1 |
| 46 | የሚያኒለው | 4 |
| 47 | የሺጥሏ | 3 |
| 48 | ኳሷን | 2 |
| 49 | ከነሰውዬው | 4 |
| 50 | አገር | 2 |
| 51 | መምታት | 2 |
| 52 | ሮማዱ | 2 |
| 53 | ነበር | 2 |
| 54 | ግብ | 1 |
| 55 | ለማግባት | 3 |
| 56 | የሚመጡ | 4 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 57 | ሁሉ | 2 |
| 58 | የሺጥሏ | 3 |
| 59 | ገና | 2 |
| 60 | መንደርደሩን | 4 |
| 61 | ሲጀምር | 3 |
| 62 | ሲያዩ | 3 |
| 63 | ከቻሉ | 3 |
| 64 | ኳሷን | 2 |
| 65 | ነኳ | 2 |
| 66 | አደርገው | 2 |
| 67 | አለበለዚያም | 6 |
| 68 | ሮዩ | 3 |
| 69 | ኳሷቸው | 3 |
| 70 | ደመሰሱ | 4 |
| 71 | ነበር | 2 |
| 72 | ዋሠፈሩ | 4 |
| 73 | ሪጆች | 2 |
| 74 | እነዚህ | 3 |
| 75 | ሩጃ | 2 |
| 76 | እነበሩም | 4 |
| 77 | እነአሥራት | 4 |
| 78 | ቂሉ | 2 |
| 79 | እነወንዳፍራሽ | 5 |
| 80 | ተንበሉ | 3 |
| 81 | ሁሉ | 2 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 82 | አብረውት | 3 |
| 83 | ይማሩ | 3 |
| 84 | ነበር | 2 |
| 85 | አሥራት | 2 |
| 86 | ዛሬ | 2 |
| 87 | መሐንዲስ | 3 |
| 88 | ነው | 1 |
| 89 | ወንዳፍራሽ | 3 |
| 90 | ደግሞ | 2 |
| 91 | አገበ ቶ | 2 |
| 92 | ሁለት | 2 |
| 93 | ሮሲ ዷሰ | 2 |
| 94 | ያንን | 2 |
| 95 | ትቶ | 2 |
| 96 | ዛሬ | 2 |
| 97 | ጭምት | 2 |
| 98 | ሆኗል | 2 |
| 99 | አሉ | 2 |
| 100 | ዱሮ | 2 |
| | ድምር | 269 |

ናሙና ሦስት

| ተ. ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የሰው | 2 |
| 2 | ሰው | 1 |
| 3 | ትን ታሪክን | 4 |
| [illegible] | [illegible] | [illegible] |
| 5 | የሚያኖሩለት | 6 |
| 6 | ብዙ | 2 |
| 7 | ነገሮች | 3 |
| 8 | አሉት | 2 |
| 9 | ከ ነዚህ | 3 |
| 10 | ቀነኛው | 3 |
| 11 | ወይ | 2 |
| 12 | ኋላ | 2 |
| 13 | ተመሰቦ | 4 |
| 14 | በዐይ ነሕሊናው | 6 |
| 15 | እንዲያይ | 3 |
| 16 | በዕዝ ነሕሊናው | 7 |
| 17 | እንደሰማ | 4 |
| 18 | የሚያደር ገው | 5 |
| 19 | አዕምሮው | 3 |
| 20 | ነው | 1 |
| 21 | ሌሎች | 3 |
| 22 | ደግሞ | 2 |
| 23 | ደብዳቤ | 3 |
| 24 | ሙዚቃ | 3 |
| 25 | ሲኒማ | 3 |
| 26 | ፎቶግራፍና | 5 |
| 27 | እ ነዚህን | 4 |
| 28 | የሚ ባሰሉት | 5 |
| 29 | ና ቸው | 2 |
| 30 | ሜገም | 2 |
| 31 | ገው | 1 |
| [illegible] | [illegible] | 2 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የ ቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 33 | የተጻፈለትን | 6 |
| 34 | ደሮ ዓቢ | 3 |
| 35 | ሲያ ነብ | 3 |
| 36 | አንዳች | 2 |
| 37 | ነገር | 2 |
| 38 | ይ ቀሰቀሰበ ታል | 7 |
| 39 | አፍቀሮ | 3 |
| 40 | የከዳት | 3 |
| 41 | ሰው | 1 |
| 42 | በአፍሏው | 3 |
| 43 | የፃፈለትን | 5 |
| 44 | ደሮ ዓቢ | 3 |
| 45 | የም ታ ነብ | 4 |
| 46 | ቢት | 1 |
| 47 | የሞ ተቻ | 3 |
| 48 | ሚሶ ቶን | 2 |
| 49 | ደሮ ዓቢ | 3 |
| 50 | የሚያ ነብ | 4 |
| 51 | ሰው | 1 |
| 52 | ፖን | 1 |
| 53 | እንደሚሰማ ቸው | 6 |
| 54 | መ ገመ ት | 3 |
| 55 | አ ያስ ቸገርም | 4 |

| ተ. ቁ | ቃላት | የ ቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 56 | ሙዚቃም | 3 |
| 57 | እንዲሁ | 3 |
| 58 | ነው | 2 |
| 59 | አንዱ | 1 |
| 60 | ሙዚቃ | 3 |
| 61 | በሬዲዮ | 4 |
| 62 | በሚሰማበት | 5 |
| 63 | ጊዜ | 2 |
| 64 | የ ተ ተከለቹ | 5 |
| 65 | ጥፋት | 2 |
| 66 | የትም | 2 |
| 67 | ይሁን | 2 |
| 68 | መ ቼም | 2 |
| 69 | ያ | 1 |
| 70 | ሙዚቃ | 3 |
| 71 | በ ተሰማ | 4 |
| 72 | ቁጥር | 2 |
| 73 | በጆሮ | 3 |
| 74 | ሰ ታሰ ተጋቢ | 5 |
| 75 | ትኖራለች | 4 |
| 76 | በ ተለይም | 4 |
| 77 | በፍቅር | 3 |
| 78 | ፍዜማ | 3 |

| ተ.ቁ | ቃላት | የቀለም ብዛት |
|---|---|---|
| 79 | የተሰማ | 4 |
| 80 | ሙዚቃ | 3 |
| 81 | የፍቅረኛቹን | 5 |
| 82 | መሰከ | 1 |
| 83 | ብቻ | 2 |
| 84 | ሣይሆን | 3 |
| 85 | ያንለት | 2 |
| 86 | የለበሱትን | 5 |
| 87 | የሰቢሰ | 2 |
| 88 | የበሉትን | 4 |
| 89 | ምግብ | 2 |
| 90 | የጠጡትን | 4 |
| 91 | መጠጥ | 2 |
| 92 | ዓይነት | 2 |
| 93 | የረገጡትን | 5 |
| 94 | አፈር | 2 |
| 95 | የተገናኙበትን | 7 |
| 96 | ጊዜና | 3 |
| 97 | ሰዓት | 2 |
| 98 | ያስታውሳል | 4 |
| 99 | ሲኒማም | 3 |
| 100 | ቀዕበታፒነት | 5 |
| | ድምር | 313 |

# አባሪ — ረ

## የግንዛቤ ሙከራ ናሙናዎች

### ናሙና አንድ

መመሪያ:— ከዚህ በታች በቀረበው ምንባብ ውስጥ ክፍት ለተተዉት ባዶ ቦታዎች ተስማሚ የሆነ ቃል ለብቻ በተሰጠህ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በመጻፍ መልስ ። አስታውስ! ለአንድ ክፍት ቦታ የሚያስፈልገው አንድ ቃል ብቻ ነው ።

የሰው ልጅ አሁን የምናውቀውንና የምንሠራበትን ቋንቋ ከመፍጠሩ በፊት ብዙ ሚሊዮን ዓመታት በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመግባባት ሲጠቀም ቆይቷል ። ከነዚህ ልዩ ልዩ ዘዴዎች ___1___ ምልክት በመስጠት መግባባት ነበር ። ___2___ ያለ ሁኔታ ብዙ ሺህ ___3___ ካሳለፈ በኋላ ቀስ በቀስ ___4___ ቋንቋ ወደ መግባባት ደረጃ ___5___ ። በየጊዜው ከሚያገኛቸው ልምዶች ይበልጥ ___6___ ተራቀቀ ደረጃ ለመድረስ ሲጣጣር ___7___ በኋላ ለአንዳንድ ግዙፍ ነገሮች ___8___ ህብረት ስያሜ ከመስጠት አልፎ ___9___ ለሆኑ ነገሮች መጠሪያና መግባቢያ ___10___ ወደ መፍጠሩ ደረጃ ደረሰ ። ___11___ እየተራመደና በአስተሳሰቡ በጣም እየተራቀቀ ___12___ የቋንቋ ጥበብና ሳይንስ ሥርዓትም ___13___ ከተራቀቀ ደረጃ ደርሷል ። እንግዲህ ___14___ ልጅ የቋንቋ እድገት ከሥልጣኔው ___15___ ጋር አብሮ የሚራመድ ሂደት ___16___ መገንዘብ ይቻላል ።

ቋንቋ ከምልክታዊ ___17___ ወደ ድምጻዊ መግባቢያነት በመሸጋገሩ ___18___ ልጅ አሁ የሚባል እድገት ___19___ ወደ መጠረሻው የመገናኛ ዘዴው ___20___ ደረጃ እንዳደረሰ ይሰማው ነበር ። ___21___ ውጭ የሆነና ለቋንቋ ኦጋች ___22___ ሌላ መገናኛ ዘዴ እንደሚያስፈልገው ___23___

በማያደርጋቸው ሙከራዎች ይገለጽ ነበር :: 24 በድንጊያ፣ በብረት፣ በቆዳ፣ በእንጨትና 25 ነገሮች ላይ የሚቀርጻቸው ሊቆ 26 ቅረጻ ቅርጾችና ምልክቶች ነበሩ :: 27 በሞተበት ጊዜ ዉሳሳ ድንጊያ 28 ላይ ማድረጉ በዚያ ቦታ 29 መቀበሩን ለሌሎች መልዕክት ለማስተላለፍ 30 :: ይህም ያንን ቦታ በአካባቢው 31 ቦታዎች የተለየ ስለሚያደርገው መልዕክት 32 ተላልፏል ማለት ነው :: እንዲህ 33 የምልክት መግባቢያ በጣም አስፈላጊ 34 ለጊዜና ለቦታ ችግር መፍትሔ 35 ነው ::

ከቦታ ርቀት አንጻር 36 በቋንቋው የሚደረገው ግንኙነት ውሱን 37 እናገኛለን :: በቋንቋ ግንኙነት የሚያደርጉት 38 በአካል አንድ ቦታ መገኘት 39 :: ለጽሁፈት ግንኙነት ግን ይህ 40 አይደለም :: ለምሳሌ ያህል በሰለጠነው 41 ዘንድ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ 42 ጽሑፎች ደብዳቤዎችን ምን ያህል 43 ከሰው፣ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ዘመንን 44 የማገናኘት ችሎታ እንዳላቸው መገመቱ 45 ይበቃል :: ሌላው ሕዝብ የደረሰበትን 46 ደረጃ የምርምሩንና የዕውቀቱን ውጤት 47 ሺህ ኪሎ ሜትር ሳንጓዝና አኩያው 48 በአካል ሳንገናኝ ካለንበት ሆነን 49 ጠረዳትና የዕውቀ ፍሬ ተካፋዮች 50 እንችላለን ::

## ናሙና ሁለት

መመሪያ:- ከዚህ በታች በቀረበው ምንባብ ውስጥ ክፍት ለተተውት ባዶ ቦታዎች ተስማሚ የሆነ ቃል ለብቻው በተሰጠህ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በመጻፍ መልስ :: አስታውስ! ለአንድ ክፍት ቦታ የሚያስፈልገው አንድ ቃል ብቻ ነው

ያለፈ ነገር ሲያስታውሱት በጣም ያስገርማል ። እነዚያ ጓደኞቼ ሁሉ ዛሬ __1__ የሉም ። ሆኖም አንድ አንድ __2__ ሥራቸው ሁሉ በፊቴ ይደቀናል ። __3__ ቀለሙ ትዝ ሲለኝ እስቃለሁ ። __4__ የታምራት የኪስ ሽበብ ሲታወሰኝ __5__ የሚያህል ጣቶች ከተ ያለ __6__ የበፈራችንን በሙን ካገኘነት ውስጥ __7__ ይገኝበታል ። አንዱምኑ የሁለት __8__ የሚያህለው የሺፕሊ ቧቧን ከነሰውየው __9__ መምታት ለማቆ ነበር ። ገበ __10__ የሚጠጡ ሁሉ የሺፕሊ ገና __11__ ሲጀምር ሲያቆ ከቻሉ ቧቧን __12__ አድርገው፣ አለበለዚያም ወደ ኋላቸው __13__ ነበር ።

የበፊሩ ልጆች እነሡ __14__ አልነበሩም፣ እነአሥራት ጭምር፣ እነወንዳፍራሽ __15__ ሁሉ አበረውኝ ይማሩ ነበር ። __16__ ዛሬ መሐንዲስ ነው ። ወንዳፍራሽ __17__ ሁለት ወልዷል ። ያንን ትቶ __18__ ጥምት ሆኗል አሉ ። ቁር __19__ ተማሪ ቤት በመገና ደረጃ __20__ የሚያህል አልነበረም ። ትንሽም የምትወዳደረው __21__ ነበረች ። ብርቄ የሰፈሩ ጥያቄ __22__ ቀጥር ዘወትር ትገረፍ ነበር ። __23__ የምትጀምረዉ ገን ገና እቴ __24__ ያንን መነጽራቸውን ሰክተው "ስም __25__ ምን ማለት ነው?" ለማለት __26__ ነው ። በተለይም አንዱ ቀን __27__ ክፍል ሳለን የትምህርት ቤቱን __28__ እጎቸው ለማትፈልግ "ዜይ" __29__ ገና ስትጀምር የሳቅነው ሳቀና __30__ ሙሳቱ የተገረፈችው መገረፍ ትዝ __31__ ።

በእንግሊዝኛ የቃል ጽሕፈት ጊዜ __32__ ወንዳፍራሽ አሥር አሥር ሳይገረፉ __33__ አያውቅም ። በነርሱ ላይ ይበረታል __34__ ነው እንጂ ሁላችንም አንድ __35__ መቀመጫችን አይቀርም ነበር ። ገና __36__ በሩን ከፍተው " ጉድ ሞር ኒግ " __37__ ሁላችንም መርበድበድ እንጀምራለን ። ማስማሪያው፣ __38__ ወንበር ተሸከሞ መሙ አጁ __39__ ላይ አድርጎ መንበርከኩ ሁሉ __40__ የሚለንያኔ ነው ። ከዚያ __41__ ተጠይቆ ጥያቄ ሲጠፍ ያጠናው __42__ የቆ እሩምታ ሲያምታታው ያላጠናው __43__ ... ችላው፣ ዉጥታው ይሁ ነው __44__ ።

አስተማሪው ወዲያ ሲሉ ደግሞ ___45___ ሌላ መስክ ይይዛል :: እነሲሳይ ___46___ በሌላው ተንደርድረው ይናኙና ሥዕል ___47___ :: ወንዳፍራሽና ምትኬ ተውኔት መሥራት ___48___ :: እነጋይሌ በእንግሊዝኛ እየተነጋገሩ ይንጓደዳሉ :: ___49___ የምንለው አርጋው እንቧን የገበረገበ ___50___ አለቃ ኤፍሬም ሲያደርጉ እዩት ትንሽ ቆብ ራሱ ላይ ይደፉና አሥር ቱ ቃላትን ካላስተማርኳችሁ ይላል :: ...

## <u>ናሙና ሦስት</u>

መመሪያ:- ከዚህ በታች በቀረበው ምንባብ ውስጥ ክፍት ለተተውት ቦታ በታዎች ተስማሚ የሆነ ቃል ለብቻው በተሰጠህ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በመጻፍ መልስ :: <u>አስታውስ</u>፤ ለአንዱ ክፍት ቦታ የሚያስፈልገው <u>አንድ ቃል</u> ብቻ ነው ::

የሰው ልጅ ትዝታውን ጠብቆ የሚያኖርበት ብዙ ነገሮች አሉ :: ከነዚህ ዋነኛው ወደኋላ ተመልሶ ___1___ እንዲያይ በዐዘነ ሕሊናው እንዲሰማ ___2___ አእምሮው ነው :: ሌሎች ደግሞ ___3___ ሙዚቃ፣ ሲኒማ፣ ፍቶግራፍና እነዚህን ___4___ ናቸው :: ማንም ሰው ኋር ___5___ ደብዳቤ ሲያነብ እንዳች ነገር ___6___ :: አፍቀር የከዳት ሰው በአፍላው ___7___ ደብዳቤ የምታነብ ሴት ቁተች ___8___ ደብዳቤ የማያነብ ሰው ምን ___9___ መገመት አያስቸግርም :: ሙዚቃም እንደዚሁ ___10___ :: አንድ ሙዚቃ በረዶ በሚሰማበት ___11___ የተከሰቸ ጥይት የትም ይሁን ___12___ ያ ሙዚቃ በተሰማ ቁጥር ___13___ ስታስተጋባ ትኖራለች :: በተለይም በፍቅር ___14___ የተሰማ ሙዚቃ የፍቅረኛን መሰከ ___15___ ሳይሆን ያንለት የለበሱትን የልብስ፣ ___16___ ምግብ፣ የጠጡትን መጠጥ ዓይነት ___17___ ሽፈር፣ የተገናኙበትን ጊዜና ሰዓት ___18___ :: ሲኒማም ቅጽበታዊነት ይኖረው እንጂ ___19___ ተለይቶ የሚታይ አይደለም ::

እነዚህ ____20____ በዝዛኛው በደስታው የተደረገውን ሁሉ ____21____ ለማየት መቻላቸው ሲታሰብ የተፈጥሮ ____22____ በጣም ያስገርማል ። ሆኖም የፎቶግራፍን ____23____ አያስደንቅም ። ምክንያቱም ፎቶግራፍ የሚቀሰቀሰው ____24____ ከሁሉም በጣም የሚልቅ ይመስላል ። ____25____ በሞት የተለያችሁን ሰው ፎቶግራፍ ____26____ መንፈስ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ። ____27____ ነገር ታውቃላችሁ? ወቹም እንደ ተመልካች ____28____ ። አንዳንዱ ከሰውየው ጠባይ ደጋጉን ____29____፣ አንዳንዱም፣ ከፉ ከፉውን ።

ሌላ ____30____ ሁሉንም ሊያይ ይችላል ። ግን ____31____ ፎቶግራፉ ባሳይታይ እንዲሁ በዓይነ—ሕሊና ____32____ ትዝታ ይልቅ ይከናው የበለጠ ____33____ ያለው፣ የበለጠ ብሩህ መሆኑ ____34____ ። ሥዕሉ ሲታይ ሰውየው እዚያው ____35____ ዓይነት ሆኖ ይሰማል ። "ነበርኩ፣ ____36____ ግን የለሁም" የሚል ይመስልና ____37____ ጭጋግ ከተሸፈነ አንዳች የሕይወት ____38____ ውስጥ ይጥላል ። ይህ የሚሆነው ____39____ ጋር ሲሆን የዓይነ ሕሊናችን ደረጃ ____40____ ስለሚገለ ይመስላል ። እንዲህ ዓይነቱ ____41____ በሚታይበት ጊዜ የሰውየው የሕይወት ____42____ ሥዕሉ ራሱ እንደሚንቀ፣ቀስ ዓይነት ____43____ ሆኖ ይሰማል ። ዓይኖች እንደሚያዩ ____44____ ወደ ተመልካች የሚያተኩ ወይም ____45____ ይመስላሉ ። ፈገግታም ካለው ለተመልካች ____46____ የተሰነዘረ፣ እንዲያውም ለማውራት የሰተናኝ ____47____ ይመስላል ።

ትዝታ እጅግ ብዙ ____48____ ። በሕይወት ይኑርም አይኑርም ያንዱ ____49____ ፎቶግራፍ ሲታይ ብዙ ነገሮች ____50____ ይመጣሉ ።

# አባሪ ሰ

## የግንዛቤ ሙከራ ናሙናዎች መልሶች

### ሀ/ የናሙና አንድ መልሶች

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. አንቀ | 17. መግባቢያነት | 33. ያለው | 49. አንበቦን |
| 2. በእንደዚህ | 18. የሰው | 34. የሆነበት | 50. መሆን |
| 3. ዓመታት | 19. ቢያሳይም | 35. ለመስጠት | |
| 4. በድምፃዊ | 20. ዕድገት | 36. ስናየው | |
| 5. ደረሰ | 21. ከደንደው | 37. ሆና | |
| 6. ወደ | 22. የሆነ | 38. ክፍሎች | |
| 7. ከቀየ | 23. በየጊዜው | 39. አለባቸው | |
| 8. በድምፀ | 24. እነዚህም | 40. አስፈላጊ | |
| 9. ረቂቅ | 25. በሌሎች | 41. የለም | |
| 10. ዘኔ | 26. ሰፊ | 42. ብተገ | |
| 11. በሠለጠነው | 27. ወገኑ | 43. ሰውን | |
| 12. ሲሄድ | 28. አመቻቸሩ | 44. ከዘመን | |
| 13. እጅግ | 29. ሰው | 45. ብቻ | |
| 14. የሰው | 30. ነው | 46. የሠለጠነ | |
| 15. ዕድገት | 31. ካሉት | 47. ብዙ | |
| 16. መሆኑን | 32. በሚገባ | 48. ቦታ | |

### ለ/ የናሙና ሁለት መልሶች

| | | |
|---|---|---|
| 1. አጠገቤ | 7. የተፀውኦ ስም | 13. የመሰሉ |
| 2. ባስታውሳቸው | 8. ሰው | 14. ብቻ |
| 3. የተፀውኦ ስም | 9. አገር | 15. ተንኩሉ |
| 4. " " | 10. ለማግባት | 16. የተፀውኦ ስም |
| 5. እነሱን | 11. መገደርደሩን | 17. አግብቶ |
| 6. አይመስለኝም | 12. ነኝ | 18. ዛሬ |

19. በኛ
20. የተፀውኦ ስም
21. 〃 〃/ሴት/
22. በመጧ
23. ሣለ ቀስ
24. የተፀውኦ ስም
25. ማለት
26. ሲሰና ቅ
27. አምስ ተኛ
28. ዲሬክ ተር
29. ብሏ
30. በአቶ
31.

30. በአቶ
31. ዩለኛለ
32. ብር ቶና
33. ውሳው
34. ለማለት
35. አለፍ
36. አስ ተማሪው
37. ሲሉ
38. መ ፕረ ጊያው
39. ወደ
40. ሳይ
41. ትዝ
42. ምት

43. አገደ
44. ሲቀባጥር
45. አይቧሉም
46. ከፍሳቸን
47. ወደ
48. ይስሳሉ
49. ይጀምራሉ
50. ጨዋ

ጠ. <u>የናሙና ሦስት መልሶች</u>

1. በዓይ ነሕሊናው
2. የሚያደር ገው
3. ደብ ዳቤ
4. የመ ሰሰሉት
5. የ ተጻፈ ለትን
6. ይ ቀነቀስበ ታል
7. የጻፈ ሳትን
8. ሚሰ ትን
9. እንደሚሰማ ቸው
10. ነው

11. ጊዜ
12. መ ቼም
13. በጀር
14. ቀዜማ
15. ብ ቻ
16. የበሉትን
17. የረ ገጡትን
18. ያስ ታውሳል
19. ከ ነዚህ
20. ነገሮች

21. አንደመስ ተዋት
22. ሥራ
23. ያሀለ
24. ትዝ ታ
25. አስ ቴ
26. በረጋ
27. ምን
28. ነው
29. ያያለ
30. ደግሞ

31. የሚገርመው
32. ከሚም ጡው
33. የሚገርመው
34. ነው
35. ያለ
36. አሁን
37. በኅዘን
38. ምርምር
39. ፍ ቶግራፍ
40. ደረጃ
41. ዓይ ነቱ
42. የሕይወት
43. ዓይ ነት
44. እንደሚያቁ
45. ወይም
46. ለ ተመለከች
47. ዓይ ነት
48. ነው
49. ሰው
50. ተገ ተለተለው

| ሠ/ አያቴ አጠ. 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ናሙና ዎች | | | አማካይ | የመረዳት |
| | 1 | 2 | 3 | | |
| 69 | 48 | 38 | 30 | 39 | የጥገ ቆተ |
| 70 | 48 | 26 | 22 | 32 | 〃 |
| 71 | 48 | 26 | 22 | 32 | 〃 |
| 72 | 36 | 54 | 20 | 37 | 〃 |
| 73 | 46 | 52 | 20 | 39 | 〃 |
| 74 | 42 | 70 | 16 | 43 | 〃 |
| 75 | 34 | 48 | 18 | 44 | 〃 |
| 76 | 32 | 30 | 14 | 25 | 〃 |
| 77 | 38 | 26 | 18 | 27 | 〃 |
| 78 | 42 | 26 | 22 | 30 | 〃 |
| 79 | 12 | 12 | 14 | 13 | 〃 |
| 80 | 24 | 22 | 28 | 25 | 〃 |
| 81 | 22 | 4 | 14 | 13 | 〃 |

| ረ/ እስ.ኢ.እስ. ከፍተኛ ሃያ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ናሙና ዎች | | | አማካይ | የመረዳት ደረጃ |
| | 1 | 2 | 3 | | |
| 82 | 6 | 10 | 16 | 11 | ጥገ ቆተ |
| 83 | 18 | 20 | 6 | 15 | 〃 |
| 84 | 36 | 30 | 36 | 34 | 〃 |
| 85 | 48 | 44 | 12 | 38 | 〃 |
| 86 | 28 | 18 | 28 | 27 | 〃 |
| 87 | 32 | 34 | 16 | 27 | 〃 |
| 88 | 32 | 46 | 16 | 31 | 〃 |
| 89 | 48 | 52 | 20 | 40 | በዶገና |
| 90 | 32 | 24 | 30 | 29 | የጥገ ቆተ |

# አባሪ — ሸ

## የግንዛቤ ሙከራ ውጤት

ሀ/ የአየር ጤና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

| ተ.ቁ | ናሙናዎች 1 | 2 | 3 | አማካይ | የመረዳት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 30 | 34 | 32 | 32 | የጭንቀት |
| 02 | 28 | 20 | 24 | 24 | 〃 |
| 03 | 16 | 18 | 18 | 17 | 〃 |
| 04 | 16 | 18 | 116 | 17 | 〃 |
| 05 | 14 | 14 | 16 | 15 | 〃 |
| 06 | 26 | 26 | 28 | 27 | 〃 |
| 07 | 24 | 22 | 26 | 25 | 〃 |
| 08 | 28 | 22 | 26 | 25 | 〃 |
| 09 | 30 | 40 | 34 | 25 | 〃 |
| 10 | 10 | 10 | 12 | 11 | 〃 |
| 11 | 22 | 10 | 28 | 17 | 〃 |
| 12 | 14 | 10 | 12 | 12 | 〃 |
| 13 | 8 | 16 | 12 | 12 | 〃 |
| 14 | 10 | 26 | 20 | 19 | 〃 |
| 15 | 12 | 2 | 14 | 9 | 〃 |
| 16 | 22 | 14 | 18 | 18 | 〃 |
| 17 | 34 | 26 | 30 | 30 | 〃 |
| 18 | 8 | 8 | 12 | 9 | 〃 |
| 19 | 28 | 36 | 34 | 33 | 〃 |
| 20 | 26 | 28 | 28 | 27 | 〃 |
| 21 | 28 | 30 | 26 | 21 | 〃 |

ለ/ አዲስ ከተማ አጠ.2ኛ ደረጃ ት/ቤት

| ተ.ቁ | ናሙናዎች 1 | 2 | 3 | አማካይ | የመረዳት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | 10 | 18 | 20 | 16 | የጭንቀት |
| 23 | 16 | 18 | 18 | 17 | 〃 |
| 24 | 6 | 8 | 14 | 9 | 〃 |
| 25 | 14 | 22 | 20 | 19 | 〃 |
| 26 | 8 | 28 | 202 | 19 | 〃 |
| 27 | 10 | 8 | 12 | 10 | 〃 |
| 28 | 24 | 28 | 26 | 26 | 〃 |
| 29 | 40 | 26 | 38 | 35 | 〃 |
| 30 | 4 | 12 | 6 | 7 | 〃 |
| 31 | 32 | 30 | 32 | 31 | 〃 |
| 32 | 36 | 28 | 32 | 32 | 〃 |
| 33 | 18 | 20 | 20 | 19 | 〃 |
| 34 | 26 | 28 | 28 | 27 | 〃 |
| 35 | 22 | 34 | 36 | 31 | 〃 |
| 36 | 26 | 18 | 24 | 23 | 〃 |
| 37 | 12 | 18 | 16 | 15 | 〃 |
| 38 | 34 | 30 | 30 | 31 | 〃 |

ጠ/ ግንቦት ሃያ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ
ት/ቤት

| ተ. ቁ | ናሙናዎች 1 | 2 | 3 | አማካይ | የመረዳት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 39 | 14 | 18 | 18 | 17 | ጥገ ቀት |
| 40 | 20 | 28 | 24 | 24 | ״ |
| 41 | 36 | 42 | 40 | 39 | ״ |
| 42 | 2 | 4 | 16 | 7 | ״ |
| 43 | 16 | 6 | 14 | 12 | ״ |
| 44 | 26 | 16 | 22 | 21 | ״ |
| 45 | 10 | 1[illegible] | 18 | 14 | ״ |
| 46 | 22 | 22 | 24 | 23 | ״ |
| 47 | 24 | 20 | 24 | 23 | ״ |
| 48 | 14 | 20 | 18 | 17 | ״ |
| 49 | 18 | 22 | 22 | 21 | ״ |
| 50 | 46 | 46 | 28 | 40 | ״ |
| 51 | 26 | 36 | 12 | 25 | ״ |
| 52 | 16 | 44 | 14 | 25 | ״ |
| 53 | 44 | 36 | 18 | 33 | ״ |
| 54 | 46 | 40 | 30 | 35 | ״ |
| 55 | 6 | 18 | 6 | 10 | ״ |

ወ/ [illegible] ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ
ት/ቤት

| ተ. ቁ | ናሙናዎች 1 | 2 | 3 | አማካይ | የመረዳት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 56 | 26 | 20 | 18 | 21 | የጥገ ቀት |
| 57 | 24 | 24 | 14 | 24 | ״ |
| 58 | 22 | 12 | 10 | 15 | ״ |
| 59 | 34 | 20 | 22 | 25 | ״ |
| 60 | 38 | 24 | 2 | 21 | ״ |
| 61 | 14 | 6 | 10 | 10 | ״ |
| 62 | 28 | 32 | 14 | 26 | ״ |
| 63 | 42 | 44 | 18 | 36 | ״ |
| 64 | 26 | 34 | 24 | 28 | ״ |
| 65 | 36 | 24 | 22 | 28 | ״ |
| 66 | 20 | 32 | 26 | 226 | ״ |
| 67 | 34 | 28 | 10 | 22 | ״ |
| 68 | 30 | 28 | 14 | 24 | ״ |

# ማረጋገጫ

እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀዉ ተማሪ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የኔ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎችና መፅሐፍች በምንጭነት የጠቀስኩ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ::

ስም:- ጌታቸው አኛ

ፊርማ:- 

ቦታ:- የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ቀን:- ግንቦት 30/1986